አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር

# የቤንች ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ

በ

ውቤ ታደገ

የአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር መርሃ ግብር የኤም.ኤ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት

አማካሪ፡- ዘሪሁን አስፋው

ሰኔ 2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር

# የቤንች ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ

## የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

| | |
|---|---|
| ______________________ | ______________________ |
| አማካሪ | ፊርማ |
| ______________________ | ______________________ |
| የውስጥ ፈታኝ | ፊርማ |
| ______________________ | ______________________ |
| የውጭ ፈታኝ | ፊርማ |

# ምስጋና

የጥናታዊ ጽሑፌን ረቂቅ በማረም እና በማስተካከል ከመምህርነት እስከ አማካሪነት ድረስ ደከመኝ ሳይሉ ከተሞክሯቸው በማካፈል እና አስፈላጊውን እርማት በሰዓቱ በመስጠት ለዚህ እንድበቃ ላደረጉኝ ውድ መምህሬ ለዘሪሁን አስፋው (ተባባሪ ፕሮፌሰር) ምስጋናዬ ከልብ የመነጨ ነው፡፡ ይህ ስራ በተባለው ቀን ይደርስ ዘንድ የእርስዎ አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነበር፡፡ ቢሮዎ ሁሌም ለተማሪ ክፍት በመሆኑ እንደ ቤታችን ገብተን ያሻነን ጠይቀን እና ተረድተን እንድንሔድ ሲያደረጉት የነበረው ሁኔታ ጥናቴን ተደስቼ ከመስራቴም ባለፈ ወደ እርስዎ ስመጣ ያለጭንቀት ስለነበር ይኸው በድጋሜ ምስጋናዬ ይድረስዎ፡፡

በመስክ ቆይታዬ አስፈላጊውን መረጃ አገኝ ዘንድ፤ ዛሬ ነገ እያልኩ የእራሴን ስራ ለማፋጠን የእናንተን ስራ ወደኋላ ብላችሁ መረጃዎችን በመስጠት ለተባበራችሁኝ በሙሉ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡ በተለይ የደቡብ ቤንች ወረዳ የባህል እና ቱሪዝም ስራተኞች ከሚገባው በላይ ስላደረጋችሁልኝ ትብብር አመሰግናለሁ፡፡

ቤተሰቦቼ እና ጓደኞቼ (እናቴ፣ እህቴ፣ ቅመም አማረ (እሙዬ)፣ መ/ር ኃይሉ መገርሳ፣ መ/ር ፀሐዬ ፣ መ/ር ደምሴ ፀጋ፣) እንዲሁም የክፍል ጓደኞቼ ጥናትህ የት ደረሰ? የሚለው የዕለት ተዕለት ጥያቄያችሁ ጠንክሬ እንድሰራ እና ዛሬ ላይ እንድደርስ አግዞኛልና ምስጋና ይገባችኋል፡፡

ማውጫ


ይዘት ገጽ

ምስጋና ........ I

አጠቃሎ ........ V

1. መግቢያ ........ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 2

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 3

1.3 የጥናቱ ዓላማዎች ........ 4

1.4 የምርምር ጥያቄዎች ........ 4

1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት ........ 4

1.6 የጥናቱ ወሰን ........ 5

1.7 የጥናቱ ዘዴ ........ 5

1.7.1 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ........ 6

1.7.1.1 ምልከታ ........ 6

1.7.1.2 ቃለ መጠይቆች ........ 7

1.7.1.3 ተተኳሪ የቡድን ውይይት ........ 8

1.8 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች ........ 9

1.9 የመስክ ተሞክሮ ........ 10

2. ክለሳ ድርሳን ........ 13

2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........ 13

2.2 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ........ 22

2.2.1 ሞት ........ 22

2.2.2 ክዋኔ ........ 25

2.3 የሙሾ ግጥሞች ........ 30

3. የቤንች ብሔረሰብ ማህበረ ባህላዊ ዳራ ........ 32

3.1 የቤንች ማጂ ዞን አጠቃላይ ገጽታ ........ 32

3.2 የቤንች ብሔረሰብ አመጣጥ እና አሰፋፈር ..... 32
3.3 ቋንቋ ..... 34
3.4 ኢኮኖሚ ..... 35
3.5 ባህላዊ አስተዳደር ..... 35
3.6 እምነትና አምልኮ ..... 37
3.7 በዓል አከባበር ..... 38
3.8 የምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ ..... 39
4. የቤንች ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ..... 40
4.1 የባለቃልቻዎች የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ..... 41
4.1.1 ከቀብር በፊት ..... 41
4.1.2 በቀብር ጊዜ ..... 46
4.1.3 ከቀብር በኋላ ..... 56
4.2 የባላባትና የባለሚያንግ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ..... 57
4.2.1 ከቀብር በፊት ..... 58
4.2.2 በቀብር ጊዜ ..... 61
4.2.3 ከቀብር በኋላ ..... 64
4.3 የእድሜ ባለፀጎች የለቅሶ ስርዓት ..... 65
4.3.1 ከቀብር በፊት ..... 65
4.3.2 በቀብር ጊዜ ..... 68
4.3.3 ከቀብር በኋላ ..... 71
4.4 የወጣቶች የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ..... 72
4.4.1 ከቀብር በፊት ..... 72
4.4.2 በቀብር ጊዜ ..... 74
4.4.3 ከቀብር በኋላ ..... 77
4.5 የሕፃናት የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ..... 78

5. ማጠቃለያ እና ይሁንታ ........ 79

5.1 ማጠቃለያ ........ 79

5.2 ይሁንታ ........ 80

ዋቢ ጽሑፎች ........ 82

አባሪዎች

አባሪ አንድ፡- የመረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል

አባሪ ሁለት፡- ለመነሻ ሀሳብ የተዘጋጁ ጥያቄዎች

አባሪ ሶስት፡- የተሰበሰቡ የሙሾ ግጥሞች

አባሪ አራት፡- የጥናቱን ቦታ የሚያመለክቱ ካርታዎች

# አጠቃሎ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የቤንች ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ በሚል ርዕስ የቀረበ ነው፡፡ ትኩረቱም የቤንች ብሔረሰብን የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔን መግለፅ ላይ ነው፡፡ የጥናቱ ዓላማም የቤንች ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔን ከቃል ግጥሞቹ ጋር በማያያዝ ምን እንደሚመስል መተንተን ነው፡፡

ለዚህ ዓላማ መሳካት ይረዳ ዘንድም ሶስቱ የመስክ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች (ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ እና የተተኳሪ ቡድን ውይይት) አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ እነዚህ ዘዴዎችም ተግባራዊ ይሆኑ ዘንድ በሶስት ተፈጥሯዊ የለቅሶ መቼቶች በመገኘት እና ዳር ቆሞ በመመልከት መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡ በዚህም መሰረት በቤንች ብሔረሰብ የተለያዩ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔዎች በሟች ማህበራዊ ደረጃ ፣በፆታ እና እድሜ ላይ በመመስረት በአምስት ተከፍለው እንደሚከወኑ ታውቋል፡፡

በእያንዳንዱ የለቅሶ ክዋኔ ውስጥም የሚተላለፉ መልዕክቶች ሲኖሩ የመልዕክቶቹ ይዘትም እንደሟቹ ማንነት እና ማህበራዊ ደረጃ የተለያዩ መሆናቸው በጥናቱ ታይቷል፡፡ ከሟች አንፃር የእምነት መሪ፣ የአካባቢ አስተዳዳሪ፣ የሐገር ሽማግሌ፣ ወዘተ መሆናቸውን ከመግለፃቸው ጎን ለጎን የሟችን ተግባርና ማንነት እንደሚያመለክቱ ታውቋል፡፡ በዋናነት በግኝቱም የብሔረሰቡ የታሪክ ተሳታፊነትን የሚያፀኑ፣ የብሔረሰቡ ቋሚ የሆነ ሀገረሰባዊ የስልጣን ሽግግርን የሚያበስሩ፣ የብሔረሰቡን ወይም የጎሳውን የዘር ግንድ መሰረት የሚገልፁ፣ የብሔረሰቡን ሐገረሰባዊ እምነት የሚገልፁና የሚያስጠብቁ፣ ወዘተ የሚሉት ይዘቶች መኖራቸውን ጥናቱ አሳይቷል፡፡ በአጠቃላይ በብሔረሰቡ ውስጥ በሚገኙ (በእድሜ፣ በፆታና በማህበራዊ ደረጃ) አንፃር ለየት ያሉ የለቅሶ ክዋኔዎች መኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

## 1. መግቢያ

ፎክሎር ዘርፈ ብዙ ነው፡፡ ይህ ዘርፈ ብዙ የሆነ መስክ ደግሞ ከሰው ልጅ ጋር የጠበቀ ቁርኝት አለው፡፡ በፎክሎር ሰዎች አስተሳሰባቸውን፣ አመለካከታቸውን፣ እምነታቸውን፣ ደስታቸውን፣ ሐዘናቸውን ወዘተ. ይገልፃሉ፡፡

ሰዎች እርስ በርስ ባላቸው ማህበራዊ ግንኙነት የሐዘን ስሜታቸውን ከሚገልጹባቸው ፎክሎራዊ ጉዳዮች አንዱ የለቅሶ ስርዓት ነው፡፡ እንደየማህበረሰቡ ባህል የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔውም ይለያያል፡፡ በሀገራችን ያለውን ስርዓት ብንወስድ፤ በአንዳንድ አካባቢ ደረት በመድቃት፣ ፊት በመቧጠጥ፣ ፀጉር በመላጨት ወዘተ ይለቀሳል፡፡ በሌላ አካባቢ ደግሞ በጭፈራ ወይም በዘፈን የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔውን ያከናውናሉ፡፡ ይሁንና በየማህበረሰቡ የሚደረጉ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔዎች የራሳቸው የሆነ መነሻ ምክንያት አላቸው፡፡

በብዙ ባህሎች ውስጥ ከለቅሶ ክዋኔው ጋር ተነጥለው የማይታዩት ደግሞ የሙሾ ቃል ግጥሞች ናቸው፡፡ ለለቅሶው ድምቀትን ይሰጣሉ፡፡ እነዚህ ግጥሞችም ፉከራ፣ ቀረርቶ ወዘተ. ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በሀገራችን ካሉ ብሔረሰቦች መካከልም በለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ጊዜ የሙሾ ቃል ግጥሞችን ከክዋኔው ጋር አያይዘው ከሚከውኑ መካከል የቤንች ብሔረሰብ ይጠቀሳል፡፡

የዚህ ጥናት ትኩረትም በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ በሚገኘው የቤንች ብሔረሰብ የለቅሶ ሥርዓተ ክዋኔና የለቅሶ ቃል ግጥሞች ትንተና ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የቤንች ብሔረሰብ እንደሌሎች የሀገራችን ብሔረሰቦች ሁሉ ሰው ሲሞት የራሱ የሆነ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ አለው፡፡ ከለቅሶ ስነ ስርዓቱ ጋር ተያይዘው የሚከወኑ የሙሾ ቃል ግጥሞችም አሉት፡፡

እኔም በቤንች ብሔረሰብ ባህል የማህበረሰቡ አባል የሆነ ሰው ሲሞት የሚኖረውን የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ከቃል ግጥሞች ጋር አያይዤ ተንትኛለሁ፡፡ ጥናቱን ለማካሄድ ለጥናቱ ተስማሚ የሆነውን የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ (*Performance theory*) ን መሰረት በማድረግ ነው፡፡

የጥናት ወረቀቱ አወቃቀርም፤ በምዕራፍ አንድ በመግቢያ ስር የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዓላማዎች፣ የምርምር ጥያቄዎች፣ የመረጃ መሰብሰቢያና መተንተኛ መንገዶች፣ የጥናቱ ወሰን እና የጥናቱ ውጤት አስፈላጊነት ተካተዋል፡፡ በምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳናት እና ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ቀርበዋል፡፡ ምዕራፍ ሶስት ስለ ቤንች ብሔረሰብ አካባቢያዊ ዳራ በተለይም ማህበረ-ባህላዊ አውድ (*social- cultural context*) በዝርዝር የተካተቱበት ክፍል

ነው። ምዕራፍ አራት ደግሞ በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች ተተንትነው የቀረቡበት ክፍል ሲሆን በመጨረሻም በምዕራፍ አምስት ማጠቃለያና የይሁንታ ሃሳቦች ቀርበዋል።

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የቤንች ብሔረሰብ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ይገኛል። የብሔረሰቡ አባላት በጋራ ከሚያከናውኗቸው ማህበራዊ ጉዳዮች አንዱ ለቅሶ ነው። የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔው በብሔረሰቡ አስተሳሰብ፣ ፍልስፍና እና እምነት የተቃኘ ነው። ክዋኔውንም ለማድመቅ የተለያዩ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ይጠቀማሉ። ለምሳሌ፡- ቁሳዊ ባህሎች፣ ስነ ቃሎች፣ ትውን ጥበባት ወዘተ. የክዋኔው አካላት ናቸው። ከክዋኔው ጋር ተያይዘው የሚመጡት እነዚህ ጉዳዮች የዚህ ጥናት ተተኳሪዎች ናቸው።

ሞት፣ የሙሾ ቃል ግጥሞች፣ የቀብር ስነ ስርዓት ወዘተ. የሚሉ ፅንሰ ሀሳቦችን በማንሳት በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት ተማሪዎች የተለያዩ ጥናቶች ከአሁን በፊት ተካሂደዋል። ስራዎቹም በአብዛኛው ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ናቸው። ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ አምስት ጥናታዊ ስራዎች ይገኛሉ። እነሱም ሞገስ ሚካኤል (2002)[1]፣ ሕይወት አበሩ (2003)፣ በሪሁን መንግስቱ (2004)፣ ዘላለም ፋንቱ (2004) እና ማናየ እንግዳው (2005) ናቸው።

ከላይ እንደጠቀስኩት ለባችለር ዲግሪ ማሟያነት በለቅሶ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ትኩረት ያደረጉ በርከት ያሉ ጥናቶች ተሰርተዋል። አብዛኞቹ ማለት ይቻላል፤ በሙሾ ቃል ግጥሞች ይዘት ትንተና ላይ ያተኮሩ ናቸው። ለምሳሌም፡- ሐረገወይን ድፋባቸው (1974)፣ ባልከው ቸርነት (1974)፣ ወርቅነሽ ደምለው (1992)፣ ዘላለም እዮብ (1995)፣ ዳምጠው በቀለ (1996)፣ ፈለገህይወት ዘገዬ (1997) ወዘተ. መጥቀስ ይቻላል።

በሁለቱም ደረጃዎች (በመጀመሪያና በሁለተኛ ዲግሪ ተመራቂዎች) የቀረቡ ጥናቶች በአብዛኛው ወይ ክዋኔው ላይ አልያም ደግሞ ቃል ግጥሞቹ (ሙሾ) ላይ በመመስረት የተጠኑ ናቸው። የተወሰኑ የመጀመሪያ ዲግሪ ተመራቂዎች ሁለቱንም (የለቅሶ ክዋኔውን እና የለቅሶ ግጥሞችን)

---

[1] በዚህ ወረቀት በአማርኛ ለተጠቀሱ ስሞች አመተ ምህርት ስጠቅስ እንደ ኢትዮጵያውያን አቆጣጠር፤ በእንግሊዝኛ ለተጠቀሱ ስሞች ደግሞ እንደ አውሮጳውያን አቆጣጠር ነው።

ያጠኑም አሉ። ከደረጃቸው አንፃር ጥሩ ጅምር ቢሆንም በበቂ ሁኔታ አጥንተዋል ለማለት አያስደፍርም።

በሁሉም ጥናቶች መገንዘብ እንደሚቻለው በተለያዩ አካባቢዎች የተለየ የለቅሶ ሥርዓት ክዋኔ መኖሩን ነው። ስለዚህ በለቅሶ ላይ የተደረጉ ጥናቶች ምን ደረጃ ላይ ደረሰ? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተጠኑ ሥራዎችን ዋቢ በማድረግ ጥልቅ የሆነ ጥናት ተደርጓል ማለት አይቻልም። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ የአብዛኛዎቹ ጥናቶች ወይ በክዋኔ ላይ ከፍ ካለም በሙሾ ግጥሞቹ ላይ በተናጥል የተካሄዱ መሆናቸው ነው። የለቅሶ ክዋኔ ካለ የሙሾ ግጥሞች መኖራቸው ግድ ነው። ስለዚህ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔን ለማጥናት ሁለቱን (ክዋኔና ቃል ግጥም) መነጣጠል አይቻልም ባይ ነኝ። በተለይ የለቅሶ ቃል ግጥሞችን ይዘት ለማጥናት እና ለመተንተን የግድ አውድ እና አጋጣሚ (*Context and occasion*) መኖር አለበት። አውድና አጋጣሚ የሚኖረው ደግሞ ክዋኔው ሲኖር ነው።

በእኔ ጥናት ግን ክዋኔ እና ቃል ግጥምን በጥምረት በማየት ከላይ የገለጽኩትን ክፍተት በጥቂቱም ቢሆን ለመድፈን ተሞክሯል። በመሆኑም የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት የቤንች ብሔረሰብን የለቅሶ ክዋኔ እና የለቅሶ ቃል ግጥሞች ይዘት መተንተን ነው።

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የቤንች ብሔረሰብን በሚመለከት የተለያዩ ጥናታዊ ጽሁፎች ተጠንተዋል። ከነዚህም ጥናቶች መካከል "ተረት እና ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ የቤንች ብሔረሰቦች ትውን ጥበባት፣ ቃላዊ ዝርው ተረኮች፣ የቤንች ብሔረሰብ ቋንቋ፣" የሚሉት ይጠቀሳሉ። ነገር ግን በብሔረሰቡ ዘንድ ሰው ሲሞት የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ምን እንደሚመስል እና የሙሾ ቃል ግጥሞችን ያጠና መኖሩን እስካሁን አላገኘሁም። ስለዚህ ጉዳዩ ቢጠና ስለብሔረሰቡ ባህል ተጨማሪ ግብዓት ይሆናል ከሚል የመነጨ ነው።

ለተወሰኑ ዓመታት ከብሔረሰቡ ጋር ስለቆየሁና በማህበራዊ ጉዳዮች (በሰርግ፣ በለቅሶ፣ ወዘተ.) ስለተሳተፍኩ እና አከዋወኑን በተወሰነ ደረጃ ዳር ቁሜ ለመመልከት ስለቻልኩ አሁን ባለኝ ፎክሎራዊ እውቀትና ግንዛቤ ታግዤ ባጠናው አንድም ብሔረሰቡን በደንብ ለማወቅ በሌላ በኩል ደግሞ ለሌሎች (ብሄረሰቡን ለማያውቁት) ለማሳወቅ ይጠቅማል ብዬ ነው።

### 1.3 የጥናቱ ዓላማዎች

ጥናቱ ዓቢይ እና ዝርዝር ዓላማዎችን የያዘ ነው። የዚህ ጥናት ዓቢይ ዓላማ የቤንች ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔን ከቃል ግጥሞቹ ጋር በማያያዝ ትንታኔ መስጠት ነው። ይህን አቢይ አላማ ያደረገው ጥናት የቤንች ብሔረሰብ የለቅሶ ሥርዓት ክዋኔ ላይ ምን ነገሮች እንደሚደረጉ መግለፅ፤ እና የቤንች ብሔረሰብን የሙሾ ቃል ግጥሞችን በማሰባሰብ ይዘታቸውን መተርጎም፤ የሚሉ ዝርዝር አላማዎች አሉት።

### 1.4 የምርምር ጥያቄዎች

ይህ ጥናት የሚከተሉትን የምርምር ጥያቄዎች ይመልሳል ተብሎ ይገመታል።

1. የቤንች ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ምን ይመስላል?
2. የቤንች ብሔረሰብ የለቅሶ ቃል ግጥሞች ምን ምን ጉዳዮችን ያነሳሉ?
3. በቤንች ብሔረሰብ ዘንድ ሰው ሲሞት ማዘናቸውን እንዴት ይገልፃሉ?
4. በቤንች ብሔረሰብ ነዋሪዎች ዘንድ በእድሜ፣ በፆታ፣ በማህበራዊ ደረጃ ወዘተ. ሳቢያ የተለየ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ይደረጋል?

### 1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት

ጥናቱ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፤ ተብሎ ይታመናል።

ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ማጥናት ህዝቡን ማጥናት ነው። ህዝቡን የምናጠናው ደግሞ ከህዝቡ የዕለት ተዕለት ገጠመኙን እና ማህበራዊ ክንውኑን መሰረት በማድረግ ነው። ለቅሶም የቤንች ብሔረሰብ አንድ ባህል ስለሆነ ስለብሔረሰቡ የተወሰነ ዕውቀት ሊሰጥ ይችላል።

የቤንችን ብሔረሰብ ባህል፣ ማንነት ወዘተ. ለሚያጠኑ ተመራማሪዎች የመነሻ ሃሳብ ይሰጣል። እንዲሁም በተመሳሳይ ርዕስ ለሚያጠኑ መሰል ተማሪዎች እንደ አንድ ግብዓት ሊያገለግል ይችላል።

የብሔረሰቡን አጠቃላይ ታሪክና ባህል ለሚያጠኑ እና በመጽሐፍ መልክ ለሚያዘጋጁ ሰዎች ከባህል አንፃር ጥናቱ የራሱን ድርሻ ሊያበረክት ይችላል።

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በቤንች ብሔረሰብ የለቅሶ ሥርዓተ ክዋኔ እና በለቅሶው ወቅት በሚወርዱ የለቅሶ ቃል ግጥሞች ላይ የተወሰነ ነው፡፡ ብሔረሰቡ ለክዋኔው ማድመቂያ የሚገለገልባቸው ማንኛውንም ፎክሎራዊ ጉዳዮች ጥናቱ አካቷል፡፡

የቤንች ብሔረሰብ አባላት በዋናነት በሶስት ወረዳዎች ሰፍረው ይገኛሉ፡፡ እነሱም ሰሜን ቤንች፣ ደቡብ ቤንች እና ሼ ቤንች ወረዳዎች ናቸው፡፡ ከእነዚህ ወረዳዎች መካከል ብሔረሰቡ በስፋት ሰፍሮ የሚገኘው በደቡብ ቤንች እና ሰሜን ቤንች ወረዳዎች ነው፡፡ ይህ ጥናት ብሔረሰቡ በብዛት ሰፍሮ በሚገኙባቸው ወረዳዎች ላይ ብቻ የተመሰረተ ነው፡፡ ሼ ቤንች ወረዳ ያልተካተተበት ምክንያት በአብዛኛው የቤንች ብሔረሰብ ከሌሎች ብሔረሰቦች ጋር ተሰባጥረው ስለሚኖሩ ነው፡፡

## 1.7 የጥናቱ ዘዴ

የዚህን ጥናት አላማ ከግብ ለማድረስ ተገቢ የሚሆነው ንድፈ ሀሳብ የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ (*performance theory*) ነው፡፡ ለክዋኔ ንድፈ ሀሳብ የሚሆነው ዘዴ ደግሞ ክዋኔ ተኮር (*Performance centered approach*) ነው፡፡ ይህ ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት በለቅሶው ስርዓተ ክዋኔ ወቅት የሚከወኑ ማናቸውንም ጉዳዮች ለማጥናት ከዚህ ንድፈ ሀሳብ የተሻለ ዘዴ ሊኖር አይችልም ብየ ስለአመንኩ ነው፡፡ እንደ Bauman (1977,9) አገላለጽ በቤንች ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ወቅት በከዋኙ እና በታዳሚዎች (በተሳታፊዎች) መካከል ስላሉት ተምሳሌቶች፣ ትዕምርቶች፣ ወዘተ በአውዱ ለመመርመር እና ለማጥናት ንድፈ ሀሳቡ ያግዛል፡፡ በተጨማሪም ጥናቱ በመስክ ላይ የሚከወንና የሚጠናው የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔና የለቅሶ ግጥሞች በመሆኑ፣ ዘዴው ስለአቅራቢው፣ ስለተመልካቹ፣ ስለመቼቱ፣ በአቅራቢውና በታዳሚው መካከል ስላለው ግንኙነትና አስተያየት፣ ስለአውዱ፣ እንዲሁም በክዋኔ ወቅት ስላለው ደንብ ለመረዳትና ለመተርጎም አጋዥ በመሆኑ ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የመስክ መቼቶች ከሚባሉት መካከልም በጥናቱ ተፈጥሯዊ መቼት (*Natural settings*) ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ይህን መቼት የመረጥኩበት ምክንያት ክዋኔውን (የለቅሶ) በተፈጥሯዊ መቼት ለማግኘት አስቸጋሪ ባለመሆኑና በተፈጥሯዊ መቼት ተጠቅሞ መረጃ መሰብሰብ መቻል ለተመራማሪው የተሟላ መረጃ ለማግኘት ከፍተኛ እድል ስለሚፈጥር ነው፡፡

የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ በመስክ በመታገዝ መረጃዎችን መሰብሰብን የሚጠይቅ በመሆኑ፣ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተግባር ላይ ውለዋል፡፡ እነሱም ቀጥለው ይቀርባሉ፡፡

### 1.7.1 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ይህን ጥናት ለማካሄድ መረጃዎችን ከቀዳማይና ከካልዓይ የመረጃ ምንጮች ተሰብስበዋል፡፡ በካልዓይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የቤንች ብሔረሰብን አስመልክቶ የተጻፉ ጽሁፎች፣ እንዲሁም ከርዕሱ ጋር የሚዛመዱ የምርምር ውጤቶች ተሰብስበዋል፡፡ በተጨማሪም ለጥናቱ ግብዓት ይሆናሉ የምላቸውን መረጃዎች ከተለያዩ የመረጃ መረቦች (ከጋዜጣ፣ ከመጽሔት፣ ከድረ-ገጽ፣ ከታሪካዊ መዛግብት ወዘተ.) ሰብስቤያለሁ፡፡

በቀዳማይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ደግሞ ጥናቱ መስክ ወጥቶ መረጃ መሰብሰብን ስለሚጠይቅ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቆች እና በተተኳሪ የቡድን ውይይት በመታገዝ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ እነዚህን ሦስቱን የፎክሎር የመስክ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተጠቀምኩበት ምክንያት እያንዳንዱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የራሱ የሆነ ጠንካራ እና ደካማ ጎን ስላለው የአንዱን ድክመት የሌላው ጥንካሬ እንዲሸፍንልኝ ለማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በመስክ ላይ እንዴት እንደተጠቀምኩ እንደሚከተለው ይቀርባሉ፡፡

#### 1.7.1.1 ምልከታ

ምልከታ ለጥናቱ የተመረጠ አንዱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው፡፡ ለዚህ ጥናት የተመረጠበት ምክንያትም ጥናቱ መስክ ወጥቶ ጉዳዩ በሚከወንበት ጊዜ በቦታው ተገኝቶ መመልከትን ስለሚጠይቅ ነው፡፡ Goldstein (1964,77) የምልከታን አስፈላጊነት ወይም ጠቀሜታ ሲገልጹ "*Observation methods used by the field worker in obtaining data by direct observation, looking from the outside in and describing the situation as he sees it*" ይላሉ፡፡

በተጨማሪም ምልከታ በአይን መመልከትን ብቻ ሳይሆን አጥኚው የሚመለከተውን ጉዳይ በሌሎች የስሜት ህዋሳቶቹ እንዲረዳ እና እንዲገነዘብ የማድረግ ኃይል አለው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ Goldstein (1964,77) *"the term "Observation" as used in this situation, but*

*also involves a full range of sensual experience including hearing, feeling, smelling, and tasting…"* ይላሉ፡፡

ሌላው ጥናቱ የሚመርጠው የክዋኔ ንድፈ ሃሳብ (*performance theory*) ምልከታን መሰረት ያደረገ ስለሆነ ነው፡፡ ያለ ምልከታ ክዋኔን ማየት ስለሚያስቸግር ለመረጃ መሰብሰቢያነት መርጨዋለሁ፡፡ የምልከታ ዘዴ የከዋኞችን የክዋኔ ስልት (አካላዊ እንቅስቃሴ፣ ድምጽ አወጣጥ፣ የተሳታፊዎች ሚና፣ የከዋኝ- ተሳታፊ ተራክቦ ወዘተ) ምን እንደሚመስል ዳር ቆሞ ለመመልከት ያግዛል፡፡

የቤንች ብሔረሰብ ተወላጅ ስላልሆንኩ እና ቋንቋውንም ስለማልችል ትኩረቴ የሆነውም ሳይሳተፉ የሚደረግ ምልከታ (*non-participation observation*) ነው፡፡ በመሆኑም አስተርጓሚዎችን በመያዝ እና የሚሉትን (በክዋኔው ጊዜ) እንዲገልፁልኝ በማድረግ መረጃዎችን መሰብሰብ ተችሏል፡፡ በተያያዘም በቴክኒክነት የተጠቀምኩት ያልተገደበ (*open-ended*) የተሰኘውን የምልከታ ቴክኒክ ዓይነት ነው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ የመመልከት አቅሜን ሳልገድብ ወይም ሳልወስን በምመለከትበት ወቅት ለጥናቴ የሚያግዙኝ የተለያዩ መሰረታዊ መረጃዎችን እንዳገኝ ስለሚረዳኝ ነው፡፡ በዚህ መሰረትም መስክ በቆየሁባቸው ጊዜዎች ሶስት የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔዎችን ተመልክቻለሁ፡፡

#### 1.7.1.2 ቃለ መጠይቆች

ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በምልከታ ወቅት ያየኋቸውን እና ማህበረሰቡ እንዲመልስልኝ የምፈልጋቸውን ጥያቄዎች እንድጠይቅ ስለሚያግዘኝ ልመርጠው ችያለሁ፡፡ ጥናቴ ከቃለ መጠይቅ አይነቶችም ጥልቅ (*in-depth*) ቃለ መጠይቅን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ለጥናቱ በቂና ትክክለኛ የሆኑ መረጃዎችን መሰብሰብ ስለሚያስችል ነው፡፡ የቃለ መጠይቅ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ብሔረሰቡ በለቅሶ ስርዓተ ክዋኔው ሊያስተላልፍ የፈለገውን ይዘት፣ የክዋኔው ሰዓት፣ የሙሾ አውራጁ ማህበራዊ ደረጃ እና ሙያ፣ የከዋኝ ተሳታፊ ማንነትና ሚና፣ ወዘተ ምን እንደሚመስል ጠይቆ መረጃ ለመሰብሰብ ስለሚያግዝ ነው፡፡

ለቃለ መጠይቁ የተዘጋጁ ጥያቄዎች በሁለት መንገድ (ቴክኒክ) ተዋቅረዋል፡፡ የመጀመሪያው በምልከታ የተፈጠሩ ጥያቄዎችን መረጃ አቀባዮች ከመገኘታቸው በፊት ቀድመው በተዘጋጁ ጥያቄዎች (*structured interview*) አማካይነት መረጃ መሰብሰብ የሚያስችል ሲሆን ሁለተኛው

ደግሞ በንግግር ወቅት በአውዱ በድንገት የሚፈጠሩ ጥያቄዎች (*unstructured interviews*) መሰረት ያደረገ ነው፡፡

በቃለ መጠይቁ የተካተቱት መረጃ አቀባዮችን በኢላማ ተኮር የናሙና አወሳሰድ በአካባቢው ከታወቁ ሰዎች፣ በስራ ጠባያቸው የተነሳ ባህሉን በቅርበት ከሚያውቁ፣ በምልከታ ወቅት ሲከውኑ ከተመለከትኳቸው ከዋኞች፣ ከዞኑ (የቤንች ማጅ ዞን) የባህል እና ቱሪዝም ቢሮ ሐላፊዎች የተመረጡ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ሀያ አንድ (21) የሚሆኑ መረጃ አቀባዮችን ቃለ መጠይቅ አድርጌያለሁ፡፡ ከዚህ መካከል አስራ ስምንቱ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ናቸው፡፡

### 1.7.1.3 ተተኳሪ የቡድን ውይይት

ይህ ለጥናቱ በመረጃ መሰብሰቢያነት የተመረጠ ሶስተኛው ዘዴ ነው፡፡ የተመረጠበት ምክንያትም ከላይ በጠቀስኳቸው ሁለት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ያልተመለሱ ጥያቄዎችን ለመመለስ እና አጠራጣሪ የሆኑ መረጃዎችን ለማረጋገጥ የሚያስችል ዘዴ በመሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም ስምንት ሰዎችን በቡድን (ሁለት ጊዜ) በማወያየት መረጃ ተሰብስቧል፡፡ ስምንት ሰዎችን የመረጥኩበት ምክንያት Kruegor (1994,79) ተተኳሪ የቡድን ውይይት አባላት ከ 8-10 ቢሆን የተሻለ መረጃ መሰብሰብ ይቻላል፤ ከሚሉት ሐሳብ በመነሳት ነው፡፡

በቡድን ውይይቱ የተሳተፉት ሰዎች ስለምጠይቃቸው ጥያቄዎች ጥሩ ግንዛቤ ያላቸው ናቸው፡፡ የእድሜ ባለፀጎችን፣ ታሪኩንና ባህሉን የሚያውቁ ሰዎችን የብሔረሰቡ አባላት እንዲጠቁሙኝ አስቀድሜ ስለሰዎቹ በመሰብሰብ እንዲወያዩ አድርጌያለሁ፡፡ ጥያቄዎቹም በምልከታና በቃለ መጠይቅ ወቅት ቀድመው የተወሰኑ በመሆኑ አላማዬን በመግለፅ፤ የተገደበ (*structured*) ቴክኒክን በመጠቀም የቡድን ውይይቱን አካሂጃለሁ፡፡

በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ፣በተተኳሪ የቡድን ውይይት እንዲሁም ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች የተገኙት መረጃዎች በሙሉ በገለፃ መልክ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ የገለፃ የመረጃ መተንተኛ ስልት የተመረጠበት ምክንያት ከመረጥኳቸው የመስክ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች እና ተፈጥሯዊ መቼት ጋር ተስማሚ ስለሚሆን ነው፡፡

## 1.8 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች

ይህን ጥናት በማጠናበት ጊዜ የተለያዩ ችግሮች ገጥመውኛል። ከእነዚህም መካከል የመጀመሪያው የቋንቋ ችግር ነው። የቤንችኛ ቋንቋ ፊደል አልተቀረፀለትም። በመሆኑም ቋንቋውን ወደ አማርኛ ለመተርጎም እና በጽሁፍ ለማስፈር ሲወክሏቸው የሚችሉ የተወሰኑ አቻ ድምፆች በአማርኛ የሉም። ይህም በመሆኑ የተሰበሰቡ የሙሾ ግጥሞችን ወደ አማርኛ በቀጥታ ለመመለስ ከቋንቋ አንፃር አስቸጋሪ ነበር። ይህንንም ችግር ከቃል በቃል ትርጉም ይልቅ ይዘቱ ላይ በማተኮር ለማቃለል ተችሏል።

ሁለተኛው ችግር ሁሉንም የለቅሶ አይነቶች በተፈጥሯዊ መቼት ማግኘት አለመቻሉ ነው። የተገኙትም ቢሆኑ ከክዋኔው መጀመሪያ እስከ ፍፃሜ ድረስ ያለውን ዝግጅት ሙሉ በሙሉ እንድመለከት ባህሉ አለመፍቀዱ ደግሞ ሌላው እንቅፋት ነው። ለእነዚህ ችግሮችም ከአሁን በፊት በመሳተፍ እና ሙሉውን የክዋኔ ሂደት በማየት እንዲሁም “ቆንብ እና ወይዘስ” (የባለቃልቻው እና የባላባቱ አገልጋዮች በተከታታይ) በመሆን ሲያገለግሉ የነበሩ ሰዎችን በመረጃ አቀባይነት በማካተት ችግሩን መፍታት ተችሏል። እንዲሁም በ 30/01/05 ዓ.ም የተቀረፀ የአንድን የባለቃልቻ የለቅሶ ስርዓት በሚገልፅ ቪዲዮ ፊልም በመታገዝ በተፈጥሯዊ መቼት ያላገኘሁትን የለቅሶ ስርዓት ለማጥናት ችያለሁ።

በተፈጥሯዊ መቼት የተገኙ የለቅሶ ስርዓቶችን ለመቅረፅ የሚጠየቀው የገንዘብ መጠን ከተመደበው የምርምር ገንዘብ ጋር ያልተመጣጠነ መሆኑ ነው። ለዚህ ማስረጃነት በአንድ የለቅሶ ስርዓት ላይ የተጠየኩትን 10,000 ብር መጥቀስ ይቻላል። በመሆኑም ይህን ያህል ክፍያ ለመክፈል ስለማልችል አንዳንዶችን ዳር ቆሞ በመመልከት፤ ዝቅተኛ ክፍያ የሚጠይቁትን ደግሞ በመክፈል መረጃዎችን ለመሰብሰብ ችያለሁ። በተጨማሪም አንዳንድ መረጃ አቀባዮችን ቃለ መጠይቅ በማደርግበት ጊዜ የሚጠይቁኝ የገንዘብ መጠን ከፍተኛ መሆኑ የሚጠቀስ ነው። በአንፃሩ ደግሞ አንዳንድ መረጃ አቀባዮች ያለምንም ክፍያ መረጃዎችን ስለሚሰጡኝ ለእነሱ ያሰብኩትን ክፍያ ለሌሎች በመጨመር ልወጣው ችያለሁ።

እነዚህ ከላይ የጠቀስኳቸው በጥናቱ ጊዜ ያጋጠሙ ዋና ችግሮች ይሁኑ እንጂ ሌሎች (የመጓጓዣ እጥረት፣ የምግብ ማጣት እና ለባህሉ ምግብ እንግዳ መሆን፣ ወዘተ) የዚህ ጥናት ተጨማሪ ችግሮች ነበሩ።

### 1.9 የመስክ ተሞክሮ

ወደ መስክ ከመሄዴ በፊት በቤተ መጻሕፍት በመታገዝ ስለምሔድበት አካባቢ በተለያዩ ሰዎች የተሰሩ ስራዎችን ተመልክቻለሁ። በተለይም በቤተ መጻሕፍት የሚገኙ መጽሐፎች፣ ጆርናሎች እንዲሁም የምርምር ስራዎች ተጠቃሾች ናቸው። እነዚህን ስራዎች ካነበብኩ እና አስፈላጊውን ማስታዎሻ ከያዝኩ በኋላ ለመስክ ስራው የሚያስፈልጉ መሳሪያዎችን እንደ (መቅረፀ ድምፅ፣ ካሴቶች፣ ቪዲዮ ካሜራ፣ ፎቶ ካሜራ፣ ማስታወሻ ደብተሮች) በመግዛት እና በመዋስ ዝግጅቴን አጠናቀቅኩ።

ከዚያም ከአዲስ አበባ 561 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ወደምትገኘው የቤንች ማጂ ዞን ዋና ከተማ (ሚዛን) በ 22/04/05 ዓ.ም ጉዞ አደረኩ። በማግስቱ ከቀኑ 9:25 አካባቢ ደረስኩ። ለአንድ ሳምንት ያህል የብሔረሰቡ አባላት የሚገኙባቸውን ሶስት ወረዳዎች ከጓደኛዬ (ከኃይሉ መገርሳ) ጋር ተዟዙረን ጎበኘን። እግረ መንገዴንም በአካባቢው ጥናት ያደረጉ ሰዎችን ተዋወኩ። ከእነዚህ ሰዎች መካከልም ፀሐዬ የተባሉ መምህር አንዱ ናቸው። እሳቸውም በጥናታቸው ወቅት ያጋጠሟቸውን እኩይ እና ሰናይ ገጠመኞች ስለነገሩኝ ከሚያጋጥሙኝ ችግሮች ቀድሜ እንድጠነቀቅ ረድተውኛል። ሌሎችን መረጃ አቀባዮችን የማገኝበትን መንገድም ጠቆሙኝ።

ከሳምንት ጉብኝት እና ከአንዳንድ ሰዎች ትውውቅ በኋላ በ 30/04/05 ዓ.ም በትምህርት ክፍሉ የተፃፈልኝን የድጋፍ ደብዳቤ በመያዝ ለቤንች ማጂ ዞን ባህልና ማስታወቂያ ቢሮ እንዲሁም ለዞኑ አስተዳደር የሔድኩበትን አላማ በመግለፅ እንዲተባበሩኝ ጠየኩ። በዚህ ቀንም በቤንች ማጂ ዞን ባህል እና ማስታወቂያ ቢሮ ለሦስቱም የወረዳ ጽ/ቤቶች ደብዳቤ ተጻፈልኝ።

በ 01/05/05 ዓ.ም በዞኑ ባህልና ማስታወቂያ ቢሮ የተፃፈልኝን ደብዳቤ በመያዝ የቤንች ብሔረሰብ በብዛት ይገኙበታል፤ ወደተባልኩበት ደቡብ ቤንች ወረዳ ከተማ ወደ ሆነችው ደብረ ወርቅ ሄድኩ። ከቦታው እንደደረስኩም የተፃፈልኝን ደብዳቤ ለወረዳው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በማቅረብ አስፈላጊውን ትብብር እንዲያደርጉልኝ ጠየኩ። የቢሮው ሐላፊም አላማዬን ከተረዳ በኋላ ለአስተርጓሚነት እና ለቪዲዮ ቀራጭነት ሁለት ሰዎች በመመደብ ከእኔ ጋር አብረው እንዲሰሩ አደረገ። የብሔረሰቡ ተወላጂ ስላልሆንኩ እና ቋንቋውን መናገርም ሆነ መስማት እናዲሁም መፃፍ ስለማልችል አስተርጓሚ መያዝ ግድ ነበር። እነዚህ አስተርጓሚዎቼም ቃለ የተዘጋጁ መጠይቆችን መሰረት በማድረግ የተመጡ መረጃ አቀባዮችን ቃለ መጠይቅ በማድረግ መረጃዎችን እንድሰበስብ አግዘውኛል። በተያያዘም በመቅረፀ ድምፅ የተያዙ መረጃዎችን ወደ

አማርኛ ተርጉመውልኛል፡፡ የተሰጡኝ ሰዎችም ከአሁን በፊት ከተለያዩ የውጭ ሀገር ሰዎች ጋር ሲሰሩ የቆዩ ስለነበሩ የምጠይቃቸውን በሙሉ በቀላሉ ያመላክቱኝ ነበር፡፡ ቀጠሮ በማስያዝ እና የለቅሶ ስርዓት ሲኖር እንዲደውሉልኝ በማድረግ ተለያየን፡፡

በ 03/05/05 ዓ.ም ደግሞ የሰሜን ቤንች ወረዳ ዋና ከተማ ወደሆነችው ጠመንጃጅ ሄድኩ፡፡ ልክ እንደ ደቡብ ቤንች ወረዳ ሁሉ ዓላማዬን በመግለፅ አስፈላጊውን ትብብር እንዲያደርጉልኝ ጠየኩ፡፡ የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሐላፊም ለመረጃው ቅርበት አላቸው ያለኝን ሰዎች አስተዋወቀኝ፡፡ ከእነሱም ጋር አድራሻ ተለዋውጠን የለቅሶ ስርዓት በሚኖርበት ጊዜ እንዲደውሉልኝ አደረኩ፡፡

እነዚህን ሁኔታዎች ካጠናቀኩ በኋላ በ 11/05/05 ዓ.ም ከሁለቱ ወረዳዎች (ሰሜን ቤንች እና ከደቡብ ቤንች) ሰው እንደሞተ ሰማሁ፡፡ የደቡብ ቤንች ወረዳ እኔ ካለሁበት (ሚዛን) ስለሚርቅ እና በስርዓቱ ላይ በሰዓቱ ስለማልደርስ ወደ ሰሜን ቤንች ወረዳ (ጋቸብ ቀበሌ) ከአስተርጓሚዬ ጋር ሔድኩ፡፡ ከቦታው እንደደረስንም በእድሜ የገፉ አዛውንት መሞታቸው ተነገረን፡፡ በአስተርጓሚዬ በኩል ቤት ውስጥ የሚደረገውን ስርዓት እንዳይ ብጠይቅም ባህሉ እንደሚከለክል ተነገረኝ፡፡

ከዚያም የሚጨፍሩ ሰዎችን በካሜራ ስቀርፅ፤ የሟች ዘመዶች በመቆጣት እንዳቆም ነገሩኝ፡፡ መቅረፅ የሚቻለውም ብር ለከፈለ ብቻ መሆኑንም አስረዱኝ፡፡ የጠየቁት ብርም ከእኔ አቅም ጋር ስለማይመጣጠን መቅረፁን ትቼ በምልከታ ለማጠናከር ሞከርኩ፡፡ በመቃብር ቦታውም መገኘት እንደማልችል ስለተነገረኝ ቀብረው እስኪመጡ ድረስ ከሌሎች የብሔረሰቡ አባላት ጋር ቆየሁ፡፡ ከቀብሩ በኋላም ያለውን መስተንግዶ ከአስተርጓሚዬ ጋር በመሆን አንድ ባንድ በማስታወሻዬ አሰፈርኩ፡፡ ከዚያም በለቅሶ ቤቱ ውስጥ የሚገኙ ሽማግሌዎችን የተመለከትኳቸው ጉዳዮች የተወሰኑትን እየጠየኩ አብሬ አደርኩ፡፡ በማግስቱ ጠዋት 4፡00 ተነስተን ወደ ሚዛን ተመለስን፡፡ በለቅሶ ክዋኔ ጊዜ የተመለከትኳቸውን መሰረት በማድረግ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ቀጠሮ ካስያዝኳቸው ሰዎች ጋር ቃለ መጠይቅ በማድረግ የተለያዩ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ቻልኩ፡፡

በ 20/05/05 ዓ.ም ጠዋት አማን ሆስፒታል አንድ ሰው መሞቱ ተነግሮኝ ሔድኩ፡፡ አስተርጓሚዬን ደወልኩለትና ተያይዘን አብረን እስከ ሟቹ ቤት ሄድን፡፡ ይህም ተፈጥሯዊ መቼቱን ተጠቅሜ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ጥሩ አጋጣሚ ነበር፡፡ ከመጀመሪያው የለቅሶ ክዋኔ ባገኘሁት ልምድ መሰረት ለመቅረፅ እንዳስፈቅድ ተገደድኩ፡፡ ነገር ግን አንድ የውጭ ዜጋ ከሁለት ወር በፊት ለሟች አባት 10,000 ብር ከፍሎ የሰርግ ስነ ስርዓት እንደቀረፀ እና እኔም ይህን ያህል ብር ካልከፈልኩ መቅረፅም ሆነ ፎቶ ማንሳት እንደማልችል ተነገረኝ፡፡ ነገር ግን ተማሪ

መሆኔን በአስተርጓሚዬ በኩል ተነግሮት ፎቶ ብቻ እንዳነሳ ተፈቀደልኝ፡፡ ቤት ውስጥ ያለውን ስርዓትም ለመመልከት ባህሉ እንደማይፈቅድልኝ ተነገረኝ፡፡ ሌሎች ተያያዥ ያላቸውን ክዋኔዎች ግን ዳር ቁሜ መመልከት ችያለሁ፡፡ በዚህ ቤት ሁለት ቀን አደርኩ፡፡

ከ 23/05/05 — 27/05/05 ዓ.ም በተለያዩ ቦታዎች በመዘዋወር እና ስለ ባህሉ ጥሩ ግንዛቤ አላቸው የተባልኳቸውን ሰዎች ቃለ መጠይቅ በማድረግ መረጃዎችን ሰበሰብኩ፡፡ መረጃ ስብሰባው በአንድ የመስክ ተሞክሮ ሊጠናቀቅ እንደማይችል በመገንዘብ ቀሪ የለቅሶ ዓይነቶች (ባለቃልቻ፣ የባላባትና ሚያንግ) መመልከት አስፈላጊ በመሆኑ እነዚህ የለቅሶ አይነቶች በሚኖሩበት ጊዜ እንዲደውሉልኝ ተነጋግሬ በ 28/05/05 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ ተመለስኩ፡፡

ሁለተኛው ዙር የመስክ ተሞክሮዬ ጉዞ የተጀመረው በ 09/06/05 ዓ.ም ነበር፡፡ ለመሄድ የተነሳሁበት ምክንያትም በደቡብ ቤንች ወረዳ አንድ ባላባት መሞቱ ተደውሎ ስለተነገረኝ ነበር፡፡ የባላባት ለቅሶ እስከ ሁለት እና ሶስት ወር እንደሚጨርስ ቀደም ሲል ከነበረኝ ተሞክሮ ስለተረዳሁ እንደምደርስ በማሰብ ሄድኩ፡፡ ከቦታው በ 12/06/05 ዓ.ም ደረስኩ፡፡ ነገር ግን በዚህ የለቅሶ አይነት የባላባትነት ዘር ያላቸው ሰዎች ሲሞቱ ወዲያውኑ ስለማይነገር የሟች ቤተሰቦች አልሰማንም፤ በማለት ፈቃደኛ እንዳልሆኑ ገለፁልኝ፡፡ አንዳንድ ሰዎች ግን እንደነገሩኝ ከወር በፊት ጠባቂዎቹ መካነ መቃብሩ ቦታ (መንከር) ውስጥ አስከሬኑን ይዘው እንደሄዱ ተነገረኝ፡፡ በዚህ ቦታ ሂዶ ማየት ከባድ እንደሆነ ስለተነገረኝ ለማየት እድሉን አላገኘሁም፡፡

ከአምስት ቀን በኋላ (17/06/05 ዓ.ም) የሟች ቤተሰቦች ዝግጅት እያዘጋጁ መሆኑን ሰምቼ ወደ ቦታው ሄድኩ፡፡ በሁለት ቀን ቆይታየም በአካባቢው ከሚገኙ ሽማግሌዎች ጋር ጥሩ ግንኙነት በመፍጠር የምፈልገውን መረጃ ለመሰብሰብ ቻልኩ፡፡

በመጨረሻም የባለቃልቻ የለቅሶ ስርዓት እንደማላገኝ ስለተነገረኝ ነገር ግን መስከረም 30/2005 ዓ.ም ደቡብ ቤንች ወረዳ በባህል እና ቱሪዝም ቢሮ የተቀረፀ ቪዲዮ ፊልም እንዳለ እና መመልከት እንደምችል ስለተነገረኝ ከፊልሙ ለእኔ ጥናት ይሆናሉ የምላቸውን ወደ ወረቀት ካሰፈርኩ በኋላ የተለያዩ ሰዎችን ቃለ መጠይቅ እና የተተኳሪ የቡድን ውይይት በማድረግ በቂ የሚባሉ መረጃዎችን ሰበሰብኩ፡፡ መረጃዎቼን በትክክል መጠናቀራቸውን ካረጋገጥኩ እና የትርጉም ስራዎች በትክክል ወደ አማርኛ መተርጎማቸውን በሌሎች ተጨማሪ ጋዜጠኞች ካረጋረጥኩ በኋላ 27/06/05 ዓ.ም ተነስቼ ወደ አዲስ አበባ መጣሁ፡፡

## 2. ክለሳ ድርሳን

በዚህ ምዕራፍ ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ስራዎች እና ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ ተቃኝተው ይቀርባሉ።

### 2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

የለቅሶ ስርዓትን በሚመለከት በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ በባችለር ዲግሪ ተመራቂዎች የተሰሩ በርከት ያሉ የማሟያ ጥናቶች አሉ። ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያነትም ከአምስት የማይበልጡ ጥናቶች ተካሂደዋል። ነገር ግን የቤንች ብሄረሰብን የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔን መሰረት በማድረግ የተጠኑ ጥናቶች እስካሁን አላገኘሁም። ይሁን እንጂ በቤንች ብሄረሰብ ላይ በሌሎች ርዕሰ ጉዳዮች ጥናቶች ተካሂደዋል። ከእነዚህም መካከል ተራመድ ጥላሁን (1992)፣ ማንያለው አባተ (1999) እና ምንታም ልንገርህ (2003) ያጠኗቸው ጥናቶች ይጠቀሳሉ።

ተራመድ ጥላሁን በ (1992) "የቤንች ተረት እና ምሳሌዎች ቅርፅና ይዘት ትንተና" በሚል ርዕስ አጥንቷል። የተራመድ ጥናት ትኩረት ተረቶችን እና ምሳሌዎችን ሰብስቦ ይዘታቸውንና ቅርፃቸውን ማሳየት ነው። በቅርፅ በኩልም የተሰበሰቡ ተረትና ምሳሌዎችን "ግጥማዊነት፣ በዝርው የቀረቡ እና ዘይቤያዊ ንግግሮች" ብሎ በመመደብ አጥንቷል። የተሰበሰቡት መረጃዎችም ከይዘት አንፃር "ስለቤተሰብ፣ በሴቶች ላይ የተነገሩ፣ በዝምድና ላይ የተነገሩ፣ በሞኝነት ላይ የተነገሩ፣ በችኩልነት ላይ የተነገሩ ፣ በስራ ክቡርነት እና በስንፍና ላይ የተነገሩ፣ በደሃ ላይ የተነገሩ፣ ምርቃት እና ሀቀኝነት" በማለት ከፋፍሎ አጥንቷል። መረጃዎችን በሙሉ የሰበሰበው በቃለ መጠይቅ ነው። ይዞት የተነሳውን የጥናት አላማም አሳክቷል። ትንታኔውም ሆነ መረጃዎችን ለመመደብ የተጠቀመው ዘዴ በተሰበሰቡት መረጃዎች ተመስርቶ ስለሆነ ተገቢነት አለው።

ማንያለው አባተ በ1999 ዓ.ም "የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮችና ማህበራዊ ፋይዳቸው" በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጥናት አቅርቧል። የእሱ ጥናት ትኩረትም የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮች የሚያሳዩትን ማህበራዊ ፋይዳ መግለፅ ነው።

ማንያለው በጥናቱ የሰበሰባቸውን ቃላዊ ዝርው ተረኮችን ከክዋኔ አውዳቸው፣ ከፈጠራነታቸው እንዲሁም ከትረካቸው ግብ አላማ አንፃር "ቤንችቶስ እና ኤሽሽ" በማለት በሁለት ይከፍላቸዋል።

አከፋፈሉም ብሔረሰቡ የሰጠውን አከፋፈል መሰረት ያደረገ ስለሆነ ተገቢነት ያለው እና ሳይንሳዊ አመዳደብን የተከተለ መሆኑን ከስራው መረዳት ይቻላል፡፡

በተያያዘም ማንያለው ቃላዊ ዝርው ተረኮቹ የሚተረኩበትን መቼት በመጥቀስ ለምን ለምን ማህበራዊ ግልጋሎት እንደሚውሉ በስራው ውስጥ ተንትኗል፡፡ በተለይም "ቤንችቶስ" የተባለው ዝርው ቃላዊ ተረክ የሚተረከው በቀን ሲሆን ተራኪዎቹም በሚተርኩበት ጊዜ የሚተርኩበትን ጉዳይ ከማን እንደሰሙ በመግለፅ እንደሚጀምሩ፤ "ኤሽሽ" የተሰኘው ዝርው ቃላዊ ተረክ ደግሞ ታሪኩ የፈጠራ ሆኖ ክዋኔውም የሚካሔደው በምሽት (ማታ) እንደሆነ ገልጿል፡፡ በታሪኩ ውስጥ የሚጠቀሱት ገፀባህሪያትም በአብዛኛው እንስሳት እንደሆኑ፤ ይህ የትረካ አይነት በአሁኑ ወቅት ብዙም እንደማይተረክ እና ትረካው እየተረሳ መምጣቱን በጥናቱ አሳይቷል፡፡ ለምን እንደማይተረክ እና በምን ምክንያት እየቀነሰ እንደመጣ አጥኚው የገለጸው ነገር የለም፡፡ ይህን ባለመግለፁም ጥናቱ ክፍተት እንዲኖረው አድርጓል፡፡

ማንያለው እነዚህን ተረኮች ማን እንደሚተረካቸው (ከከዋኖቻቸው አንፃር) ለማጥናት ችሏል፡፡ በአብዛኛው አዋቂዎች (ሽማግሌዎች) የተለያዩ አጋጣሚዎችን ተጠቅመው እንደሚከውኑ ጠቅሷል፡፡ ተረኮቹ ለማህበረሰቡ የሚሰጡትንም ማህበራዊ ፋይዳ ገልጿል፡፡ የተረኮቹ ፋይዳም ባህልን ጠብቆ ለትውልድ ለማስተላለፍ፣ የባህላዊና ማህበራዊ ተቋማትን እና እሴቶቻቸውን ጠቀሜታ ከፍ ለማድረግ፣ ለማስተማር፣ ለማዝናናት እና ታሪክን ለመቅረስ ወዘተ የመሳሰሉ ማህበራዊ ፋይዳዎችን እንደሚሰጡ፤ የተሰበሰቡ ተረኮችን ተንትኖ አሳይቷል፡፡

የማንያለው ጥናት ጥሩ የሚባል እና የፎክሎር የጥናት አቅጣጫዎች የተከተለ ነው፡፡ ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው የምናጠናበት ብሔረሰብ አንድ መሆን እና በተወሰነ መልኩ ደግሞ በቃለ መጠይቅ እና በምልከታ መታገዛችን ነው፡፡

ምንታምር ልንገርህ (2003) "የቤንች ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት" በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ሥነጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ አቅርባለች፡፡ የተመለከተቻቸውም "የቤንች ሀገረሰባዊ ሙዚቃ፣ የሰርግ ሙዚቃ፣የስራ ሙዚቃ፣ሃይማኖታዊ አውድ፣ ቃልቻ ዱብ፣ የቤንች ሐገረሰባዊ ዳንስ (ዶር) ፣ማህበረ ባህላዊ አውድ የሰርግ ዳንስ እና የየብ ዳንስ፣የቤንች ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት መከወኛ ቁሶች (የእጅ ዱብ ፣የትንፋሽ ዱብ እና የእግር የዱብ መሳሪያ)" ናቸው፡፡

ምንታምር ጥናቱ በተወሰነ መንገድ ስለለቅሶ መከወኛ ቁሶች ለመዳሰስ ሞክራለች። የለቅሶው ስርዓተ ክዋኔውን ቅደም ተከተል፣ ከእድሜ አንፃር ያለውን የለቅሶ ስርዓት፣ የሙሾ ግጥሞች እና ይዘታቸው፣ ከለቅሶው ጋር ተያይዘው የሚመጡ ፎክሎራዊ ትርጓሜዎች ወዘተ. ግን በጥናቱ አልተካተቱም። ስለዚህ ምንታምር ጠቅላላ የቤንች ብሔረሰብን ትውን ጥበባት ገፅታ ብቻ ለማሳየት ነው የሞከረችው። ሁለታችንም በአንድ ብሔረሰብ ላይ ተመስርተን ጥናት ለማድረግ መነሳታችን እና መረጃዎችን ለመሰብሰብ የተጠቀምንባቸው ዘዴዎች ያመሳስሉናል።

ቀጥሎ የምቃኘው በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ በመጀመሪያ ዲግሪ ተመራቂዎች እንዲሁም በሁለተኛ ዲግሪ ተመራቂዎች የቀረቡና ሙሉ በሙሉም ሆነ በከፊል ከኔ ጥናት ጋር የሚዛመዱትን ይሆናል። በመሆኑም ከ 1995 ዓ.ም ጀምሮ በመጀመሪያ ዲግሪ ተመራቂዎች የተሰሩትን ስድስት ጥናቶች እና በሁለተኛ ዲግሪ የተሰሩ ሶስት ጥናቶች በዚህ ክፍል ተቃኝተዋል። ሌሎች በሁለተኛ ዲግሪ ተመራቂዎች የተጠኑት (የበሪሁን መንግስቱ እና ማናየ እንግዳው) ስራዎች ግን በቤተመጻሕፍት ውስጥ ስላላገኘኋቸው ቅኝት አልተደረጉም።

የለቅሶን ጽንሰ ሀሳብ መሰረት አድርገው ከ1963 ዓ.ም ጀምሮ ጥናቶች ቢኖሩም ከዘመን ርቀት አንፃር፣ በዚህ ጥናት ቅኝት ቢደረጉ የሚያመጡት ፋይዳ አይታየኝም። በተጨማሪም እነዚህ ጥናቶች በሶስት የሁለተኛ ዲግሪ ተማሪዎች በተመሳሳይ መንገድ ቅኝት ተደርጎባቸዋል። ተማሪዎቹም ሞገስ ሚካኤል (2002)፣ ሕይወት አበሩ (2003) እና ዘላለም ፋንቱ (2004) ናቸው። በእነዚህ ጥናቶች ውስጥ ያልተካተቱትን እና በደንብ ቅኝት አልተደረገባቸውም ብዬ የመረጥኳቸውን ስራዎች ግን ቃኝቻለሁ።

ጥናታዊ ስራዎቹን በሶስት ንዑስ ክፍሎች መድቤ ነው የምቃኛቸው። ክፍሎቹም የለቅሶ ክዋኔውንና የለቅሶ ግጥሞችን በአንድ ላይ ያጠኑ፣ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔውን ብቻ ያጠኑ እና የለቅሶ ግጥሞችን ያጠኑ የሚሉት ናቸው። በዚህ ቅኝት የሚዳሰሱት ሥራዎች በተለያዩ ዓመታት የተሰሩ ስለሆኑ ሁሉንም ለየብቻ ቅኝት ካደረኩ በኋላ አነፃፅራለሁ። ለአካሄድ ያመች ዘንድም ከሩቅ ዘመን ወደ ቅርቡ ዘመን (1995 ወደ 2004 ዓ.ም) ቅደም ተከተሉን ጠብቄ አቅርቤያለሁ። በተመሳሳይ አመት የተሰሩ ስራዎችን ደግሞ በአጥኝዎቹ የስም ፊደል ቅደም ተከተል መሰረት ቃኝቻለሁ።

የለቅሶ ክዋኔውን እና የለቅሶ ቃል ግጥሞችን አያይዘው ካጠኑ የባችለር ዲግሪ ተመራቂዎች መካከል ወርቃየሁ አረጋ አንዷ ናት። ወርቃየሁ በ1995 ዓ.ም "የአዊ ህብረተሰብ ሴንቲ (የለቅሶ

ስርአት) እና የአወኚ ዚንዚምኚ (የሙሾ) ግጥሞች ይዘት ትንተና" በሚል ርዕስ ጥናት አቅርባለች፡፡ የጥናቱ አላማም የአውኚ የሙሾ (ዚንዚምኚ) ግጥሞችን ሰብስቦ ይዘታቸውን መተንተን የሚል ነው፡፡ መረጃዎች የተሰበሰቡትም በቃለ መጠይቅ እና በምልከታ መሆኑን ስራው ያሳያል፡፡ የአዊን ህብረተሰብ የለቅሶ ስርዓት (ሴንቲ) ከቀብር በፊት (ዴወፅዴስፍና)፣ የቀብር ሥርዓት (ዴወፅዊ) እና ከቀብር በኋላ (ዴወጽዴስ) በማለት ከፋፍላ አጥንታለች፡፡ የለቅሶ ስነ ስርዓቱ የተሳካ እንዲሆን በማድረግ ረገድ እድሮች የሚጫወቱትን ሚና ገልጻለች፡፡ ይህንንም በማድረጓ ከሌሎች መሰል አጥኝዎች ይለያታል፡፡ ይህም የጥናቷ ጠንካራ ጎን ነው፡፡

የሙሾ ግጥሞችን ለወንዶች (ማለትም አባት ሲሞት፣ ወንድም ሲሞት፣ ልጅ ሲሞት የሚገጠሙ ግጥሞች) እና ለሴቶች (እናት እና እህት ሲሞቱ) የሚገጠሙ ግጥሞችን አንዳንድ ምሳሌዎች በማካተት ገልፃለች፡፡ የተሰበሰቡ ግጥሞችን ግን አልተነተነችም፡፡ ትንተና ባለማድረጓም ከጥናቷ ርዕስ እና አላማ እንድትወጣ አድርጓታል፡፡ በዚህም የተነሳ የዓላማ እና የትንታኔ አለመመጣጠን ጎልቶ ይስተዋላል፡፡

አስቴር አንጀሎ በ1997 ዓ.ም "የጋሞ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት" በሚል ርዕስ ያጠናችው ጥናት አላማ የጋሞ ብሔረሰብን የለቅሶ ስርዓት ምን እንደሚመስል እና ከሌሎች ብሔረሰቦች ጋር ያለውን የባህል ዝምድና ማሳየት የሚል ነው፡፡ አስቴር የሙሾ ቃል ግጥሞችንም ለመተንተን ሞክራለች፡፡ ነገር ግን የሙሾ ቃል ግጥሞቹን እንደምትተነትን በአላማው ውስጥ አላካተተችም፡፡ የብሔረሰቡን የለቅሶ ስርአት "ከቀብር በፊት"፣ "በቀብር ጊዜ" እና "ከቀብር በኋላ" ብላ በመከፋፈል፤ የጋሞ ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓትን እና የግጥሞችን ይዘት በስድስት ንዑስ ክፍሎች መድባ አጥንታለች፡፡ እነሱም ወጣት ሲሞት፣ ጎልማሳ ሲሞት፣ አባት ሲሞት፣ እናት ስትሞት፣ ወንድም እና እህት ሲሞቱ የሚከናወኑ የለቅሶ ስርዓቶች እና የሚደረደሩ ግጥሞች የሚሉት ናቸው፡፡ መረጃዎችንም በቃለ መጠይቅ እና በምልከታ ዘዴዎች ታግዛ ሰብስባለች፡፡ በዚህም ከእኔ ጥናት ጋር በከፊል ያመሳስለናል፡፡

ጥናቱ ሶስት ክፍተቶች አሉት፡፡ የመጀመሪያው በአንድ የቀብር ስርዓት ብቻ ላይ ተመስርታ ካጠናች በኋላ የጋሞ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት ይህ ነው ብላ ድምዳሜ መስጠቷ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የለቅሶ ስርዓቱን በሚመለከት አንዳንድ ጉዳዮችን በመዘርዘር ይህ ጎጅ ነው፤ ይህ ደግሞ ጠቃሚ ነው፤ በማለት ውሳኔ መስጠቷ ነው፡፡ በፎክሎር ጥናት እንዲህ ያለ ውሳኔ መስጠት አይፈቀድም፡፡ ማንኛውም ማህበረሰብ ለሁሉም ነገር መነሻ ምክንያት ስላለው ጎጅ ወይም ጠቃሚ ብሎ መደምደም ተገቢነት የለውም፡፡ ሶስተኛው ክፍተት ደግሞ ርዕሱ ሰፊ

ከመሆኑ የተነሳ አልማ የተነሳችውን ጉዳይ መዘንጋቷ ነው። ከጥናቱ ዓላማ የምንረዳው የጋሞን ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት ካጠናች በኋላ ከሌሎች ብሔረሰቦች ጋር ያለውን የባህል ዝምድና ማሳየት የሚል ነው። ይህንን ግን በጥናቷ አላካተተችም።

ሽመልስ አክሊሉ በ1997 ዓ.ም "የቋሪት ወረዳ የለቅሶ ስነ ስርዓትና የለቅሶ ግጥም ይዘት ትንተና" በሚል ርዕስ አጥኝቷል። የጥናቱ ዋና ዓላማዎች "የወረዳውን የሙሾ ግጥሞች ተንትኖ መመልከት" እና "በቋሪት ወረዳ ውስጥ የሚገኘውን የለቅሶ ስርዓት ማሳየት" የሚሉት ናቸው። የሽመልስ ጥናት በአብዛኛው በ1995 ዓ.ም ወርቃየሁ አረጋ ካጠናችው ጥናት ጋር ይመሳሰላል።

የጥናቱ ክፍተት አውድ እና አጋጣሚውን ተጠቅሞ መረጃዎችን አለመሰብሰቡ ነው። ሙሉ በሙሉ መረጃዎችን ሰበሰብኩ ያለው በቃለ መጠይቅ ነው። ስለዚህ በቃለ መጠይቅ ብቻ ታግዞ ግጥሞችን በአውዳቸው ለመመደብ አስቸጋሪ እንዲሆን የሚያደርገው ይመስለኛል። ለአባት የተገጠመው የሙሾ ግጥም ለወንድም፣ እንዲሁም ለእናት የተገጠመው ደግሞ ለእህት ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም አጥኝው ተፈጥሯዊ መቼቱን ጠብቆ መረጃዎችን ለመሰብሰብ አልሞከረም።

ሌላው ፈለገህይወት ዘገዬ በ 1997 ዓ.ም "በባንጃ ሽኩዳድ ወረዳ የቀብር ሥነ ሥርዓትና የለቅሶ ግጥሞች ስብስብ ይዘት ትንተና" በሚል ርዕስ ያጠናው ነው። "የቀብር ሥነ ስርዓቶች፣ የሙሾ ግጥም ቅርፆች እና የሙሾ ግጥም ይዘት ትንተና" የሚሉ ጉዳዮችንም በማንሳት በተለያዩ ሰዎች የተሰሩ ሥራዎችን በማጣቀስ አያይዞ አቅርቧል።

መረጃዎችን የሰበሰበው የለቅሶ ክዋኔውን በመመልከት፣ በቴፕ ሪከርደር በመቅረጽ፣ ፎቶ ግራፍ በማንሳትና ቃለ መጠይቅ በማድረግ ነው። ፈለገህይወት ቃል ግጥሞችን ብቻ ሳይሆን ክዋኔውንም በተወሰነ መልኩ ገልጿል። በተለያዩ መንገዶች የሰበሰበውን የለቅሶ ግጥሞች በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች መድቧል። እነሱም "ወንድ ሲሞት የሚገጠሙ" (ለአባትና ለወንድም) እና "ሴት ስትሞት የሚገጠሙ" (ለእናትና ለእህት) የሚሉት ናቸው። አከፋፈሉ ተገቢነት አለው። ምክንያቱም ግጥሞቹን የሰበሰበው አጋጣሚውን (ለቅሶውን) በመጠቀም ስለሆነ ከሟቹ (ቿ) ማንነት ጋር ቃል ግጥሞቹ ያላቸውን ግንኙነት አሳይቷል። ትንታኔውም ጥሩ የሚባል፤ የለቅሶ ክዋኔውን እና አውዱን መሰረት ያደረገ ነው። በጥናቱም የደረሰው ድምዳሜ ባጠናው አካባቢ የለቅሶ ሥነ ስርዓት ሲከወን ለክዋኔው ማድመቂያ ሰፊ ጊዜና ቦታ ተሰጥቶ የሚከወነው የፉከራ ግጥሞች መሆናቸውን ተገንዝቧል። እንደ ክፍተት የሚታየው ደግሞ እነዚህን የፉከራ ግጥሞች በጥናቱ ውስጥ አለማካተቱ ነው።

ሞገስ ሚካኤል በ 2002 ዓ.ም "በላይ አርማጭሆ ወረዳ የማዕርግ የቀብር ስነ ስርአት፣ በስርአቱ ላይ የሚካሄድ ቀረርቶ፣ ፉከራና ክዋኔው" በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ አቅርቧል። የጥናቱ ዋና ትኩረትም በላይ አርማጭሆ ወረዳ የማዕርግ የቀብር ስነ ስርዓት እና በስነ ስርዓቱ ላይ የሚካሄዱ ቀረርቶ፣ ፉከራና ክዋኔውን የሚመለከት ነው። መረጃዎችንም በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ አማካይነት ሰብስቧል። ጥናቱ የቀረበበት ወይም የተተነተነበት መንገድም በገለፃ ነው። በመረጃ አሰባበቡ በከፊል፤ በአተናተኑ ደግሞ ሙሉ በሙሉ ከእኔ ጥናት ጋር ይመሳሰላል።

በንድፈ ሃሳባዊ ዳራውም ስለ ቀረርቶ፣ ፉከራ፣ ክዋኔና የቀብር ስነ ስርዓት ምንነት ከተለያዩ ምሁራን ሃሳቦች ጋር በማዛመድ በስፋት ዘግቧል። በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተገኙ መረጃዎችንም የቅድመ ሞት ዝግጅት፣ ጊዜ ሞት እና ከቀብር በኋላ የሚከናወኑ ሥርዓቶች በማለት ከፍሏል። የለቅሶውን ስርዓተ ክዋኔ መግለጽ ብቻ ሳይሆን ከክዋኔው ጋር ተያይዘው የሚመጡ ፎክሎራዊ ጉዳዮችንም ቃለ መጠይቅ በማድረግ ለመተርጎም ጥረት አድርጓል።

የሞገስ ስራ ጠንካራ ጎኑ የማህበረሰቡን እውቀት ይዞ ክዋኔውን ለመተርጎም ያደረገው ጥረት ነው። እንደ ክፍተት የሚታየው ግን ጥናቱ ሊመልሳቸው የሚችሉ የምርምር ጥያቄዎች አለመኖሩ እና ምልከታን (የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴን) ባግባቡ አለመጠቀሙ ናቸው። ሞገስ በአብዛኛው ምልከታ ሳይሆን ያደረገው ዶክመንተሪ ፊልሞችን (በ1996 እና 2002 ዓ.ም አጥኚው ሳይኖር የተቀረፁ) ስራዎችን መሰረት ማድረጉን ገልጿል። ይህ ደግሞ ከምልከታ ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም።

የሞገስን ስራ ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው የለቅሶ ክዋኔውን እና እሱ በተወሰነ መልኩ ቀረርቶ እና ፉከራን ማየቱ ነው። የጥናቱ ወሰን የማዕርግ ጀግና የለቅሶ ስርዓት ላይ ያተኮረ መሆኑ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴው ቃለ መጠይቅ እና ምልከታ ብቻ መሆኑ በከፊል ሲያመሳስለን፤ የምናጠናው ቦታ ወይም ማህበረሰብ መለያየት ሁለታችንም ይለያየናል።

ሌላው በሁለተኛነት በዚህ ክፍል የሚቃኙት የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔን ብቻ ያጠኑት ናቸው። ከእነዚህ መካከል ቀዳሚው ጌታመሳይ ግዛው ነው። ጌታመሳይ በ 2002 ዓ.ም ያቀረበው የባችለር ዲግሪ ጥናት "የሽናሻ ብሔረሰብ የቀብር ስርዓተ ክዋኔ ከፎክሎር ዘውጎች አንፃር" የሚል ነው። የብሔረሰቡን የቀብር ስርዓተ ክዋኔ "ከቀብር በፊት፣ የቀብር ስርዓት ክዋኔ፣ ድህረ ቀብር ስርዓት

ክዋኔ፣ የደም ማጥራት ስርዓተ ክዋኔ፣ የተገኮር ስርዓተ ክዋኔና የውርስ ስርዓት" ብሎ በመክፈል አጥንቷል።

የጥናቱ ክፍተት ከለቅሶ ክዋኔው ጋር ተያይዘው የሚመጡ የሙሾ ግጥሞችን አለማየቱ ነው። ፎክሎራዊ ገፅታዎችን እመለከታለሁ፤ ካለ የሙሾ ግጥሞችም የዚህ ገፅታ አንድ አካል ስለሆኑ መታየት ነበረባቸው። በተጨማሪም የደም ማጥራት፣ የተገኮር እና የውርስ የሚሉት ስርዓቶች እራሳቸውን ችለው ሊጠኑ የሚገባቸው ርዕሶች ሆነው እያለ ቀብር በሚለው ስር አካቶ ማጥናቱ አላማውን እንዲስት እና ግብ እንዳይመታ አድርጎታል። መረጃዎችን በምን ዘዴ ተጠቅሞ እንደሰበሰበም የገለፀው ነገር የለም።

ሁለተኛው ጥናት ሕይወት አበሩ በ 2003 ዓ.ም "የመኤኒት ብሄረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስነ ስርዓት ክዋኔ" በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ያቀረበችው ነው። የጥናታዊ ጽሁፉ ትኩረት በመኤኒት ብሄረሰቡ የለቅሶ ስርዓት ላይ ገላጭ ትንተና በማድረግ የለቅሶ ስርዓቱን ማሳየት ነው። መረጃዎችንም በቃለ መጠይቅ፣ በምልከታ እና በቡድን ውይይት ታግዛ ሰብስባለች።

ሕይወት በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተገኙ መረጃዎችን "የመኤኒት ብሄረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት አከዋወን" በሚል ርዕስ ስር ተንትናለች። በትንታኔዋም ከዕድሜ አንጻር "ከህፃንነት እስከ አቅመ አዳም (ሄዋን) ለደረሱ እና ለዕድሜ ባለፀጋዎች የሚደረጉ፣ ለባለቃልቻዎች (ኔሬይ) እና ለጎሳ መሪዎች (ኮሙሩት) ቅድመ ሞት፣ ጊዜ ሞት እና ድህረ ቀብር" ክዋኔዎች ምን እንደሚመስሉ ገልፃለች። አያይዛም የመኤኒት ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት መከወን፤ "የብሔረሰቡ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ታሪክን ከማቆየት፣ ባህላዊና ማህበራዊ ተቋማትን ከማስጠበቅና የማህበረሰቡን አመለካከትና እምነት ከመግለጽ" አንፃር ያለውን ፋይዳ አጥንታለች።

የሕይወት ጥናት ጠንካራ ጎን ሁሉንም የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተጠቅማ በቂ የሚባል መረጃዎችን መሰብሰቧ እና መተንተኗ ነው። የለቅሶ ክዋኔ መኖር ለማህበረሰቡ የሚሰጠውን ማህበራዊ ፋይዳ በዝርዝር ማጥናቷ ደግሞ ይበልጥ ስራዋን ጠንካራ አድርጎታል። የመኤኒት ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት ሲያከናውን የለቅሶ ግጥሞችንም እንደሚጠቀም ገልፃለች። ነገር ግን አጥኝዋ የመኤኒት ብሄረሰብን የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ አጠናሁ ካለች፤ የክዋኔው አንድ አካል የሆነውን የለቅሶ ቃል ግጥሞች አያይዛ ማጥናት ነበረባት። ይህን ባለማድረጓም ከእኔ ጥናት ጋር እንለያያለን።

ከሕይወት አበሩ በመቀጠል እና የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔውን ብቻ ካጠኑት ሌላው ዘላለም ፋንቱ ነው። ዘላለም በ 2004 ዓ.ም "የለቅሶ ሥነ-ሥርዓት ክዋኔ በበና ፀማይ ወረዳ" በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጥናት አቅርቧል። የጥናቱ ዓላማም በበና ፀማይ ወረዳ በበና ብሄረሰብ ያለውን የለቅሶ ስነ ስርዓት ክዋኔና ትርጉም መግለጽ ነው። ቃለ መጠይቅ፣ ምልከታ እና የቡድን ውይይትን ተጠቅሞ መረጃዎችን በመሰብሰቡ ከሕይወት አበሩም ሆነ ከኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል። የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝትም በአብዛኛው ከሕይወት አበሩ ጥናት እና ከሞገስ ሚካኤል ጥናት ጋር ተዛማጅነት አለው። ተዛምዶውም በሁለት መልኩ መመልከት ይቻላል። የመጀመሪያው ቅኝት ያደረጋቸው የመጀመሪያ ዲግሪ ጥናቶች አንድ መሆን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ቅኝት ለማድረግ የተመረጡት መስፈርቶች መመሳሰል ነው።

በትንታኔው ክፍልም "የለቅሶ ስነ ስርዓት ክዋኔ በበና ብሄረሰብ" በሚል ርዕስ በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የሰበሰባቸውን መረጃዎች "የቅድመ ሞት ዝግጅት፣ የጊዜ ሞት ዝግጅት፣ የድህረ ቀብር ክዋኔዎች እና የቀጠሮ ለቅሶ" በማለት ከፋፍሎ ተንትኗል። የቅድመ ሞት ዝግጅት በሚለው፤ ማህበረሰቡ ሞት መቅረቡን ማረጋገጫ ብልሃቶች (ኑዛዜ፣ ለለቅሶው ማከናወኛ እና ማስኬጃ የሚደረጉ ዝግጅቶች) የሚሏቸውን፤ ጊዜ ሞት በሚለው አስከሬኑን ይዘው ብሄረሰቡ ወደ ቀብር የሚያደርጉትን ጉዞ እና በቀብር ወቅት የሚደረጉ ክንውኖችን ስዕላዊ በሆነ መንገድ ገልጿል።

በማጠቃለያው እና በይሁንታው ክፍልም እያንዳንዱ የባህል ዘርፍ የራሱ የሆነ ቅርጽ፣ መልዕክት እና አገልግሎት እንዳለው፤ የለቅሶ ስነ ስርዓትም በውስጡ የሚያካትታቸው የቀብር ስነ ስርዓት እና የአቀባበር ሁኔታ፣ የማስተዛዘኛ እና የሀዘን መግለጫ መንገዶች የየራሳቸው ጥቅም እና አገልግሎት እንዳላቸው፤ በመጥቀስ አጠቃሏል። በጥናቱ ጊዜ ስላጋጠሙት ችግሮችም አጥኝው የይሁንታ ሀሳብ ሰንዝሮ አልፏል።

የዘላለም ጥናት ክፍተት የአንድን ጎልማሳ የቀብር ስነ ስርዓት ክዋኔ ብቻ በመመልከት የበና ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት ይህ ነው፤ ብሎ መደምደሙ ነው። ጥናቱ የሚያመለክተው ስለ አጠቃላይ ብሄረሰቡ ሳይሆን ከብሄረሰቡ አባል ስለሆነው ስለ አንድ ወጣት ነው። የብሄረሰቡ ሌሎች አባላት (እናት፣ አባት፣ ህፃናት፣ የአካባቢ አስተዳዳሪዎች ወዘተ.) ሲሞቱ የሚደረገውን ስርዓት ምን እንደሚመስል የገለፀው ነገር የለም። ሌላው የአጥኝው ድክመት የሙሾ ቃል ግጥሞችን አለማየቱ ነው። ለዚህም ምክንያቱ በቂ ባይሆንም የቋንቋ ችግር እንደሆነ ገልጿል።

ስለዚህ ሙሉውን ክዋኔ አይቷል ለማለት አያስደፍርም፡፡ የሙሾ ግጥሞችንም ባለማካተቱ ከሕይወት አበሩ ጥናት ጋር ያመሳስላቸዋል፡፡ ባጭሩ ከዘላለም ጥናት ጋር የኔን ጥናት የሚያመሳስለው ለቅሶ ስርዓት ላይ መሆኑ እና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴያችን ተመሳሳይ መሆኑ ነው፡፡

የለቅሶ ቃል ግጥሙን ብቻ ካጠኑት መካከል አቡበከር ሀሰን አንዱ ነው፡፡ አቡበከር በ1998 ዓ.ም "የሺናሻ ብሔረሰብ የሐዘንና የተዝካር ስርአት ክዋኔ" በሚል ርዕስ የባችለር ዲግሪ ማሟያ ጥናት አቅርቧል፡፡ በሺናሻ ብሔረሰብ ሰው ሲሞት ከቀብር በፊት፣ በቀብር ጊዜና ከቀብር በኋላ የሚከናወኑ ስርዓቶች ምን ምን እንደሆኑ፣ የፍትሃት (የሻሮ) እና የተዝካር ስርዓታቸው ምን እንደሚመስል በዝርዝር ግልጿል፡፡ ለትንታኔ ያመቸው ዘንድም ወጣት ሲሞት፣ ጎልማሳ ሲሞት፣ አዛውንት (ባልቴት) ሲሞቱ እና ጀግና ሲሞት የሚከናወኑ የለቅሶ ስርዓቶችን ከፋፍሎ አቅርቧል፡፡ በሙሾ ግጥሞች ላይም የይዘት ትንተና አድርጓል፡፡

የአቡበከር ጥናት ክፍተት ይዞት ከተነሳው ርዕስ በተጨማሪ ሌሎች ርዕስ ጉዳዮችን ማካተቱ ነው፡፡ ለምሳሌ፡ የተዝካር ስርዓተ ክዋኔን መመልከት ይቻላል፡፡ ተዝካር ከለቅሶ ውጭ የራሱ የሆነ ክዋኔ አለው፡፡ ስለዚህ ለብቻው ሊጠና የሚችል ርዕስ ነው ማለት ይቻላል፡፡ መረጃዎችንም የሰበሰበው በቃለ መጠይቅ ነው፡፡ በቃለ መጠይቅ ብቻ ተጠቅሞ ስርዓቱን ለመክፈል እና ቃል ግጥሞቹን ለመመደብ ያስቸግራል፡፡ ምክንያቱም ግጥሞቹን ለመክፈልም ሆነ በይዘታቸው ለመመደብ በአካል በተፈጥሯዊ መቼቱ መገኘትን ስለሚጠይቅ ነው፡፡ ይህን ባለማድረጉ ደግሞ ጥናቱ ክፍተት እንዲኖረው ሆኗል፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ በአጭሩ የቃኘኋቸው ጥናቶች ከኔ ጥናት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገዶች ግንኙነት አላቸው፡፡ አንዳንዶቹ እንደ (ወርቃየሁ፣ፈለገህይወት፣ሞገስ፣ ሽመልስ ወዘተ.) የለቅሶ ክዋኔውን እና ግጥሞችን በማጥናታቸው ስንመሳሰል፤ ጥናት በሚያደርጉበት ብሔረሰብ እና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ደግሞ በከፊል እንለያያለን፡፡ ሌሎቹ ደግሞ (ሕይወት አበሩ እና ዘላለም ፋንቱ) የለቅሶ ክዋኔውን ብቻ በማጥናታቸው ከኔ ጥናት ይለያሉ፡፡ ምክንያቱም የኔ ጥናት የለቅሶ ግጥሞችንም ስለሚያካትት ነው፡፡ በመጨረሻ ደግሞ የለቅሶ ግጥሞችን ብቻ መሰረት በማድረግ ካጠኑት አጥኝዎች (አቡበከር) ጋር በከፊል በጥናቱ ዘዴ እና በርዕስ ስንመሳሰል ክዋኔውን አያይዤ በማጥናቴ ደግሞ ይለያየናል፡፡

## 2.2 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

ይህ ክፍል ሞት/ለቅሶ፣ ክዋኔ፣ የለቅሶ/ሙሾ ግጥሞች፣ቁሳዊ ባህል ወዘተ. የመሳሰሉት ጉዳዮች ከተለያዩ ምሁራን ሀሳቦች ጋር ተያይዘው የሚቀርቡበት ነው፡፡

### 2.2.1 ሞት

ሞት የተለያዩ ብያኔዎች አሉት፡፡ ሞትን በመበየን ከሚጠቀሱት መካከል ሀይማኖታዊ ተቋማት ይገኛሉ፡፡ በክርስትና ሀይማኖት ሞትን በሁለት ከፍለው ያዩታል፡፡ የመጀመሪያው ስጋዊ ሞት ነው፡፡ ስጋዊ ሞት አካልን ወይም ስጋን በመጉዳት እምነቱ ለሚፈልገው የነፍስ ልምላሜ መዘጋጀት ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የነፍስ ሞት ነው፡፡ የነፍስ ሞት ሀይማኖቱ አታድርግ ብሎ ከሚያዘው ህግ ፈፅሞ መገኘት ነው፡፡ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ባዘጋጀው *የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት* የሞት እሳቤ የሚከተለውን ሃሳብ ይይዛል፡፡ "ሞት የነፍስና የስጋ መለየት ወይም ህይወት ማጣት፤ ... ሰው በስጋ ሲሞት ነፍሱ ከስጋው ከተለየ በኂላ ወደ እግዚያብሔር ይመለሳል፡፡ ከሞት በኂላ ትንሳኤ ስላለ ሞት እንቅልፍ በሚል ቃል ተገልጿል፡፡" (1992፣62-3)፡፡ ከዚህ ሀሳብ እንደምንረዳው ሞት ጊዜያዊ እረፍት ወይም እንቅልፍ ተብሎ እንደተገለፀ እና ወደ ሌላኛው ዓለም መሸጋገሪያ እንደሆነ ነው፡፡

በ *World Book of Encyclopedia (1959, 241)* ሞት "*For many people, a funeral symbolizes a passage from one life to another, rather than the end of a person's existence. Such a ceremony, which is associated with the completion of one phase of life and the beginning of another*" በሚል ብያኔ ቀርቧል፡፡ ከዚህ ሀሳብ እንደምንረዳው ሞት ከአንዱ አለም ወደ ሌላ አለም መሸጋገሪያ ተደርጎ እንደሚወሰድ ነው፡፡

እንደ Lovell (1997, 30) ገለፃ ህይወት ያለው ነገር በመጀመሪያ ይወለዳል፤ ያድጋል፤ በመጨረሻም ይሞታል፡፡ የህይወት መጀመሪያ መወለድ እንደመሆኑ መጠን ወደ ሌላ አለም በሞት በመነጠል ከተጓዙ በኂላ ህይወት የሚጀመረው በሞት ነው፡፡ ሞት እና ውልደት አንዱ በአንዱ ላይ እየተተካኩ የሚሄዱና የሚጓዙ ነገር ግን የተለያዩ ክስተቶች ናቸው፡፡ ሞት በማይታወቀው ዓለም የህይወት መጀመሪያ ነው፤ በማለት ይገልፁታል፡፡

ሞት የህይወት ፍፃሜ ይሁን ወይም ወደ ሌላ ዓለም መሸጋገሪያ፤ በሚከሰትበት ጊዜ አብሮት የሚመጣው ለቅሶ ነው፡፡ በ*አማርኛ መዝገበ ቃላት* (1993፣17) "ለቅሶ" የሚለው ቃል "ሃዘን፤

ሙሾ፣ ዋይ ዋይታ፣ መጮህ፣ ማንባት፤ የእንባ መመንጨት፣ መውረድ፣ መፍሰስ" የሚል አቻዊ ፍቺ ተሰጥቶት እናገኛለን። በመሆኑም ሞት ሲከሰት ማልቀስ ይኖራል። እንደማህበረሰቡ ሁኔታ ማልቀስ ሊለያይ ይችላል። በአንዳንድ ማህበረሰቦች ሞት ሲከሰት መጨፈር፣ መዝፈን፣ ወዘተ. ሊኖር ይችላል። የተለያዩ ማህበረሰቦች ሰው ሲሞት በተለያዩ መንገዶች ስርዓተ ክዋኔውን ፈፅመው ሟችን ይሸኛሉ። ከዚህ ጋር በተያያዘ ዘሪሁን (1992፣22-23) "በአንዱ የለቅሶ ስነስርአት ሙሾ እየተደረደረ ደረት ይደለቃል÷ ይዘለላል። በሌላው ደግሞ የሟች የቅርብ ዘመዶች ፊታቸውን ይቧጥጣሉ÷ ፀጉራቸውን ይነጫሉ። በቀረው ደግሞ ከበሮ ይዞ በመጨፈር የልቅሶ ክዋኔ ይደረጋል። በሆታና በድልቂያ ሙታቸውን የሚሰናበቱም አሉ" በማለት ይገልፁታል።

የዘሪሁን ሀሳብ የአንዱ ማህበረሰብ ለቅሶ ከሌላው ማህበረሰብ ለቅሶ መለያየቱን ያሳያል። የሰዎቹ የለቅሶ ስርዓት መግለጫዎች እንዲሁ ይለያያል። አንዳንዱ ለሌላው ደስታ እንጅ ሀዘን በማይመስል መልኩ ከበሮ በመያዝ ይጨፍራል፤ ይዘፍናል። ሌላው ደግሞ ፀጉርን በመላጨት፤ ጥቁር ልብስ በመልበስ፤ ነጭ ክር በማሰር፤ ባዶ እግርን በመሄድ፤ አካልን በመጉዳት፤ ወዘተ. የመሳሰሉትን ድርጊቶች በመፈፀም ለሟች ያለውን ጥልቅ ሀዘን ይገልፃል። እነዚህ ድርጊቶችም እንደየማህበረሰቡ የተለየ መነሻ ምክንያት እና አስተሳሰብ አላቸው። በፎክሎር ምርምር ጊዜም ትኩረት ከሚሰጥባቸው ጉዳዮች የሚመደቡ ናቸው።

በተያያዘም የለቅሶ ክዋኔ እንደየማህበረሰቡ ባህል እና አስተሳሰብ ፆታን መሰረት አድርጎ ሊለያይ ይችላል። Hallam (1997,122-3) ማህበረሰቡ ፆታን ለስራ ክፍፍል መሰረት እንዳደረገው ሁሉ በለቅሶ ላይም ተፅዕኖ አሳድሯል፤ ይላሉ። ማህበረሰቡ የሴቶች እና የወንዶች የስራ ክፍፍል ብሎ እንዳስቀመጠው በለቅሶ ጊዜም ክዋኔውም ሆነ የአቀባበሩ ሁኔታ እንዲለያይ አድርጎታል። በአብዛኛው ማህበረሰብ ዘንድ ሴቶች የማይችሉ፣ ዝቅተኛ፣ ሀጢያተኛ ወዘተ ተደርገው ይታሰባሉ። በተቃራኒው ወንዶች ደግሞ የመሪነት ሚና እንዳላቸው ተደርገው ይቆጠራሉ። ይህ ተፅዕኖም በማህበራዊ ጉዳዮች (*social practice*) ላይ ጎልቶ ይስተዋላል።

አያይዘውም Hallam (1997,123) ‹Kunzle›ን ጠቅሰው ሲገልፁ በተለይ ወደ 16ኛው ክፍለ ዘመን ስንመለስ ሴት የመሆን ጉዳይ እንደ ልጅ፣ ቤት ጠባቂ፣ መወሰን የማትችል፣የሞት መንስኤ (dying)፣ ስራዋ ልጅ መውለድ ብቻ እንደሆነች አድርገው የመመልከት አዝማሚያ እንደነበረ ይጠቅሳሉ። ይህም በመታሰቡ የለቅሷቸው ስርዓት እንደሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች (ወንዶች) አይደምቅም። ይህንን ያመጣው ደግሞ ባህሉ እንደሆነ ይገልፃሉ።

ይህን ከላይ የተጠቀሰውን ሀሳብ *Neil Small (1997, 216)* "death is experienced not only in various cultures but also by men and women" በማለት ያጠናክሩታል። ይህም ሞት በተለያየ ባህል ውስጥ የተለያየ እሳቤ ቢኖረውም በአንድ ባህል ውስጥም ወንድ እና ሴት ብሎ በመከፋፈል ሊለያዩት እንደሚችሉ የሚያሳይ ነው።

የሴቶችን ሞት ዝቅ አድርጎ መመልከት እና የወንዶችን ደግሞ አጋኖ የመመልከት ሂደት ሲኖር በለቅሶ ጊዜ የሚኖረውን ስርዓትም እንዲለያይ ያደርገዋል። ይህም ማለት ሴቶች ሲሞቱ የሚዘጋጀው ዝግጁት ወንዶች በሚሞቱበት ጊዜ ከሚዘጋጀው ዝግጁት እንዲያንስ ይሆናል። ከፍ ሲል እንደገለፅኩት ይህም መነሻው እያንዳንዱ ማህበረሰብ በባህሉ (ወንድ/ሴት) ለሚለው የሰጠው ትርጉም ነው።

ሰው ሲሞት ከላይ እንደተጠቀሰው የራሱ የሆነ ክዋኔ ወይም ዝግጅት አለው። ዝግጅቱ የሚጀምረውም ታማሚው የማይድን መሆኑ ከታወቀበት ሰዓት ጀምሮ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ Cohen *(1996, 5)* የተባሉት የማህበራዊ ሳይንስ ተመራማሪ ሰው መሞቱ ከተሰማ ጀምሮ የሚኖረውን ድርጊት እንደሚከተለው ይገልፁታል።

> *As the death is announced, family, friends and neighbors draw together. People express grief: they weep, wail, scream, sing dirges, beat the breast, tear the hair, or other-wise mutilate themselves. The closest kin effect changes in costume. They wear white, black or red, or paint their bodies; they rend their clothes; they cover their bodies with ashes or dirt; they cut their hair, or let it grew, altering their normal appearance.*

አንድ ሰው መሞቱ ከተሰማ ጀምሮ ቤተሰብ፣ ጓደኛ፣ ጎረቤት አንድ ላይ በመሆን ለሟቹ የተሰማቸውን ሀዘን በተለያዩ ድርጊቶች ይገልፃሉ። በለቅሶ፣ በመዝፈን፣በመጮህ፣ ሙሾ በመደርደር፣ አካልን በመጉዳት፣ ፀጉርን በመላጨት፣ ጥቁር፣ ነጭ ወይም ቀይ ልብሶችን በመልበስ፣ አካላቸውን በቀለም በማስጌጥ፣ ሰውነታቸውን አመድ ወይም አቧራ በመቀባት ወዘተ. ሀዘናቸውን ይገልፃሉ። ይህ ሁሉ ግን እንደ ማህበረሰቡ እና ባህሉ ይለያያል።

ሰው እንደሞተ የለቅሶ ስርዓቱ ይጀምራል። ከፍ ሲል እንደገለፅኩት እንደየማህበረሰቡ ቢለያይም። Cohen (1996, 2) የሞትን ስርዓተ ክዋኔ በተመለከተ አንድ ሰው እንደሞተ ወዲያውኑ ለሬሳው ወይም ለሟቹ የሚደረጉ ክዋኔዎችን እንደሚከተለው ይገልፁታል።

> *...treatments of the body, disposal of the remains, and the behavior of close kin and others for a specified period of mourning are spelled out by society. The body*

*may be washed, anointed, shaved, combed, painted or perfumed. It is left naked or dressed, covered with a shroud, and sometimes adorned with jewelry. The mouth, nose, vagina, vagina and rectum may be stopped up, perhaps to prevent evil spirits from invading the body.*

ከላይ ከተጠቀሰው ሀሳብ እንደምንረዳው የሞት ስርዓተ ክዋኔ የሚጀምረው ሟች መተንፈስ ካቆመበት ጀምሮ እንደሆነ ነው፡፡ የሟችን አካል እንዳይበላሽ መጠበቅ፣ አስከሬኑን ማጠብ፣ ማድረቅ፣ ሽቶ መቀባት፣ ግንዘት፣ ማጠን፣ አፍን፣ ጆሮን፣ አፍንጫን ወዘተ የመድፈን ስርዓት ይደረጋል፡፡ ይህ ሁሉ ለምን እንደሚደረግ ደግሞ ማህበረሰቡን መሰረት በማድረግ መመርመር እንደሚያስፈልግ አያይዘው ይገልፃሉ፡፡

በመቀጠል ደግሞ ጥናቱን ለማጥናት የምገለገልባቸውን፤ እንዲሁም ለመተንተኛነት በማዕቀፍ የመረጥኳቸውን እና ከክዋኔ ንድፈ ሀሳብ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ነጥቦች እገልፃለሁ፡፡

### 2.2.2 ክዋኔ

የፎክሎር ባህሪያት ከሆኑት ክዋኔ ዋነኛው እና መሰረታዊው ነው፡፡ ክዋኔ በስነቃል ጥናት ውስጥ በተለይ ከተግባቦት ሁነት ጋር የተያያዘ እና ከበርካታ ጉዳዮች ጋር የተሳሰረ እሳቤ ነው፡፡ ክዋኔ ብዙውን ጊዜ ከተውኔት ጋር የተቆራኘ ነገር ግን በሁሉም የሰው ልጅ ተግባራት፣ ድርጊቶች እና ባህል ውስጥ የሚከሰት መሰረታዊና ቁልፍ ጉዳይ እንደሆነ Turner (1982, 107) ይገልፃሉ፡፡

ስለክዋኔ ንድፈ ሀሳብ የተለያዩ የመስኩ ምሁራን የየራሳቸውን ብያኔ ሰጥተዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል Bauman "*the term 'performance' has been used to a dual sense of artistic action-the doing of folklore an artistic event-the performance situation, involving performer, art form, audience, and setting*" (1977,4) በማለት ይገልፁታል፡፡ እንደ Bauman አገላለፅ ክዋኔ የሚለው ቃል ጥበባዊ ድርጊት ሆኖ የክዋኔውን ሁኔታ፣ በክዋኔው የሚሳተፉትን ከዋኞች፣ ጥበቡን፣ ታዳሚውን እና መቼቱን በአንድ ላይ የያዘ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

በተያያዘም *Sims* እና *Stephens "...performances have clear settings and recognizable structures that indicate to participants that the performance is taking place" (2005, 128)* በማለት ይገልፃሉ፡፡ ክዋኔው የሚካሄድበት የታወቀ መቼት እና የራሱ የሆነ የክዋኔ ቅደም ተከተላዊ መዋቅር እንዳለው ከገለፃው እንረዳለን፡፡ ይህም እንደ ፎክሎሩ አይነት እና እንደየማህበረሰቡ ሁኔታ ሊለያይ ይችላል፡፡ ለምሳሌ፡- የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ በአብዛኛው

በቤተክርስቲያን ወይም ለቀብር አላማ ተብሎ በተከለለ ቦታ፣ የፀሎት ስርዓት ክዋኔ በቤተ ፀሎት ወዘተ. በተለየና ሁሉም በሚያውቀው ቦታ ይከወናሉ፡፡

Finnegan (1992, 87) በበኩላቸው ክዋኔ ክዋኔው የሚካሄድበትን ቦታና ጊዜ፣ ክዋኔው የተዘጋጀበትን ምክንያትና ጉዳይ፣ በክዋኔው ውስጥ የሚሳተፉ ሰዎችንና የሚኖራቸው ሚና፣ የከዋኙ ጥበባዊ አቀራረብ፣ የታዳሚዎቹ አቀባበልና ውበት በሙሉ እንደሚመለከት ይገልፃሉ፡፡

ሌላው ከክዋኔ ጋር ተነጥሎ የማይታየውና አንዱ ለአንዱ መኖር ወሳኝ ነው ተብሎ በFinnegan (1992) ፣ በSims እና Stephens (2005) እና በRapport (1992) የሚጠቀሰው ስርዓት (ritual) ነው፡፡ የሁለቱን አለመነጣጠል Rapport (*1992,249-50*) ሲገልፁ "*... if there is no performance, there is no ritual, performance itself is an aspect of that which is performed*" ይላሉ፡፡ የስርዓት ዋና ባህሪ ክዋኔ እንደሆነም አያይዘው ይገልፃሉ፡፡ እንደ ስርዓቱ አይነትም ክዋኔው ይለያያል፡፡ አውድን መሰረት በማድረግም ስርዓት በሁለት ይከፈላል፡፡ እነሱም፡- ዝቅተኛ አውድ ስርዓት (*lower context*) እና ከፍተኛ አውድ ስርዓት (*higher context*) ናቸው፡፡

ዝቅተኛ አውድ ስርዓት የሚባለው ክዋኔው ብዙም ያልሰፋ፣ ብዙ ጥረት የማይጠይቅ፤ ረዘም ያለ ጊዜ የማይወስድ፣ ከዋኞቹ ለመከወን ብዙ ጥረት የማያደርጉበት፣ የስርዓት አይነት እንደሆነ Finnegan (1992,98) ይገልፃሉ፡፡

ከፍተኛ አውድ ስርዓት የሚባለው ደግሞ የዝቅተኛ አውድ ስርዓት ተቃራኒ ነው፡፡ ይህ ስርዓት ክዋኔው ብዙ ጥረትን የሚጠይቅ፣ ሰፊ ጊዜ የሚወስድ፣ ከዋኞቹም ልምድ ያላቸውና ክዋኔውን በስርዓት የሚያውቁት፣ ሰፊ ዝግጅት (በምግብ፣ በቁሳቁስ) የሚደረግበት፣ ወዘተ. አይነት ከበራ ነው፡፡ ከሁለቱም የስርዓት አይነቶች መረዳት እንደሚቻለው ከስርዓቱ ጋር ክዋኔ መኖሩን ነው፡፡ ስርዓቱን የተሳካ ለማድረግ ክዋኔው አብሮ ይመጣል፡፡ የስርዓቱ ዓይነትና ክዋኔው የተሳካ እንዲሆን ሁለቱም ተጣጥመው መገኘት አለባቸው፡፡ ለምሳሌ፣ የሰርግን ስርዓት ለመከወን የሙሾ ክዋኔ አያስፈልግም፤ ልደትን ለማክበር የሰርግ ክዋኔ አይካሄድም፡፡ ሁለቱም (ክዋኔውና ስርዓቱ) ሂደታቸው የሰመረ እንዲሆን በየዘርፋቸው መከወን እንዳለባቸው እንረዳለን፡፡ ስለዚህ ለእያንዳንዱ ስርዓት የራሱ የሆነ ክዋኔ አለው ማለት ነው፡፡ ይህም የሚያመለክተው ክዋኔ እና ስርዓቱ የማይነጣጠሉ መሆናቸውን ነው፡፡

ሰዎች በእነዚህ ስርዓቶች እና በክዋኔዎቻቸው ማንነታቸውን፣ ፍልስፍናቸውን፣ አስተሳሰባቸውን፣ ታሪካቸውን፣ ወዘተ ከትውልድ ወደ ትውልድ ያስተላልፉበታል፡፡ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩትን የክዋኔ ሂደቶች እና ስርዓቶች ተከትሎ ማጥናት ደግሞ የሚጠናውን ማህበረሰብ በሚገባ ለማወቅ ያስችላል፡፡

ከክዋኔ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሌላው ጉዳይ የክዋኔ ባህሪያት ናቸው፡፡ እነዚህ የፎክሎር የክዋኔ ባህሪያት የሚባሉትም ፎክሎራዊ ጉዳዩ የሚካሄድበት መቼት፣ የፎክሎሩ አይነት (text) ፣ ከዋኙ፣ አድማጭ (ተመልካች) ፣የአከዋወን ቅደም ተከተሉ፣ ደንቡ፣ የሚተላለፈው መልዕክት፣ ናቸው፡፡ የዘርፉ ምሁራንም እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት የክዋኔ ባህሪያትን ፎክሎራዊ ጉዳዮች በሚከወኑበት ወቅት ፎክሎሩ ከበቀለበት ባህል አንፃር ሊተረጎሙ የሚገባቸው ነጥቦች መሆናቸውን ያሳስባሉ፡፡

ከክዋኔ ጋር ተያይዘው የሚመጡና የማይለዩ ጉዳዮች ናቸው፤ ተብለው በተለያዩ የባህል አጥኝዎች ከሚጠቀሱት መካከል የመከወኛ አጋጣሚ፣ ከዋኝ፣ ታዳሚ፣ አውድ እና የክዋኔ ጠቋሚዎች የሚባሉት ይገኛሉ፡፡ የፎክሎራዊ ጉዳዩን ክዋኔ በትክክል ለመረዳትና ለመተርጎም ደግሞ እነዚህ ነጥቦች ወሳኞች ናቸው፡፡ በተጨማሪም አንድ ሰው አድማጭ በሌለበት ቦታ ተረት እንደማይተርት ሁሉ ያለ አጋጣሚ፣ ያለ ከዋኝ፣ ያለ ታዳሚ፣ ያለ አውድ፣ ወዘተ. ክዋኔን ማሰብ አይቻልም፡፡ ክዋኔ የእነዚህ እና ሌሎች መሰል ጉዳዮች ጥምር ውጤት ነው፡፡ እነዚህን ቀጥሎ በዝርዝር እንመልከታቸው፡፡

የመጀመሪያው የመከወኛ አጋጣሚዎች ነው፡፡ ፎክሎር ለመከወን አጋጣሚ መኖር አለበት፡፡ "*Performances are not produced at random times. The occasions for performances are limited and can be observed in the field*" እንዲሉ Vansian (1985, 49)፡፡ ለምሳሌ፡- ያለለቅሶ ሙሾ አይወረድም፡፡ ያለሰርግ የሰርግ ዘፈን አይዘፈንም፤ ያለስራ የስራ ግጥም አይገጠምም፤ ያለአጋጣሚው ጉዳዩን ለመከወን ቢታሰብ ድምቀት አይኖረውም፡፡ ትኩረት ሰጥቶ የሚመለከተውም ያጣል፡፡

የፎክሎራዊ ጉዳዩን ሁኔታ ለመረዳት፣ ትዕምርቱን፣ ሜታፈሩን፣ አገላለፁን (የአካል እንቅስቃሴ፣ የድምፅ አወጣጥ፣ አልባሳት) ዳር ቆሞ ወይም አብሮ በመሳተፍ ለመረዳት አጋጣሚዎች ያስፈልጋሉ፡፡ ክዋኔው የሚካሄድበትን ቦታ እና ጊዜ፣ ክዋኔው የተዘጋጀበትን ምክንያት እና

ጉዳይ፣ በክዋኔው ውስጥ የሚሳተፉ ሰዎች እና የሚኖራቸው ሚና፣ የከዋኙ ጥበባዊ አቀራረብና የታዳሚዎቹ አቀባበል ሁሉ ከአጋጣሚዎች ጋር ተያይዘው የሚመጡ ተከዋኝ ጉዳዮች ናቸው፡፡

ሁለተኛው ጉዳይ ከዋኙ ነው፡፡ ክዋኔ ሲታሰብ ከዋኝ አለ፡፡ ያለ ከዋኝ ክዋኔ ይኖራል ብሎ ማሰብ አይቻልም፡፡ ከዋኙ ድልድይ ነው፤ ያለፈውን ትውልድ ጥበብ ለሚቀጥለው እና አሁን ላለው ትውልድ ያስተላልፋል፡፡ "*Performance involves on the part of the performer an assumption of accountability to an audience for the way in which communication is carried out, above and beyond its referential content*" (Bauman 1975, 293) እንዳሉ፡፡

ከዋኝ የሚባለው ፎክሎራዊ ጉዳዩን የሚከውነው አካል ነው፡፡ ተረቱን የሚተርተው፣ ሙሾውን የሚያወርደው፣ ምሳሌውን የሚመስለው፣ ታሪኩን የሚተርከው ወዘተ. አካል ነው ከዋኝ፡፡ ለክዋኔው መሳካት የከዋኙ ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ስለዚህ ከዋኝ በክዋኔ ውስጥ ሰፊ ድርሻ ወይም ሚና ይኖረዋል፤ ማለት ነው፡፡

የከዋኙ ማንነት እንደሚከወነው ፎክሎራዊ ጉዳይ እና አይነት ይለያያል፡፡ ከዋኞች በዕድሜ፣ በፆታ፣ በማህበራዊ ደረጃ እና በልምድ ይለያያሉ፡፡ መለያየታቸው ብቻ ሳይሆን ከእያንዳንዱ ከዋኝ ማንነት እና ደረጃ አንፃር ጉዳዩን መመርመር እንደሚገባ *Finnegan (1992, 90)* ያሳስባሉ፡፡

በአንድ ክዋኔ ውስጥ አንድ ሰው ብቻውን የከዋኝነት ሚና ሊጫወት ይችላል፡፡ በአንዳንድ የክዋኔ አይነቶች ደግሞ ሁለት እና ሶስት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች በጋራ የከዋኝነት ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ በለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ወቅት ሙሾ አውራጆች የከዋኝነት ሚና ይጫወታሉ፡፡ አንዱ ሙሾውን ሲደረድር ሌሎች ደግሞ የመቀበሉን ሚና ይይዛሉ፡፡ ስለዚህ ክዋኔው የሚከወነው በጋራ ይሆናል፡፡

ሌላው ክዋኔና ከዋኝ ሲታሰብ አብሮ የሚመጣው ታዳሚ ነው፡፡ ታዳሚ የክዋኔው አንዱ አካል ነው፡፡ ያለ ታዳሚ ክዋኔ አይኖርም፡፡ Finnegan (1977, 216) "*Audience is really part of the performance itself*" እንዳሉ፡፡ ታዳሚ በክዋኔ ውስጥ የራሱ ሚና አለው፡፡ ከሚናዎቹ መካከልም ከዋኙን ማጀብ፣ አብሮ የመሳተፍ እና የአድማጭነት ተግባር የሚሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ታዳሚዎች ከዋኙን ተከትለው በጭብጨባ፣ በመሳሪያ፣ በሆታ፣ በእልልታ፣ በድምፅና በዜማ ወዘተ ሊያጅቡት ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ በሙሾ ጊዜ ሙሾ አውራጁ (ጇ) በግጥምና በዜማ ሙሾውን በሚያወርዱበት ጊዜ አውራጁን ተከትለው በማጀብ ሊከውኑ ይችላሉ፡፡

ከላይ የተገለጹትን አጠቃሎ የሚይዘው ደግሞ አውድ ነው፡፡ አውድ አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ በሚከወንበት አካባቢ ያለውን ሁሉ አጠቃሎ ይይዛል፡፡ ፎክሎራዊ ጉዳዩን፣ ቁሳዊ ባህሉን፣ የፎክሎራዊ ጉዳዩ ታሪካዊ ሂደት፣ ከዋኙን፣መቼቱን እና ታዳሚውን ያካትታል፡፡ ይህንን ሀሳብ Sims እና Stephens (2005, 138) "*context refers to anything and everything that surrounds a text and performance*" በማለት ይገልፃሉ፡፡ አንድን ፎክሎራዊ ጉዳይ ለመረዳት ደግሞ አውዱን በቅድሚያ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ፡- ለቅሶ እንደየማህበረሰቡ እምነት እና ፍልስፍና ይለያያል፡፡ ይህንን የለቅሶ ስርዓት ደግሞ ለመረዳት ማህበረሰቡን መሰረት በማድረግ ከማህበረሰቡ አውድ አንፃር መረዳትና መተርጎም ያስፈልጋል፡፡
አውድን በሁለት ክፍሎች ከፍሎ መመልከት እንደሚቻል Sims & Stephens፡ Dan Ben Amosን ጠቅሰው ይገልፃሉ፡፡ እነዚህም ተጨባጭ አውድ (*physical context*) እና ማህበራዊ አውድ (*social context*) ናቸው፡፡

ተጨባጭ አውድ ሲባል ጉዳዩ የሚቀርብበትን አጠቃላይ መልክዓ ምድራዊ ሁኔታ፣ የአየር ፀባይ፣ ቁሳዊ ባህሎችን፣ የከዋኞችን አካላዊ እንቅስቃሴ በሙሉ ያጠቃላል፡፡ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት በሙሉ በክዋኔው ወቅት ትኩረት የሚሰጣቸው ነጥቦች መሆናቸውን Ben-Amos (1993, 215-216) ይገልፃሉ፡፡
ማህበራዊ አውድ ሁለተኛው የአውድ ክፍል ሲሆን አጠቃላይ የክዋኔውን መዋቅር ይመለከታል፡፡ የከዋኞችን ማንነት (ማህበራዊ ደረጃ፣ ፆታ፣ እድሜ፣ እውቀት፣ ሀይማኖት፣ የትምህርት ደረጃ) ፣ የታዳሚውን ማንነት እና ተመሳሳይ ጉዳዮችን በሙሉ ያካትታል፡፡
በክዋኔው ላይ የሚታዩ እና የሚሳተፉ ማንኛውንም ነገሮች መመልከትና ለመረዳት መሞከር ፎክሎራዊ ጉዳዩን ለመረዳት ያስችላል፡፡ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ከማህበረሰቡ ጎሳዊ አመለካከት፣ ሀይማኖታዊ ተፅዕኖ፣ ከሌሎች ማህበረሰቦች ጋር ካላቸው ግንኙነት፣ ከማህበረሰቡ ባህል፣ በቅለው በከዋኞች አማካኝነት ለታዳሚዎች የሚደርሱ በመሆኑ የመጀመሪያውን መነሻ ማወቅ እና መረዳት እንደሚያስፈልግ Sims & Stephens (2005, 139) ያስረዳሉ፡፡

በክዋኔ ጉዳዩ የሚጠቀሰው ሌላው ነገር ደግሞ የክዋኔ ጠቋሚዎች ናቸው፡፡ የክዋኔ ጠቋሚዎች የሚባሉት ፎክሎራዊ ጉዳዩ መጀመሩን እና መጠናቀቁን የሚያበስሩ ሲሆኑ Sims & Stephens (2005, 141) "*...devices or actions mark the ends and beginnings of performances*" በማለት ይገልጿቸዋል፡፡ እነዚህ ጠቋሚዎች ደግሞ ማህበረሰቡ ለመግባባት ያመቸው ዘንድ ይሁነኝ ብሎ የተስማማባቸው ናቸው፡፡ ለምሳል፡- ተረት በሚተረትበት ጊዜ "ተረት ተረት፣

ከዕለታት ባንድ ቀን፣ እንትናና እንትና ነበሩ" ወዘተ. እየተባለ ወደ ጉዳዩ ይገባል፡፡ እነዚህ በሙሉ ተረቱ መጀመሩን የሚያበስሩ የተረቱ መከወን እውን መሆንን የሚያመለክቱ ጠቋሚዎች ናቸው፡፡ ጠቋሚዎቹ በሚታዩበት ጊዜ ማህበረሰቡ በስምምነቱ መሰረት ምን ሊከሰት እንደሚችል ወይም ምን እንደተከሰተ አስቀድሞ እንዲያውቅ እድሉን ይሰጣሉ፡፡ እድሉን መስጠት ብቻም ሳይሆን የእያንዳንዱ ተመልካች የስራ ድርሻ ምን ሊሆን እንደሚችል የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ሀይማኖታዊ ስርዓቶችን መመልከት ነው፡፡ በሀይማኖታዊ ስርዓት ጊዜ በምዕመናኑ እና በሃይማኖት መሪው (ስርዓት አስፈፃሚው) አካል መካከል የሚያግባቡ ጠቋሚዎች አሉ፡፡ ጸሎት እንዴት እንደሚጀመር፣ እንዴትስ እንደሚጠናቀቅ፣ ወዘተ የሚያመለክቱ ጠቋሚዎች አሉ፡፡ እነዚህ ጠቋሚዎችም በሁለቱ አካላት መካከል ይሁነኝ ብለው የፀደቁ ስምምነቶች ናቸው፡፡
አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ ሲከወን ከተለመደው የማህበረሰቡ የአከዋወን ስልት ወይም ፍልስፍና እንዳይወጣ የክዋኔ ጠቋሚዎች ሚና ከፍ ያለ ነው፡፡

ከእነዚህ የክዋኔ ባህሪያት ጋር እጅ እና ጓንት ሆነው ለክዋኔው መሳካት ያግዙ ዘንድ ከፎክሎራዊ ጉዳዮች ተለይተው የማይታዩት ቁሶች ናቸው፡፡ እነዚህ ቁሶች ከክዋኔው ጋር አብረው በመምጣት ክዋኔውን በማጀብ ለጉዳዩ ድምቀት ከመስጠታቸው ባሻገር የማህበረሰቡን ማንነት እና አሻራ በማሳየት በኩል ጉልህ ድርሻ አላቸው፡፡
ቁሶችም (የእጅ ስራዎች፣ አልባሳት፣ ምግቦች ወዘተ) ባህላዊ ፈጠራ ታክሎባቸው የሚዘጋጁ ናቸው፡፡ ፎክሎራዊ ጉዳዮች በሚከወኑበት ጊዜ የተለያዩ ቁሶችን ማካተት የተለመደ ነው፡፡ ክዋኔው ሙሉ የሚሆነው እነዚህ ቁሶች አብረው ሲከወኑ ነው፡፡ እንዳውም ያለቁሳዊ ባህል ፎክሎራዊ ጉዳዮች አይከወኑም፤ ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ እነዚህን ቁሶች ከክዋኔው ጋር አያይዞ ማጥናት ደግሞ አስፈላጊ ነው፡፡

## 2.3 የሙሾ ግጥሞች

የሙሾ ግጥም ከስነቃል በተለይ ደግሞ ከቃል ግጥም አይነቶች አንዱ ነው፡፡ የለቅሶ ስርዓቱን ለማድመቅ፣ ሰዎች ለሟች ያላቸውን ወዳጅነት ለመግለፅ፣ ወዘተ ከዝርው ይልቅ ግጥሞችን በመግጠም ስሜታቸውን ይገልፃሉ፡፡

የቃል ግጥሞችን ፋይዳ አስመልክተው Finnegan (1977,25) "ቃል ግጥም ትኩረት በሚሹ ጉዳዮች ላይ (*serious purpuses*) ከሀተታ የበለጠ ጠንከርና ከረር ያለ ሀሳብ ለመስጠት ያገለግላል" ይላሉ፡፡ ከዚህ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው በቃል ግጥሞች ሊተላለፉ የሚፈለጉት

ጉዳዮች ቁም ነገር ያለው እና አንገብጋቢ የሆኑ መልዕክቶች እንደሆኑ ነው፡፡ በደራሲው እና በተደራሲው መካከል ያለው ቅርበት እና ርቀት ቢለያይም የሙሾ ግጥሞች የተናጋሪውንና የአድማጮችን ተሳትፎ የሚጠይቁ ናቸው፡፡ ታዳሚው አካል ቀጥተኛ ተሳታፊ እንዲሆን የማድረግ ኃይል አላቸው፡፡ ምክንያቱም በአብዛኛው ቃል ግጥሞች የሰውን ስሜት የመቀስቀስ እና የማነቃቃት ኃይል አላቸውና ነው፡፡ ክዋኔው ሙሉ የሚሆነው ደግሞ የሙሾ ግጥሞቹ ከክዋኔው ጋር በአንድ ላይ ሆነው ሲታዩ፣ ሲጠኑ እና ሲቀርቡ ነው፡፡ የሙሾ ግጥሞችን ከክዋኔው ለይቶ ማጥናት ክዋኔ አያሰኘውም፤ የሙሾ ግጥሞችን ሳያካቱ ሙሉውን የለቅሶ ክዋኔ አይቻለሁ፤ ማለትም አያስደፍርም፡፡ ይህንን ሀሳብ ፈቃደ (1984፣1-2) እንደሚከተለው ያብራራሉ፡፡

> *አንዲት አልቃሽ በአንድ ለቅሶ የምታደርገውን ግጥም ስብስብ በፅሁፍ ማስፈርና ለአንባቢ ማስተላለፍ ይቻላል ዛሬ፡፡ ነገር ግን ይህ ስብስብ የሙሾውን አከዋወን አይጨምርም፡፡ አልቃሽ ከግጥሙ ውጭ የሆነውን የክዋኔው ማጎልበቻ አድርጋ የምትገለገልባቸውን ጠቅላላ ድባቡንም አይጨምርም፡፡ የሚያነበውን ሰው ስሜት ምንም ያህል አይነካም፤ አካሉ ከሆነው ማህበራዊ እውነታውና ክዋኔው ተለይቷልና፡፡*

ከፈቃደ ሀሳብ እንደምንረዳው የሙሾ ግጥም ለብቻው ከተጠና ከእውነተኛ አካሉ ተነጥሏል፤ ማህበራዊ እውነታውን (ማህበረሰቡ በግጥሙ ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልዕክት) ያጣል፡፡ ስለዚህ በአጭሩ ክዋኔውን ስናጠና ሁለቱን ነገሮች (ግጥሙንና ክዋኔውን) ሳንለይ ማጥናት አስፈላጊ ነው፡፡

በለቅሶ ጊዜ የሚኖረው የሙሾ አወራረድ፣ የግጥሞቹ ዜማ፣ ከግጥሞቹ ጋር ተያይዘው የሚመጡት የአካል እንቅስቃሴዎች፣ ወዘተ. ለለቅሶው ድምቀት ከመስጠት በተጨማሪ የማያለቅሰውን እንዲያለቅስ፣ የማያዝነውን እንዲያዝን እና ሁሉም ታዳሚዎች እና ከዋኞች በአንድ ላይ ህብር ፈጥረው እንዲከውኑ የሙሾ ግጥሞቹ አይነተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡

ስለዚህ ባጭሩ የሙሾ ግጥሞች የለቅሶ ክዋኔው አንድ አካል ስለሆኑ ከክዋኔው ተነጥለው ለብቻ ሊጠኑ እንደማይችሉ እንረዳለን፡፡ በሙሾ ግጥሞች ውስጥ ክዋኔውን መሰረት በማድረግ የማህበረሰቡን የተወሰነ መልክ ማጥናት ይቻላል፡፡ ማህበረሰቡ በሙሾ ግጥሞች የተለያዩ አስተሳሰቦችና አመለካከቶችን ሊያንጸባርቅ ይችላል፡፡

## 3. የቤንች ብሔረሰብ ማህበረ ባህላዊ ዳራ

ይህ ክፍል የቤንች ማጂ ዞን እና የቤንች ብሔረሰብ የተወሰኑ ማህበረ ባህላዊ ጉዳዮች የሚቀርቡበት ነው፡፡ በመጀመሪያም ስለ ቤንች ማጂ ዞን አጠቃላይ መልክ ከገለፅኩ በኋላ ስለ ቤንች ብሔረሰብ ማህበረ ባህላዊ ዳራ ከኔ ጥናት ጋር ተያያዥነት አላቸው ያልኳቸውን ባህል ነክ መልኮች (ብሔረሰቡ ታሪካዊ አመጣጥ፣ አሰፋፈር፣ ቋንቋ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊ አስተዳደር፣ መልክዓ ምድራዊ ገፅታ፣ የምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ) አቀርባለሁ፡፡

### 3.1 የቤንች ማጂ ዞን አጠቃላይ ገጽታ

የቤንች ማጂ ዞን በደቡብ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ከሚገኙ 14 ዞኖች መካከል አንዱ ነው፡፡ የዞኑ ዋና ከተማ ሚዛን ስትሆን ከአዲስ አበባ በስተደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ በ 561 ኪ/ሜ እና ከክልሉ ርዕሰ ከተማ ሀዋሳ በ 836 ኪ/ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡

የዞኑ ጠቅላላ የቆዳ ስፋት 19,965.8 ስኩዌር ኪ.ሜ ሲሆን በሰሜን ከሸኮ ዞን፣ በደቡብ ከኬንያ፣ በምዕራብ ከሱዳን እና በምስራቅ ከከፋ ዞን ጋር ይዋሰናል፡፡ በዞኑ ቤንች፣ ዲዚ፣ መኤኒት፣ሸኮ፣ ሱርማና ዝልማሙ (ባሌ) የተባሉ ስድስት ብሔረሰቦች ይገኛሉ፡፡ የመሬት አቀማመጥጡ ሜዳማ፣ ተራራማና ሸለቋማ ነው፡፡ እንዲሁም ከባህር ወለል በታች እስከ 1000 ሜትር የሚደርስ መልክአ ምድራዊ ገፅታ ሲኖረው የአየር ንብረቱ ደግሞ ደጋ፣ ወይናደጋና ቆላማ ነው፡፡ በዞኑ የሚገኙ ብሔረሰቦች ዋና መተዳደሪያ ግብርና ነው፡፡ በ1999 ዓ.ም የህዝብ እና ቤት ቆጠራ ውጤት መሰረት የዞኑ አጠቃላይ ሕዝብ ብዛት 659,046 እንደሆነ *የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ፕሮፋይል* (2001፣86-87) ያሳያል፡፡

### 3.2 የቤንች ብሔረሰብ አመጣጥ እና አሰፋፈር

የቤንች ብሔረሰብ በቤንች ማጂ ዞን ውስጥ ከሚገኙ ስድስት ብሔረሰቦች መካከል አንዱ ነው፡፡ የብሔረሰቡ አሰያየም "ቤንችቴያት" ከተባለው ጥንታዊ የብሔረሰቡ መሪ እንደተወረሰ *የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ፕሮፋይል* (2001፣60) ተገልጿል፡፡ "ቲያት" የሚለው ቃል "ጌታ" ማለት ሲሆን "ቤንች" የሚለው ቃል ለብሔረሰቡ እና ለቋንቋው መጠሪያ ነው፡፡

የብሔረሰቡ አባላት በዋናነት በዞኑ በሰሜን ቤንች፣ በደቡብ ቤንች እና በሼ ቤንች ወረዳዎች እንዲሁም በሸኮ እና ጉራፈርዳ ወረዳዎች ውስጥ ይኖራሉ፡፡ ከዞኑ ውጭም የብሔረሰቡ አባላት ኩታ ገጠም በሆኑት በከፋ ዞን በጨና እና ዲቻ ወረዳዎች እና በሸካ ዞን በየኪ ወረዳ አካባቢዎች

ይገኛሉ፡፡ ብሔረሰቡ በሰሜን ምስራቅ የካፋ፣ በደቡብ እና በምዕራብ የሸኮ፣ በምስራቅ እና በደቡብ የመኤኒት ብሔረሰቦች ጋር ይዋሰናል፡፡ በ1999 ዓ.ም በተደረገው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ውጤት መሰረት የብሔረሰቡ ብዛት 353,526 ነው፡፡ *(የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ፕሮፋይል* 2001፣81)

ስለቤንች ብሔረሰብ ጥንተ አመጣጥ በቂ የሆነ የፅሁፍ ማስረጃ ባይኖርም የብሔረሰቡ ታሪክ አውሸዎች የተለያዩ የቃል ማስረጃዎችን ከቀደም አያቶቻቸውና አባቶቻቸው እንደሰሙት በቃለ መጠይቅ ጊዜ አቶ ሾጫ እና አቶ ኖፒ እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡፡

> *የቤንች ሕዝብ ከየትኛው ብሔረሰብ እንደፈለሰ በውል ባይታወቅም ከኦሞ አካባቢ እንደተነሱና ወደ ዴቻ (ጎባ ጫራ) አካባቢ መጥተው ለተወሰኑ አመታት ከቆዩ በኂላ ከዚያ ዴቻ (ጎባ ጫራ) ተነስተው ባቹማን ወይም ጎልዲያን አቋርጠው በሼ ቤንች አካባቢ ዣዥ በሚባል ስፍራ ከረዥም አመታት ከመኤኒት (ዳይም) ከሚባለው ብሔረሰብ ጋር አብሮ እንደኖሩ ይነገራል፡፡ አንዳንድ ታሪክ አውጊዎች እንደሚናገሩት በዣዥ ላይ ተወልደው ቁጥራቸው እየበዙ ሲሄዱ በቦታ ጥበት ከመኤኒት ጋር በመጋጨት እና የመኖሪያ ቦታ ወይም ግዛት ለማስፋፋት ሲባል አሁን ወደሚኖሩበት አካባቢ ሁለት ጎሳ የሆኑት ማለትም ቤንችና ሜር ቤንች የተባሉት ጎሳዎች ቀደም ሲል መጥተው እንደሰፈሩ ይነገራል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት 13 እና 17/ 2005 በተከታታይ)*

በተያያዘም ቄስ ሳሙኤል (2000፣5) የተባሉ የቋንቋ አጥኝ እና የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጎሚ የቤንች ብሔረሰብን አመጣጥ አስመልክተው "...ዣዥ በሚባለው አካባቢ በአንድ ላይ በነበሩበት ጊዜ የመጀመሪያው ቤንች ሕዝብ አባትና የጎሳው መሪ ተብሎ የሚታወቁት ቤኑብ ወይም ዣዥቴት የተባሉ ሶስት ወንድ ልጆች ነበሩት፡፡ እነሱም ዛሬ ቤንችቴት፣ ሼቴትና ሜርቴት የተባሉ ታላላቅ የቤንች ብሔረሰብ ጎሳ መሪዎች አባቶች የሆኑት ሲሆን ሼቴት ከአባቱ ጋር ዣዥ አካባቢ ቆይቶ አሁን ባሉበት ሼይ ቤንች አካባቢ ተዋልዶ እንደተስፋፉ" ይገልጻሉ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ *ከደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ፕሮፋይል* (2001፣65) የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው የብሔረሰቡን ታሪክ እና አሰፋፈር በተመለከተ የሚገልፁ የተለያዩ ሀሳቦች አሉ፡፡ ከብሔረሰቡ ትውፊት ከተገኘው መረጃ አንፃር ህዝቡ ጥንት ከአሁኑ ሸዋ ቤንች አካባቢ "ቤንችቴያት" በተባለ መሪ አማካይነት "ወሮጉ" ከተባለ ስፍራ ከጋቸብ ወንዝ ዳርቻ ሰፍሮ የአሁኑን የቤንችን አካባቢ መያዙ ይነገራል፡፡

በሌላም በኩል አቶ ክፍሌ የተባሉ መረጃ አቀባይ ደግሞ የብሔረሰቡን አመጣጥ እንደሚከተለው ይገልፁታል፡፡

*ግልፅ የሆነ መረጃ ባይኖርም አንዳንድ የጽሁፍ መረጃዎች የቤንች ብሔረሰብ ከብዙ ምዕተ አመታት በፊት ጋሞጎፋ ውስጥ ሰፍሮ እንደነበርና ኋላም ወደ ኮንታ በመሻገር ረዘም ያለ ቆይታ ካደረገ በኋላ ዴቻ (ጎባ ጫራ) ሰፍረው ሸዋ ቤንች እንደነበር ይነገራል። በሌላ በኩል ደግሞ የብሔረሰቡ አባላት ከካፋ በስተደቡብ በኩል እና ብሔረሰቡ ዛሬ በሚገኝበት ስፍራ ከ18ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አንስቶ እስከ 19ኛው ምዕተ አመት አጋማሽ ባለው ጊዜ በሸዋ ቤንች በስተደቡብ በጌሻ ኮረብታ እንደሰፈሩ እና በቀስ በቀስ በመስፋፋት ዛሬ ያሉበትን ስፍራ እንደያዙም ይነገራል። (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 07/2005)*

ከፍ ሲል እንደገለፅኩት ስለ ቤንች ብሔረሰብ አመጣጥ እና አሰፋፈር የተለያዩ መረጃዎች የተለያዩ የሀሳብ መለያየት መኖሩን ቢያሳዩም በአሁኑ ጊዜ ግን በዋናነት በሰሜን ቤንች፣ ሼ ቤንች፣ ደቡብ ቤንች፣ የኪ፣ ጨና፣ ሼኮ፣ ዴቻ፣ ጉራፈርዳ፣ ወዘተ አካባቢዎች ሰፍረው ይገኛሉ።

### 3.3 ቋንቋ

የቤንች ብሔረሰብ ቋንቋ "ቤንችኛ" ሲሆን ከኦሞአዊ የቋንቋ ቤተሰብ እና ከሰሜን ጂሞጂያን ንዑስ ቤተሰብ ውስጥ እንደሚመደብ (Christian 2006: 27) ይገልጻሉ። ቋንቋው ከዳውሮኛ፣ ከሸኮኛ፣ ከዲዚኛ እና ከካፊኖኖ ጋር ይመሳሰላል። የቤንች ቋንቋ የራሱ የሆነ የአነጋገር ዘይቤ፣ ሰዋሰው እና አጠራር ድምፅ አለው። ይህንን ቋንቋ ያጠኑ ምሁራን እንደገለፁት ቋንቋው የቶን ቋንቋ (*Tone language)* ማለትም ዜማዊ ቋንቋ እንደሆነ ሳሙኤል (2000)፣ Christian (2006) እና Mary (1986) ይገልጻሉ። በተያያዘም ድምፅን ከፍና ዝቅ እንዲሁም በማጥበቅና በማላላት አንድ ቃል ከአራት በላይ ትርጉም የሚሰጥ ቋንቋ ስለሆነ ዜማዊ ቋንቋ እንዲባል አስችሎታል። ለምሳሌ፡- "ካር" የሚለው የቤንችኛ ቋንቋ ቃል ተርብ፣ የሳር አይነት፣ ንፁህ እና ከቆዳ የተሰራ መታጠቂያ የመሳሰሉ ትርጉሞችን እንደሚሰጥ ሳሙኤል (2000፣34) ይገልፃሉ።

*ከደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ፕሮፋይል* (2001፣ 84) በተገኘው መረጃ በአሁን ወቅት ቋንቋው ከመግባቢያነት አልፎ ለሌላ ተግባር አልዋለም። ይሁንና በ1990 ዓ.ም የመካነየሱስ ቤተክርስቲያን የሳባ ፊደላትን በመጠቀም ቋንቋውን የጽሁፍ ቋንቋ ለማድረግ የሙከራ ጥናት አድርጋ እንደነበር ተገልጿል። የብሔረሰቡ አባላት ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በተጨማሪ አማርኛ፣ ካፊኖኖ እና ሸኮኛ ቋንቋዎችን ይናገራሉ።

### 3.4 ኢኮኖሚ

የህዝቡ ዋነኛ መተዳደሪያ ግብርና ሲሆን ለተለያዩ ተግባራት የሚውሉ የእደጥበብ ምርቶችንም ያመርታሉ፡፡ ከተክሎች ቡና፣ እንሰት፣ በርበሬ፣ ሙዝና ሸንኮራ አገዳ ከእህል ሰብል በቆሎ፣ ማሽላ፣ ጤፍ፣ ገብስ እና ስንዴ፣ ከጥራጥሬ ባቄላ እና አተር ከፍራፍሬ ፓፓያ፣ ማንጎ፣ ብርቱካን፣ እና አቦካዶ ከቅማቅመም ኮረሪማ፣ ዝንጅብል እና እርድ፣ ከስራስር ጎደሬ፣ ካቺ እና አሪኮቲ የመሳሰሉት ይመረታሉ፡፡ ቡና ዋነኛው የገቢ ምንጫቸው ሲሆን ቅመማ ቅመም፣ ቆዳ እና ሌጦ ተጨማሪ የገቢ ማስገኛዎች መሆናቸውን የሚዛን አማን ከተማ አስተዳደር ግብርና ጽ/ቤት (2004፣8-11) አመታዊ ሪፖርት ያሳያል፡፡

### 3.5 ባህላዊ አስተዳደር

የቤንች ብሔረሰብ በልማድ የሚተዳደርባቸው የራሱ የሆኑ ማህበራዊ ሕግጋት አሉት፡፡ እነዚህም የባላባትና የቃልቻ ሕግ እና የባላባትና የሚያንጊ (ንጉስ) ሕግ ናቸው፡፡ የባላባትና የቃልቻ ሕግ አንድ ባለቃልቻ ከቃልቻነቱ በተጨማሪ የባላባትነትን ሚና ደርቦ የሚሰራ ነው፡፡ ይህ አይነት አስተዳደር ሕዝቡን የሚያስፈራራበትና የሚጨቁንበት ህግ አለው፡፡ ሕጉንም የሚያወጣው ባለቃልቻው ነው፡፡ የባላባቱን ሕግ የጣሰ ለባላባቱ ከፍተኛ፣ መካከለኛና ዝቅተኛ ተብሎ የተመደበ ቅጣት ይከፍላል፡፡ ከፍተኛ ቅጣት እናት ላም (ካርሺን)፣ መካከለኛ ቅጣት በሬ (ጋንስ) እና ዝቅተኛ ቅጣት ጥጃ (ኦት) ወይም ወይፈን (ማንት) ናቸው፡፡ ይህን ሀሳብ በተመለከተ አቶ ባላካኝ የተባሉ መረጃ አቀባይ እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡፡

> *"…ድሮ ያጠፋ ሰው ወይም መመሪያውን ያልፈፀመ ሰው ባለቃልቻው ፊት ቀርቦ እንዲቀጣ ይደረጋል፡፡ እንደጥፋቱ አይነት ታይቶ ከብት ሊከፍል ይችላል፡፡ ቀላል ቅጣት የሚባለው ደግሞ ከከብት ውጭ የባለቃልቻውን አጥር እንዲያጥር፣ እርሻ እንዲያርስ፣ አዝመራውን እንዲከውን ይደረግ ነበር፡፡ ዛሬ ዛሬ ግን ይህ እንደድሮው የለም፡፡ ጉዳዩ የሚፈታው በሌላ ሰዎች (ፍርድ ቤት) ሁኗል፡፡ ድሮ የተበደለ ወደ መሪው ሄዶ በደሉን ያስረዳ ነበር፡፡ አሁን የሚሄድ የለም፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 03/2005)*

የባላባትና የሚያንጊ (ንጉስ) ሕግ የሚባሉት ደግሞ ከቃልቻ በላይ ስለሆኑ ይግባኝ ሰሚዎች ናቸው፡፡ በሚያንጊ የታዬ ዳኝነት ደግሞ የትም በይግባኝ ሊሄድ አይችልም፡፡ ቃልቻን፣ ሚያንጊን እና ባላባትነትን ደርበው የያዙት በመሬት ላይ የማዘዝ ስልጣን፣ ዘመድ አዝማድ የሌለው ሰው ሲሞት ንብረቱን የመውረስ ፣አንድ ግለሰብ የተቀጣውን ቅጣት ሳይከፍል ቢሞት እንዳይቀበር

የመከልከል እና ካሳ የመጠየቅ ስልጣን ያላቸው ናቸው፡፡ ነገር ግን በአሁኑ ሰዓት መንግስት ይህንን ስርዓት እንደቀየረው አቶ ግርማ ግዥ (ቃለመጠይቅ፣ ጥር 05/2005) ይናገራሉ፡፡

*የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ፕሮፋይል* (2001፣ 87) በቤንች ብሔረሰብ ውስጥ በርካታ ጎሳዎች የሚገኙ ቢሆንም በአራት ዋና ዋና ማህበራዊ ቡድኖች እንደሚከፈሉ ያሳያል፡፡ እነርሱም ከምት፣ ቃም፣ መንጃ (ባንድ) እና ማኖ (ፋቂ) ይባላሉ፡፡ "ከምት" የባላባት ዝርያ ያላቸው የገዥው መደቦች ሲሆኑ "ቃም" ደግሞ በውትድርና ፣ በማር አጨዳ፣ በከብት ጥበቃ፣ በእርሻ፣ በንብ ማነብ፣ እና ውሀ በመቅዳት የገዥውን መደብ (ከምት) ነገስታት የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ "መንጃ" እንደ ዝቅተኛ ጎሳ ይቆጠር የነበር ሲሆን በባህላዊ የስራ ክፍፍሉ መሰረት የመንጃ ወንዶች በአደን፤ ሴቶች ደግሞ በሸክላ ስራ የተሰማሩ ናቸው፡፡ "ማኖ" (ፋቂ) የሚባሉት ደግሞ ቆዳን በመፋቅ እና በማልፋት የሚተዳደሩ ናቸው፡፡ በእያንዳንዱ ጎሳ ስር የተለያዩ ንዑሳን ጎሳዎች አሉ፡፡

ከላይ እንደጠቀስኩት ብሔረሰቡ የራሱ የሆነ ባህላዊ አስተዳደር እና የዳኝነት ስርዓት ያለው ሲሆን፤ ባህላዊ አስተዳደሩ የስልጣን እርከን እና የስራ ሃላፊነት የሚወሰነው በእየርከኑ ባሉ ሽማግሌዎችና በጎሳ መሪዎች ምርጫ አማካኝነት ነው፡፡

"ከምት" ከፍተኛ ከበሬታ የሚሰጠው መሪ ነው፡፡ ማንኛውንም ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ ጉዳዮችን በበላይነት ይመራል፡፡ የባህላዊ አስተዳደሩ ቁንጮ ከዚህ ጎሳ የሚሾም ሲሆን "ቤንችያት" ከምት /ባላባት/ ይባላል፡፡ ከምት የሚመረጠው "ከባይክስ" ጎሳ ሲሆን የስልጣን ሽግግሩ የዘር ሀረግን የተከተለ ነው፡፡ የመሪዎች ወይም የ"ቲያቶች" ስልጣን የሚተላለፈው ከቲያቶች የመጀመሪያ ሚስት ለተወለደ ለበኩር ልጅ ነው፡፡ መሪው ዘር ሳይተካ በሚሞትበት አጋጣሚ ወንድሙ ስልጣኑን ሊወርስ ይችላል፡፡ ለ "ቲያትነት" የሚመረጠው ልጅ ወይም ወንድም በቂ ችሎታ ያለው እና ከሌላ ወገን ያልተቀላቀለ ቤንች መሆን ይጠበቅበታል፡፡

የቤንች ብሔረሰብ ከ18ኛው ምዕተ አመት መጨረሻ ጀምሮ የራሱ የአስተዳደር ስርዓት የነበረው መሆኑን እና መሪውም "ቤንችቲያት" በሚል የማዕርግ ስም እንደሚጠራ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ለአብነት ያህል (ኩንዲሳ 1989፣ ግርማ 1999፣ ሳሙኤል 2000) ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ቤንችቲያቶች መለኮታዊ ሀይል አላቸው ተብሎ ስለሚታመኑ ይከበራሉ፤ ይመለክባቸዋል፡፡ ከመሪው በታች "ቲያቶች" የተሰኙ ስድስት ገዥዎች ሲኖሩ ከነርሱ በታች "ኡከር" (ባርት) የተባሉ የቀበሌ ሹሞች ይገኛሉ፡፡

ከባህላዊ መሪው ሌላ መንፈሳዊ መሪዎች የሚገኙ ሲሆን የራሳቸው መዋቅር አላቸው። የቤንች ብሔረሰብ በባህላዊ የአስተዳደር ስርዓት አለመግባባቶችን የሚፈታበት የተለያዩ የግጭት አፈታት ስልቶች አሉት። አቶ ቡንሶ የተባሉ መረጃ አቀባይ ከላይ ከጠቀስኩት ሀሳብ ጋር በተያያዘ የሚከተለውን ይገልፃሉ።

> *በግድያ፣ በድንበር፣ በግጦሽ መሬት፣ በጠለፋ ጋብቻ የሚነሱ ግጭቶች እንደጉዳዩ ክብደት እና ቅለት በሀገር ሽማግሌዎች ይፈቱ ነበር። አሁን ደግሞ የሀገር ሽማግሌዎች እና መንግስት በጋራ ሁነው ይፈታሉ። ግድያ ከተፈፀመ የወንጀሉ አፈፃፀም ከተጣራ በኋላ በሁለት ደመኞች ድንበር ላይ በሬ ታርዶ በደም ይታረቃሉ። ልጃገረድ ከገዳይ ወገን በካሳ ትሰጥ ነበር። በብሔረሰቡ መዋሸት፣ መስረቅ፣ ዝሙት መፈፀም አጥብቆ የተከለከለ ነው። ቅጣቱም ከበድ ያለ ነው። ይህን አይነቱን ተግባር የፈፀመ ለቃልቻ ወይፈን ወይም ጊደር እንዲሰጥ ይገደዳል። ሰው የገደለ በሞት በስቅላት፣ ገደል በመወርወር፣ በሁለት እጆቹ የፈጥኝ ታስረው የሟች ወገኖች በጦር ወጋግተው አሰቃይተው እንዲገድሉት ይደረግ ነበር። (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት 18/2005)*

በዚህ ንዑስ ርዕስ እንደገለፅኩት እና በቃለ መጠይቅ ጊዜ መረጃ አቀባዮች እንደጠቀሱት የብሔረሰቡ ባህላዊ ዳኝነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተለወጠና በሌላ (በመንግስት ፖሊሲ) እየተተካ መምጣቱን ለመረዳት ይቻላል።

### 3.6 እምነትና አምልኮ

የቤንች ሕዝብ ከጥንት ጀምሮ የሙት መንፈስ ማለት "ሚያንግ" (የሞቱት ሰዎች መንፈስ) የቀድሞ አያት፣ የአባት፣ የጎሳ መሪዎች የሚያንግ የሙት መንፈስ "ካህ" ወይም ውቃቢ ተብሎ የሚታመን የባህል እምነት እንዳላቸው ግርማ (1999፣5) ይገልፃሉ። አያይዘውም ግርማ የጫካና የተራራ አምላክ አውሬዎችና ደንን የሚጠብቅ አምላክ (መንፈስ) በየአመቱ እህል በሚደርስበት ወቅትና አውሬ በሚታደንበት ጊዜ በጫካ ዳርና በተራራ ላይ መስዋዕት (ዴጅ) የሚሰጥ ጋኔል (ቆል) የሚባል አምልኮ መኖሩን ገልፀዋል። በተጨማሪም ቄስ ሳሙኤል (2000፣ 6-7) "ኦሮብቴት" የሚባል በደጅ ወይም ትላልቅ ዛፍ ስር ወይም አንድ ድንጋይ ክምር ወይም "ባርት" ተብሎ በተከለለ ቦታ ጠላ እየተጠመቀና ቡና እየተፈላ ጎረቤት ሁሉ ተሰብስቦ የሚጠጣበት አምልኮ መኖሩን ይጠቅሳሉ።

ለታላላቅ ቃልቻዎች በከፍታ ቦታዎች ማለት በኮረብታዎች ላይ ከአንድ እስከ ሰባት የቃልቻ አምልኮ ቤቶች በእያንዳንዱ ጎሳ ሰፈር ይሰራል። እንዲሁም የሚያንግ ቤቶች በየቤተሰብ መሪዎች ጓሮ ይገኛል። እንዲሁም ትናንሽ መንፈስ (ካሕ ማብ) ቤቶች በሰፈር ውስጥ በብዛት ይገኛሉ። እነዚህ ታላላቅ ቃልቻዎች እራሳቸውን እንደፈጣሪና አምላክ አድርገው ስለሚያሳምኑና

ስለሚቆጥሩ ለትናንሽ ቃልቻዎች እንደ አባት፣ ለሕዝቡ እንደ ፈጣሪ (የአባቴ አምላክ) ተብሎ ይታመኑና ይጠሩ ነበር፡፡ በአሁን ጊዜ ደግሞ በአብዛኛው የቤንች ብሔረሰብ የፕሮቴስታንት ክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች መሆናቸውን በቡድን ውይይት ጊዜ መረጃ አቀባዮቹ ገልፀውልኛል፡፡ (የካቲት 16/2005)

### 3.7 በዓል አከባበር

በብሔረሰቡ ከወቅቶች ጋር ተያይዞ ምርት እንዲሰጥ፣ በሽታ እንዲጠፋ፣ ሰላም እንዲሰፍን በሚል በአመት ሁለት ጊዜያት የሚከብሩ መንፈሳዊ በዓላት አሉ፡፡ በዓላቶቹ በቃልቻዎች እና በባላባቶች ይመራሉ፡፡ ለበዓሉ አከባበር ቦርዴ ተጠምቆ፣ ልዩ ልዩ መልክ ያላቸው ዶሮዎች እና ከ50-60 ያህል ከብቶች ታርደው ይበላል፤ ይጠጣል፤ ይጨፈራል፡፡ አቶ መኮንን የተባሉ መረጃ አቀባይ የብሔረሰቡን የበዓል አከባበር እንደሚከተለው ገልጸውልኛል፡፡

> *በአመት ሁለት ጊዜ የሚከበሩ ዋና በዓላት አሉ፡፡ የመጀመሪያው ታህሳስ ወር ውስጥ ይከበራል፡፡ በዚህ በዓል ላይ ሁሉም የቤንች ህዝብ ወደ መሪው በመሄድ በዓሉን በጋራ ያከብራል፡፡ የእምነት መሪውም አስቀድመው ከሳምንት በፊት ለፀሎት በተዘጋጀላቸው ቤት ውስጥ ሁነው ይፀልያሉ፡፡ አንድ ሳምንት ከፀለዩ በኋላ በዓሉ እንዲጀመር ያደርጋሉ፡፡ ከእምነት መሪዎች ጋር ያሉት ቲያቾም ህዝቡን በመመረቅ በዓሉ እንዲጀመር ያደርጋሉ፡፡ … ከዚያ ወይዘሮች የተዘጋጀውን ቦርዴ ለቲያቶች ይሰጣሉ፡፡ ከዚያም እንደ ስልጣን ደረጃቸው በቅደም ተከተል ቦርዴውን ይሰጣሉ፡፡ የተሰበሰበው ህዝብ ደግሞ ለመሪው ያመጣውን ማር ተራ በተራ ያስቀምጣል፡፡ ሁለተኛው በዓል ከአንድ ወር እረፍት በኋላ የካቲት ላይ የሚደረግ ነው፡፡ ይህ በዓል የሚደረገው ተራራ ላይ በመውጣት ነው፡፡ ቆል በመባል ይጠራል፡፡ የዚህ በዓል ዋና አላማ የተዘራው አዝመራ ስለደረሰ ቆል ከሚባል መንፈስ ጋር ህዝቡ እንዲገናኝ ለማድረግ ነው፡፡ በቆሎ ተጠብሶ ይበላል፤ በበቆሎው ምክንያት ህዝቡ ከመንፈሱ ጋር ተገናኘ ይባላል፡፡ በዚህ በዓል ላይ ሴቶች አይሳተፉም፡፡ ምክንያቱም መንፈስ ሊቆጣቸው ይችላል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት 23/2005)*

ከአቶ መኮንን ሀሳብ እንደምንረዳው በየካቲት ወር በቆሎ እና ከቼ (ቦኘና) ሲደርስ የአካባቢው ነዋሪዎች በሙሉ እሸት ይዘው ወደ ተራራ ይወጣሉ፡፡ እህል ተቀቅሎ ሽማግሌዎች ከበሉ በኋላ መርቀው የአካባቢው ህዝብ እሸቱን እንዲቀምስ ይደረጋል፡፡ ከዚያም ወጣቶች ተሰብስበው እየጨፈሩ እና የተቀቀለውን በቆሎ እየበሉ ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ፡፡

*የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ፕሮፋይል* (2001፣86) ደግሞ ቤንቾች የተለየዩ በዓላትን የዘመን እና የወቅት አቆጣጠርን፣ የጨረቃ መውጣትንና መግባትን ተከትለው ከአዝመራ ወቅቶች ጋር በማዛመድ በልምድ የሚያከብሯቸው በዓላት መኖሩን ያሳያል፡፡ ምርት ከተሰበሰበ በኋላ ወጣት ሴቶች እና ወንዶች በጨረቃ ብርሃን ይጨፍራሉ፡፡ ቄስ ሳሙኤል የተባሉ መረጃ አቀባይም

“ጨረቃ ስትወጣ እና ስትገባ ወጣቶች ጥሩምባ እየነፉ ይጨፍራሉ፤ በጣም ትልቅ ደስታ ይሆናል፡፡ ብሩህ ተስፋ፣ ልምላሜ... መሆኑን የሚያመለክት ነው የጨረቃ መውጣት፡፡ ስትጠልቅ ደግሞ በመጠኑ ይጨፈራል፤ የሚጨፈረውም በዛው ጠልቃ እንዳትቀር ፈጣሪን ለመለመን ነው፤” በማለት ይገልፃሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 18/2005)

የቤንች ብሔረሰብ በህብረት እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን በዓላት ያክብር እንጂ እያንዳንዱ ጎሳ እንደየአካባቢው ሁኔታ የተለያዩ በዓላትንም እንደሚያከብር አቶ ክፍሌ የተባሉ መረጃ አቀባይ ይገልፃሉ፡፡ እነዚህ በዓላትም ከጎሳው እምነት እና አምልኮ ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- በትላልቅ ዛፎች ስር ቡና በማፍላት እና መንገደኛውን በመጥራት የሚያከብሩት በዓል፣ ድንጋይ ስር ቁጭ ብለው ጠላ እና ቦርዴ አዘጋጅተው በመጨፈር ወዘተ. የሚያከብሯቸው በዓላት ይጠቀሳሉ፡፡

## 3.8 የምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ

በብሔረሰቡ ከበቆሎ ወይም ከጤፍ የተሰራ ዳቦ፣ የእንሰት ስር (አምቾ)፣ ጎደሬ እና የጎደሬ ገንፎ ይበላል፡፡ እነዚህ ምግቦች በተለይም አምቾ እና ጎደሬ በቤንች ብሔረሰብ ዘንድ ለቅሶ ሲኖር በስፋት የሚዘጋጁ ናቸው፡፡

ሌላው የቦይና (ከቺ) ጥብስ በቅቤ እና በወተት መመገብ የተለመደ ነው፡፡ የእንሰት ምግቦች በመባያነት ጎመን ከአደንጓሬ ጋር ተቀቅሎ ቅቤ ተጨምሮ ከወተት እና ከስጋ ጋር ይበላል፡፡ በአመት በአል እርድ ይደረጋል፡፡ ከበቆሎ፣ ከጤፍ፣ ከማሽላ እና ከገብስ በመቀቀል የሚያዘጋጁት ጌዝ (ቦርዴ) የተባለ መጠጥ ተጠቃሽ ነው፡፡ ልክ እንደ ቡና ሁሉ ጠዋት በሁሉም ሰዎች ቤት የማይተፋው ደግሞ ጨሞ የተባለው የብሔረሰቡ ባህላዊ መጠጥ መሆኑን ወይዘሮ ታደለች ወዳጆ የተባሉ መረጃ አቀባይ ይገልፃሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 17/2005)

## 4. የቤንች ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ

ለቅሶ በቤንች ብሔረሰብ ዘንድ ‹‹የፐ›› ይባላል፡፡ ትርጉሙም ለቅሶ፣ ሞትና ሐዘን ማለት ነው፡፡ የቤንች ብሔረሰብ የለቅሶ (የየፐ) ስርዓተ ክዋኔ በአምስት ክፍሎች የተመደበ ነው፡፡ እነሱም የባለቃልቻዎች የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ (ሲያቲ የፐ)፣ የባለሚያንግ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ (ሚያንጊ የፐ)፣ የእድሜ ባለፀጎች የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ (አሳ እቅ የፐ)፣ የወጣቶች የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ (ሻትሚኦ ወርኒኣ ወይም ናይቲ የፐ) እና የሕፃናት የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔዎች (ኒኣ ያንፅ) ናቸው፡፡ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔው በአምስት ክፍሎች የተመደበው ሟች በብሔረሰቡ ዘንድ ባለው ማህበራዊ ደረጃ፣ፆታ እና ከሟች እድሜ አንፃር ነው፡፡

ሟች በብሔረሰቡ ዘንድ ያለው ማህበራዊ ደረጃ ሲባል በብሔረሰቡ ዘንድ ያለው የስራ ድርሻን ይመለከታል፡፡ ስራውም የእምነት መሪ፣ የአካባቢ አስተዳዳሪና የሐገር ሽማግሌ ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህን ስራዎች መሰረት በማድረግም የእምነት መሪዎች ሲሞቱ የባለቃልቻዎች የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ፤ የአካባቢ አስተዳዳሪዎች እና የሐገር ሽማግሌዎች ሲሞቱ ደግሞ የባለሚያንግ (ንጉስ ወይም "ቲያት") የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ተብሎ ይጠራል፡፡

ሁለተኛው የመክፈያ መንገድ ደግሞ የሟች እድሜ ነው፡፡ በአብዛኛው ልጅ ወልደው ጨርሰው እና ሀብት ንብረት አፍርተው በእርጅና ምክንያት እድሜያቸው ከ60 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ሲሞቱ የሚደረገውን ክዋኔ የእድሜ ባለፀጎች የለቅሶ ስርዓት ይባላል፡፡ ለአቅመ አዳምም ሆነ ሔዋን ደርሰው እንዲሁም በጋብቻ ተሳስረው ነገር ግን ሳይወልዱ ለሚሞቱት የሚደረገውን የወጣቶች የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ሲሉት፤ ሕፃናት ሲሞቱ የሚደረገውን የለቅሶ ክዋኔ ደግሞ የሕፃናት የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ በማለት ይጠሩታል፡፡

የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ እንደ ሟቹ አይነት ይለያያል፡፡ ከዚህ በመቀጠል በቃለ መጠይቅ፣ በምልከታ እና በተተኳሪ የቡድን ውይይት ጊዜያት የተሰበሰቡ መረጃዎችን በእያንዳንዱ የለቅሶ ስርዓት አይነት በመተንተን አሳያለሁ፡፡

## 4.1 የባለቃልቻዎች የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ

ባለቃልቻ (ሲ.ያቲ) ማለት መንፈስ[2] ያደረበት ሰው ነው። በሙያውም እንደ እምነት መሪ ተደርጎ ይወሰዳል። ባለቃልቻ የሆነ ሰው በቤንች ብሔረሰብ ዘንድ ትልቅ ቦታ አለው። ዝናብ ያዘንባል ወይም ያቆማል፤ ፀሐይ እንድትወጣ ወይም እንድትገባ ያደርጋል፤ ድርቅ እንዲከሰት ወይም እንዲጠፋ ያደርጋል፤ በአጠቃላይ የተናገረው ይደርሳል፤ ብለው ያምናሉ። እንደ አቶ ክፍሌ ለማ ገለፃ ‹‹ሰው የመግደል ወይም የማዳን፣ ሐብት እንዲበዛ ወይም እንዲጠፋ የማድረግ፤ ባጭሩ የፈጣሪን ሚናን የመጫወት ኃይል እንዳለው በብሔረሰቡ ዘንድ ይታመናል›› (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣07/2005)።

በብሔረሰቡ ዘንድ እንዲህ አይነት ሚና የሚሰጠው ሰው ከፍ ሲል እደጠቀስኩት ባለቃልቻ (ሲ.ያቲ) ይባላል። ይህ ሰው በሕይወት ዘመኑ ሐገሪቱን እንዳይረግም ተብሎ በእንክብካቤ እንዲኖር ይደረጋል። ከሞተ ደግሞ ስርዓተ ክዋኔው የተለየ ነው። ብዙ ዝግጅቶችን ይጠይቃል። ስፊ ጊዜንም ይፈልጋል። ምክንያቱ ደግሞ ባለቃልቻው በሚሞትበት ጊዜ መሞቱን ተከትሎ በብሔረሰቡ ዘንድ ብዙ አሉታዊ ጉዳዮች ይደርሳሉ፤ ተብሎ ስለሚታሰብ ነው።

ቀጥየ በባለቃልቻዎች የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ከቀብር በፊት፣ በቀብር ጊዜ እና ከቀብር በኋላ የሚደረገውን እተነትናለሁ።

### 4.1.1 ከቀብር በፊት

በቤንች ብሔረሰብ ዘንድ አንድ ባለቃልቻ ከመሞቱ በፊት በሕይወት ዘመኑ እንደ ሰራተኛ ሆነው የሚያገለግሉት ሰዎች አሉ። በብሔረሰቡ ቋንቋም ‹‹ቆንብ›› ይባላሉ። እነዚህ ጠባቂዎች (ቆንብ) እስከ ባለቃልቻው ሕይወት ህልፈት ድረስ አብረው ይኖራሉ። ጠባቂዎችም ባለውቃቢው በሕይወት ዘመኑ የማይመገባቸውን ምግቦች የማይመገቡ፣ የማይጠጣቸውን መጠጦች የማይጠጡ፣ የባለውቃቢ ወይም የውቃቢ እምነት ተከታዮች የሆኑ፣ ያላገቡ፣ ሴቶች ከሆኑ ደግሞ የወር አበባ ያላዩ፣ ለአቅመ ሔዋን ያልደረሱ፣ ለቅሶ ቤት ደርሰው የማያውቁ መሆን ይኖርባቸዋል። ይህ የሚሆንበትን ምክንያት አቶ ግርማ የተባሉ መረጃ አቀባይ እንደሚከተለው ይገልፁታል።

---

[2]መንፈስ ሲባል ሁሉን ነገር ያውቃል ብለው ብሔረሰቡ የሚስማሙበት ረቂቅ ነገር ነው። መንፈሱ ያደረበት ሰው ባለቃልቻ ይባላል። ይህ ባለቃልቻ ደግሞ ከሌሎች የተለየ፣ አዋቂ፣ ወዘተ. አድርገው ይቆጥሩታል።

*ሰውየው ላይ ያለው ውቃቢ (መንፈስ) ማንኛውም ሰው ገብቶ እንዲያስታምመው እንዲጠብቀው ስለማይፈቅድ ነው። ባለውቃቢውም ሆነ ጠባቂዎች (ቆንብ) በግና ዶሮ አይመገቡም። ለቅሶ ቤት አይሄዱም። የወለደች ሴት አይጠይቁም፤ ሴቶች የወር አበባ ያላዩ መሆን አለባቸው። እነዚህን ነገሮች ፈፅመው ባለቃልቻው ግቢ ውስጥ ከገቡ ውቃቢው (መንፈሱ) ይገላቸዋል፤ እንዲታመሙ ያደርጋል፤ ሐብት ንብረታቸው እንዲጠፋ ይሆናል ተብሎ ይታሰባል። (ቃለመጠይቅ፣ ጥር 05/2005)*

በተያያዘም አቶ አቤል የተባሉ መረጃ አቀባይ ‹‹በዶሮ ስጋ፣ በዶሮ እንቁላል፣ በበግ ወዘተ. ላይ ምንጊዜም ቢሆን ለውቃቢው የማይስማሙ ሌላ መንፈስ አለ። ስለዚህ ሁለቱ ተቃራኒ የሆኑ መንፈሶች ተስማምተው መኖር ስለማይችሉ አንዱ አንዱን ለማሸነፍ ሲባል የበላውን ሰው ሊገሉት ወይም ሊያሳምሙት ይችላሉ፤ እነዚህን የተመገበ ደግሞ ውቃቢው ይፈርስበታል›› በማለት ይገልፃሉ። (ቃለመጠይቅ፣ ጥር 07/2005)

ባለቃልቻው እንደሞተ ወዲያውኑ አይለቀስም። መታመሙንም ሆነ መሞቱን ከጠባቂዎች (ቆንብ) ውጭ የሚያውቅ የለም። ባለቃልቻው ወዲያውኑ እንደሞተ የማይለቀስበት ምክንያት ስርዓቱ ብዙ ጊዜ የሚወስድ በመሆኑና የባለቃልቻው ውቃቢ (መንፈስ) ከሟች ዘመድ በአንዱ እንዲገባና ስልጣኑን እንዲረከብ የፀሎት (የልመና) ስርዓት ስለሚደረግ መሆኑን በቡድን ውይይት ጊዜ (አቶ አቤል፣ አቶ አለማየሁ እና አቶ ክፍሌ፣ የካቲት 16/2005) ገልጸውልኛል።

የባለቃልቻው ነፍስ እንደወጣች ቆንቦች በሙሉ ከባለቃልቻው ቤት ተሰብስበው አስከሬኑን ይጠብቃሉ። ከዚያም ጠባቂዎች ወዲያውኑ በሟች አንገት ላይ ያለውን የቃልቻ ጨሌ (ካህኩል)፣ ጥፍሩን (ፀንግ) እና ፀጉሩን (ፎህ) ነቅለው አንድ ላይ ያስቀምጣሉ። ይህ የሚሆንበት ምክንያት መንፈሱ (ውቃቢው) የሚያርፈው በእነዚህ ላይ ነው፤ ተብሎ ስለሚታሰብ መሆኑን ቄስ ሳሙኤል፣ አቶ ክፍሌ እና አቶ አለማየሁ የተባሉ መረጃ አቀባዮች ይገልፃሉ። (የቡድን ውይይት፣ የካቲት 16/2005)። እነዚህ ነገሮች ከባለውቃቢው ተለይተው ካልቀሩ ውቃቢው ወደ ሌሎች ሰዎች እንዲተላለፍ ሲለመን በቀላሉ አይተላለፍም ተብሎ ስለሚታሰብ ነው። በአብዛኛው ውቃቢው ጨሌ እንደሚወድ፣ ከባለውቃቢው የቀኝ እጅ ጥፍር ተደብቆ እንደሚኖር እና ከባለ ውቃቢው አናት ላይ በመሆን ህዝቡን እንደሚጠብቅ ከላይ የጠቀስኳቸው መረጃ አቀባዮች አያይዘው ገልፀውልኛል።

እነዚህ ነገሮች (ጨሌ፣ የእጅ ጥፍር እና የራስ ፀጉር) ከባለቃልቻው ተለይተው ካልቀሩ ውቃቢው በሚለመንበት ጊዜ ወደ ሌላው ሰው በቀላሉ ሲለመን አይገባም፤ ወይም አይተላለፍም። አብረው

ከተቀበሩ ደግሞ በብሔረሰቡ፣ በእንስሳት፣ በአዝመራ እንዲሁም በሐገር ላይ ሰላም ይጠፋል፤ የታመመ አይድንም፤ የተዘራ አይበቅልም፣ የተወለደ አያድግም ወዘተ. ተብሎ ይታመናል (ቄስ ሳሙኤል፣ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 18/ 2005)፡፡

የባለቃልቻው ጨሌ፣ ጥፍር እና ፀጉር አንድ ላይ ከተቀመጠ በኋላ የቃልቻው መግቢያ በር (ፓርት) ይዘጋል፡፡ ባለቃልቻው በሕይወት ዘመኑ ሁለት በሮች ይዘጋጁለታል፡፡ አንደኛው ወደ ቤቱ የሚገባበት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ መውጫ በር ነው፡፡ በብሔረሰቡ ዘንድ ባለቃልቻ በገባበት በር አይወጣም፡፡ ‹‹ወደ ፊት እንጂ ወደ ኋላ መመለስ የለበትም አንዴ ከተናገረም የሚለወጥ ጉዳይ የለም፡፡ ቀጥ ብሎ መጓዝ እንዳለበት የሚያሳይ መሆኑን አቶ ተሾመ ገልፀዋል (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት 23/2005)፡፡

መግቢያ በሩ የሚዘጋበት ምክንያት ከመካከላቸው ብሔረሰቡ የማይፈልጉት ሰው ውቃቢው ይዞት የቃልቻ ቤት ውስጥ እንዳይገባ ለመከላከል ነው፡፡ በአብዛኛው በብሔረሰቡ ዘንድ የባለቃልቻውን ቦታ ተክቶ እንዲሰራ የሚፈለገው የሟች የመጀመሪያ (በኩር) ወንድ ልጅ ወይም አጎት ነው፡፡ የሟች የመጀመሪያ ልጅ ሴት ከሆነች የሟች አጎት ላይ ውቃቢው እንዲሰፍር ይለመናል፡፡ ሴቶች የማይወርሱበትን ምክንያት አቶ አቤል "…መንፈሱ አይፈልጋቸውም፤ የእምነት መሪ የመሆን አቅም አይኖራቸውም፤ መንፈሱም ቢሆን ሴቶችን አይፈልግም" ሲሉ ገልጸውልኛል (ቃለ መጠይቅ፣ጥር 07/2005)፡፡ ከእነዚህ ከሁለቱ ሰዎች ውቃቢው ካልሰፈረ ሟች ሳይቀበር እስከ አራት ቀናት ድረስ ይለመናል፡፡ የሚለምኑትም የሟች ጠባቂዎች፣ በአካባቢው ያሉ ባለውቃቢዎች እና ሽማግሌዎች ናቸው፡፡ እንዲህ እየተባለ በግጥም[3] ይለመናል፡፡

| <u>ቤንችኛ</u> | <u>አማርኛ</u> |
|---|---|
| ዋኦዬ ሽዶ ባኦቦ | የህዝብ አባት |
| ዋ ጋለ ባያቦ | የብዙሃን አባት |
| ዋ ነባኮንሳ አምሽንዬ | እኛን ጥለህ አትሂድ |
| ምንተ ዶኪ ባይብ | የላሟ አባት |

[3] በዚህ ጥናት በምዕራፍ ሦስት ለመግለፅ እንደሞከርኩት የቤንችኛ ቋንቋ ዜማዊ (tonal language) ነው፡፡ በመሆኑም ግጥሞቹ ቤት የሚመቱት እንደ አማርኛ ቋንቋ በስንኞች መጨረሻ ሳይሆን በመጀመሪያው ላይ ነው፡፡ በተጨማሪም ቋንቋው የራሱ የሆኑ ፊደላት ስለሌሉት እና ገና በመቀረፅ ላይ ስለሆነ አንዳንድ ድምፆችን ወደ አማርኛ ቀይሮ አቻ ለማግኘት አይቻልም፡፡ ስለዚህ ዋና ትኩረት የማደርገው ይዘታቸው ላይ ይሆናል፡፡ አቻ ድምፅ ያላቸውን ደግሞ በግጥም መልክ ለመቀየር ወይም ለመተርጎም ተሞክሯል፡፡

እንት የኤንት ቦክንስ አምሸንዳ
እንተ ኤንት ፀክካን እስተ ቦክንሳ አመሸንዳ
አዶወ ተመተም ተአደንተም
ተወርሞ ተገማም ተንቆለሰዌ

ትውልድህን ጥለህ አትሂድ
የአንተባሪያ(ደህ) ነን ጥለህ አትሂድ
በትውልድ ውስጥ አትጥፋብን
በበሬ በላሜ ለምኘሀለሁ አትሂድ

የግጥሙ ትኩረት ውቃቢው ወይም መንፈሱ ላይ ነው፡፡ ውቃቢው በብሔረሰቡ ላይ ምን ያህል ቦታ እንዳለው ከግጥሙ መረዳት ይቻላል፡፡ ውቃቢው ለብሔረሰቡ አባት፣ መሪው፣ ጠባቂው፣ የመኖሩ ዋስትና ሲሆን ብሔረሰቡ ወይም ህዝቡ ደግሞ ለዚህ መንፈስ ተገዥ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ በቤንች ብሔረሰብ ዘንድ ላም ለመስዋዕት የተመረጠች እንስሳ ናት፡፡ መንፈሱም በቀላሉ ከሟች ወደ ሌላው ሰው እንዳይተላለፍ ይህችን ለመስዋዕት የተፈቀደች እንስሳ ይሳሉለታል፡፡

ይህ ክዋኔ እስከሚከወን ድረስ ሟችን ከሚጠብቁት ጠባቂዎች (ቆንብ) በስተቀር ባለቃልቻው መሞቱን ቤተሰቦቹም ሆኑ ሌሎች ሰዎች አያውቁም፡፡ የባለቃልቻው መኖሪያ ቤት ለብቻው ከቤተሰቡ ተነጥሎ የተሰራ ስለሆነ ይህንን ስርዓት በሚያደርጉበት ጊዜ የሟች ቤተሰቦች አይሰሙም፡፡ ባለቃልቻው መሞቱን ሌሎች እንዳይሰሙ የሚደረግበትን ምክንያት አቶ መኮንን እንደሚከተለው ይገልፁታል፡፡ “አስክሬኑ ከመቀበሩ በፊት ብዙ ስርዓቶች ስለሚደረጉ ስርዓቱን ላለመረበሽ ነው፡፡ የቅርብ ሰዎች (ቤተሰቦች) እንዳይሰሙ የሚደረገው፡፡ መሞቱን ከሰሙ ስርዓቱ ሳያልቅ ያለቅሳሉ፡፡ ከዚያም ጎረቤት ተሰብስቦ ትልቅ ለቅሶ ይሆናል፡፡ ከተለቀሰ ደግሞ ውቃቢው በቀላሉ ወደሚፈለገው ሰው ሊገባ ወይም ሊተላለፍ አይችልም፡፡” (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት 23/2005)

ከአራተኛው ቀን በኋላ መልዕክተኞች ተመርጠው ሩቅ ላሉ ዘመዶች መሞቱን እንዲነግሩ ይደረጋል፡፡ መልዕክተኞችም ባለቃልቻው ቀኋል እንጂ አርፏል ወይም ሙቷል አይሉም፡፡ በብሔረሰቡ ቋንቋ ‹‹ኢሲ ቃላም›› ድረሱ ይባላል፡፡ ሙቷል የማይባልበት ምክንያት በብሔረሰቡ ዘንድ ባለውቃቢው ሞትን ያሸንፋል እንጂ እሱ አይሞትም፤ የተለየ ሰው ነው፤ የሁሉም የበላይ ነው ተብሎ ስለሚታሰብ መሆኑን ቄስ ሳሙኤል ገልጸውልኛል፡፡ (ቃለመጠይቅ ጥር፣18/2005)

ሌሎች ቀሪ ጠባቂዎች (ቆንብ) ደግሞ የባለቃልቻውን ግቢ እና አጥር[4] ያፀዳሉ፣ አጥሩን ይቀይራሉ፤ ቤቱ ያረጀ ከሆነ በአዲስ ይተካሉ፡፡ ይህንን ክንውን በሚያደርጉበት ጊዜ ባለቃልቻው

---

[4] የባለውቃቢው መኖሪያ ግቢ አምስት አጥሮች አሉት፡፡ የመጀመሪያው (ከውጭ በኩል) ያለው ባለውቃቢውን ፈልገው የሚመጡ አናሳ ጎሳዎች (መንጃዎች) እና ከሥጋ ዘመድ ጋር ግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈፀሙ (ሹታን) ሰዎች

መሞቱን ቤተሰቡም ሆኑ ሌሎች ሰዎች ይጠረጥራሉ፡፡ የቤቱ ክዳን በአዲስ የሚተካበት፣ ግቢው የሚፀዳበት እና አጥሮች የሚቀየሩበት ምክንያት ‹‹የሟችን (የባለውቃቢውን) ገመና ለቅሶ ለመድረስ የሚመጡ ሰዎች እንዳያዩት ነው›› በማለት አቶ ክፍሌ ገልጸውልኛል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 07/2005)

በባለቃልቻው የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ በጣም ከባዱና ረዘም ያለውን ጊዜ የሚወስደው የውቃቢው (የመንፈሱ) ከሟች ወደ በኩር ልጅ ወይም አጎት እንዲተላለፍ የሚደረገው ስርዓት ነው፡፡ የባለቃልቻው ውቃቢ (መንፈስ) በቀላሉ ከሚፈለገው ሰው ላይ አያርፍም፡፡ ብዙ ልመናን የሚጠይቅ ነው፡፡ አቶ ተሾመ በቃለ መጠይቅ ጊዜ ይህንን ስርዓት እንደሚከተለው ገልጸውልኛል፡፡

> *… እንዲህ እየተባለ[5] እስከ አራት ቀን ተለምኖ ውቃቢው ካልመጣ የሟቹ ጥፍር፣ ከአንገቱ ላይ ያለው ጨሌ፣ እና የራስ ፀጉር ተነቅሎ በአንድ ላይ በማድረግ የማር ቀፎ ላይ ይሰቀላል፡፡ ውቃቢው ማር ይወዳል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡ ይህ ተደርጎ ባለውቃቢው በሌላ ሰው ላይ ካላረፈ ለምንድነው ያላረፈው ተብሎ በአካባቢው ካለ ሌላ ባለቃልቻ እንዲጠየቅ ሽማግሌዎች ይላካሉ፡፡ መልዕክተኛ የተላከበት ባለውቃቢም በቤታችሁ ውስጥ ችግር ስላለ ነው መንፈሱ ሌላ ሰው ላይ ያላረፈው ይላል፡፡ ከዚያም መንፈሱ ተለምኖ አልሰፍርም ያለበት ቦታ ላይ ጠባቂዎች (ቆንቦች) ላም፣ ጥጃ እና ሴት ልጅ ይሳሉለታል፡፡ ሴት ልጅ የሚሳሉት ትዳር በምትይዝበት ጊዜ ባሏ የሚሰጣትን ላሞች ለተመረጠው ባለውቃቢ እንድትሰጥ ነው፡፡ (የካቲት 23/2005)*

ከዚያም አሁንም ውቃቢው ከሟች ወደ በኩር ልጅ ወይም አጎት ሊተላለፍ ወይም ላይተላለፍ ይችላል፡፡ ውቃቢው ካረፈ ያረፈበት ሰው በዛር መንፈስ ይለፈልፋል፤ ያወራል፤ ያጎራል፡፡ ይህ መንፈስ ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ በአካባቢው የሚገኝ ሌላ ባለውቃቢ ተጠርቶ በዛር መንፈስ (ሁለቱን ብቻ የሚያግባባ ቋንቋ) እንዲያወሩ ይደረጋል፡፡ አዲሱን ባለቃልቻ የያዘው መንፈስ ትክክለኛ ከሆነ ተጠርቶ የመጣው ባለውቃቢ ትክክለኛ ነው ብሎ ለተሰበሰቡት ሽማግሌዎች ይነግራል፡፡ ውቃቢው ትክክለኛ ካልሆነ ደግሞ ከቤተሰቡ አባላት በማስተዳደር ብቃቱ ቤተሰቡና አካባቢው ያመነበት ሰው ተመርጦ የሟች (የባለቃልቻውን) የሥራ ድርሻ ተረክቦ እንዲቀይ ይደረጋል፡፡

---

የሚቆሙበት (የሚያርፉበት) ክፍል ነው፡፡ ሁለተኛው አጥር ‹‹ፔሽ ፓርት›› ዘበኛ ያለበት ሲሆን እንግዶችና ባለ ጉዳዮች ባለውቃቢው በህይወት ዘመኑ ባለበት ጊዜ ስጦታና መልዕክት የሚሰጡበት ግቢ ነው፡፡ ሦስተኛው አጥር ዳኝነት የሚሰጥበት (ባለውቃቢው የባላባትነትን ሙያ ደርቦ የያዘ ከሆነ) እና የተለያዩ ስርዓቶች (ክብረበዓላት)ና ስራዎች የሚከናወኑበት ግቢ ነው፡፡ አራተኛው አጥር ግቢ ውስጥ ደግሞ የባለቃልቻው መኖሪያ ቤት ያለበት ነው፡፡ አምስተኛው ወይም የመጨረሻው መሃከል ላይ ያለው አጥር ግቢ ደግሞ ከባለቃልቻው አገልጋዮችና መስዋዕት አቅራቢዎች በስተቀረ ማንም ሰው እንዲገባ የማይፈቀድበት ክፍል ነው፡፡

[5] በገፅ 44-5 ላይ ያለውን ግጥም ለመግለፅ

ይህ የተመረጠው ሰው በአብዛኛው የሟች የበኩር ወንድ ልጅ ነው የሚሆነው፡፡ የበኩር ልጅ የሚመረጥበት ምክንያት ይህ ልጅ ብዙዎችን ሥራዎች ከአባቱ (ከሟች) ጋር የቅርብ ግንኙነት ስላለው እና አባቱ ምን ምን ሁኔታዎችን ሲያደርግ እንደነበር በቅርብ ሆኖ ሲከታተል የነበረ ስለሆነ በቀላሉ የአባቱን ሚና ያከናውናል ተብሎ ስለሚታሰብ መሆኑን በቡድን ውይይት ጊዜ ቄስ ሳሙኤል፣ አቶ ክፍሌ እና አቶ አለማየሁ የተባሉ መረጃ አቀባዮች ገልጸውልኛል፡፡ (የካቲት 16/2005)፡፡

ይህ የተመረጠው አዲሱ ባለውቃቢም አዲስ ቤት እንዲሰራለት ይደረጋል፡፡ ከአዲስ ቤት መሰራቱ በተጨማሪም አዲስ ሚስት እንዲያገባ ይደረጋል፡፡ ይህንን የሚያደርገው ግን በፊት የነበረችውን ሚስት ፈትቶ ሳይሆን በተጨማሪነት ነው፡፡ ይህ ክዋኔ ከተፈፀመ በኋላ ስርዓቱን ሲያስፈፅሙ የነበሩት ሽማግሌዎች፣ የአካባቢ ታዋቂ ባለውቃቢዎች እና ጠባቂዎች (ቆንብ) ለቤተሰቦቹ (ለሟች) ኑ በድናችሁን ውሰዱ ተብሎ ለቀብር እንዲዘጋጅ ያደርጋሉ፡፡

### 4.1.2 በቀብር ጊዜ

አንድ ባለቃልቻ ከመቀበሩ በፊት የተለያዩ ክዋኔዎችን እንደሚፈፀሙ በ (4.1.1) ንዑስ ርዕስ ለመግለፅ ተሞክሯል፡፡ እነዚህ ክዋኔዎች ከተጠናቀቁ በኋላ ደግሞ አስከሬኑ ለቀብር ይዘጋጃል፡፡ የመጀመሪያው ስርዓትም የእጥበት ሥርዓትና የመቃብር ቦታ ቁፋሮ ናቸው፡፡ በቤንች ብሔረሰብ ዘንድ አንድ ሰው እንደሞተ የሚኖረውን ሥርዓት አቶ አቤልና አቶ አለማየሁ እንደሚከተለው ይገልፁታል፡፡ “ሰው እንደሞተ የእጥበት ስርዓት ይደረጋል፡፡ የሚያጥቡት ሰዎችም እንደ ሟቹ አይነት ይለያያል፡፡ ለምሳሌ ባለውቃቢ ከሞተ ቆንብ (ጠባቂዎች) ከሽማግሌዎች ጋር በመሆን ያጥባሉ፡፡ ለማጠቢያነትም የባህር ዛፍ ቅጠልና ሳሙና ይጠቀማሉ፤ የባህር ዛፍ ቅጠል አስከሬኑ ጠረኑ እንዳይቀይር ያደርጋል” (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 07/2005)፡፡

የእጥበት ስርዓቱ ከተከናወነ በኋላ አስከሬኑ በሳጥን[6] ይቀመጣል፡፡ ከዚያም ጥይት ይተኮሳል፡፡ ጥይቱን ተከትሎ ደግሞ ከበሮ ይመታል፡፡ ይህ በሚደረግበት ጊዜ በአካባቢው ሰው መሞቱን በመረዳት የአካባቢ ሰዎች ከበሮ ወደተመታበት እና ጥይት ወደተተኮሰበት ቦታ ይሔዳሉ፡፡ ይህንን በተመለከተ አቶ መኮንን የተባሉ መረጃ አቀባይ እንዲህ ይላሉ፡፡

---

[6] ሳጥኑ የሚዘጋጀው በአብዛኛው ከዋንዛ፣ ከጥድ እና ከዝግባ እንጨቶች ነው፡፡ የሚያዘጋጁትም ‹‹መንጃ›› የተባሉ በዞኑ ውስጥ የሚኖሩ ጎሳዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ዛፎች መሬት ውስጥ በሚቀበሩበት ጊዜ በቀላሉ እንደ ማይበሰብሱ መረጃ አቀባዮች ይገልፃሉ፡፡

*... የከበሮን መመታትና የጥይት መተኮስን አስመልክቶ የሰማነው ሰዎች በሙሉ ተሰብስበን እንሔዳለን፡፡ የከበሮው ድምፅ ሰው መሞቱን የሚያመለክት ስለሆነ፣ ጦር (ማይት) ፣ ከበሮ (ቲያርብ) ፣ ጋሻ (ጎዝ) ፣ ጥሩምባና ዲንክ (የእስትንፋስ መሳሪያዎች) የመሳሰሉትን በመያዝ እንሔዳለን፡፡ ከዚያም ትላልቅ ሰዎች ለብቻ አንድ ላይ ክብ ሰርተው ይጨፍራሉ፡፡ ሴቶች ደግሞ ለብቻ አንድ አካባቢ በመሆን ሽማግሌዎች ሲጨፍሩ በእልልታ ለቅሶውን ያደምቃሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት፣ 23/2005)*

በቤንች ብሔረሰብ ዘንድ ሰው መሞቱን ለማሳወቅ የሚመታው ከበሮ ከሌሎች ከበሮዎች (ለሰርግ ወይም ለሌላ ጉዳዮች) አገልግሎት ከሚውሉት ይለያል፡፡ በመጠኑ በጣም ትልቅ የሆነ ሲመቱት የተለየ ድምፅ የሚያወጣ ነው፡፡ ብሔረሰቡ የዚህን ከበሮ ድምፅ ሲሰማ በአካባቢው ሰው መሞቱን ይረዳል፡፡ ሁሉም ሰዎች ይህንን ከበሮ አይመቱም፡፡ በአብዛኛው ትላልቅ ሽማግሌዎች ናቸው የሚመቱት፡፡ ምክንያቱ ደግሞ "ከበሮ አመታቱ ጥንቃቄን የሚጠይቅ ስለሆነና የለቅሶ ጥሪ መሆኑን ለመግለፅ አመታቱን የሚችሉት ሽማግሌዎች" መሆናቸውን አቶ ናፒ ኮይስቲ (የካቲት፣17/2005) ገልጸውልኛል፡፡ ሌላው በለቅሶ ጊዜ ጋሻ እና ጦር ተይዞ የሚለቀስበት ምክንያት የሟችን ጀግንነት ለመመስከር እንደሆነ አቶ መኮንን ይገልፃሉ፡፡

ይህ አከዋወን (ጋሻና ጦር ተይዞ የሚከወነው) የተጀመረው ከአድዋ ጦርነት በኋላ ጀምሮ መሆኑን በቡድን ውይይት ጊዜ መረጃ አቀባዮቹ ገልፀውልኛል፡፡ ከዚያ በፊት ግን በለቅሶ ጊዜ ጦር እና ጋሻ ተይዘው እንደማያውቁ (አቶ አቤል፣ አቶ ክፍሌ እና አቶ አለማየሁ የካቲት 16/2005) ገልጸውልኛል፡፡ ሟቹ (ቿ) እሱ ወይም እሷ በኢትዮ - ጣሊያን ጦርነት ጊዜ ባይኖሩም የእነሱ ዘሮች ስለነበሩ የጀግና ዘሮች ናቸው፡፡ ጣሊያንን በጦር ተዋግተው አሸንፈዋል፡፡ ስለዚህ ጦር ሊሰበቅባቸው ጋሻ ሊመታላቸው ይገባል፤ የሚል ትርጉም እንዳለው አቶ አቤል የተባሉ መረጃ አቀባይ ይገልፃሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 07/2005)፡፡

እነዚህ ቁሶችን ይዞ ለቅሶን መከወን አንዳች ነገር ለትውልድ ለማስተላለፍ ያሰቡ ይመስላል፡፡ ይህን የታሪክ ተሳታፊነትን ለመግለፅ የሚገለገሉበት ይመስላል፡፡ በቤንች ለቅሶ ክዋኔዎች ላይ ብሔረሰቡ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ጉልህ ሚና እንደነበራቸው የሚያስገነዝቡ ሁኔታዎችን እናገኛለን፡፡ ከእነዚህም መካከል ቁሳዊ ባህሎች ዋና አስረጅዎች ናቸው፡፡ ከፍ ሲል እና ወደፊትም በምጠቅሳቸው የለቅሶ ክዋኔ አይነቶች በለቅሶ ጊዜ የሚታዩት ቁሶች (ጦር፣ ጋሻ፣ ጠመንጃ፣ ጎራዴ፣ ቶሀ፣ጥሩምባ፣ ፍርግን ወዘተ.) ለቅሶውን ከማድመቅ ያለፈ የሚነግሩን ታሪክ አለ፡፡ ይህም ታሪክ ወንዶች በጦር፣ በጋሻና በጠመንጃ የኢጣሊያን ሰራዊት እንደተዋጉ፤ ሴቶች ደግሞ

በተለያዩ የስትንፋስ መሳሪያዎች በመታገዝ ከወንዶች ባልተናነሰ መንገድ ወንዶቻቸውን በዘፈን ሲያበረታቱ እንደነበር የብሄረሰቡ አባላት ይስማማሉ።

በአመት አንድ ጊዜ በሀገር አቀፍ ደረጃ የምናስበው የአድዋ ጦርነት ድል ዋና ሚናው ታሪክን ለመዘከር እና ለትውልድ ለማስተላለፍ ሊሆን ይችላል። ሁሉም የሀገራችን ብሔረሰቦች የዚህ ታሪክ ተቋዳሾች ናቸው። ይህንን የታሪክ ተቋዳሽነታቸውን በለቅሶ አማካይነት ከትውልድ ትውልድ እንዲተላለፍ ከሚያደርጉ ብሔረሰቦች መካከል ቤንቾች ተጠቃሾች ናቸው።

ይህን ሀሳብ ለማጉላት ወይም ለማጠናከር የማነሳው ጉዳይ፤ ከአድዋ ጦርነት በፊት የቤንች የለቅሶ ስርዓት በጦርና በጋሻ እንዲሁም በጠመንጃ ታግዘው ያለመከወናቸው ሚስጥር እና ከአድዋ ጦርነት በኋላ እነዚህ ቁሶች ለለቅሶ መከወኛነት ብሔረሰቡ መገልገሉ በቁሶቹ አማካይነት ሊያስተላልፈው የፈለገው መልዕክት እንዳለ እንረዳለን። ይህም መልዕክት ከፍ ሲል እንደጠቀስኩት ለተተኪው ትውልድ የአድዋን ጦርነት ታሪክ ለመንገር፤ እንዲሁም ብሔረሰቡ በጦርነቱ ወቅት የታሪክ ተሳታፊ መሆኑን ለመዘከር እንደሆነ መረዳት ይቻላል። ስለዚህ ቁሶቹ ከቁስነታቸው ባለፈ በውስጣቸው ሰፋ ያለ ሀሳቦችን ይዘው እንደሚገኙ እና ብሔረሰቡ ይሁነኝ ብሎ በክዋኔው ውስጥ አካቶ የሚከውኗቸው መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል።

እንደ አቶ አለማየሁ አገላለፅ ደግሞ ትላልቅ ሰዎች ለብቻ አንድ ላይ ክብ ሰርተው የሚጨፍሩት ምክንያት ከሌለው በእድሜ ክልል ካሉ ሰዎች በተሻለ የሟችን ነፍስ መልካም እንዲገጥማትና ገነት እንድትገባ የማድረግ (የማማለድ) አቅም አላቸው ተብሎ ስለሚታሰብ ነው። የጭፈራው አይነት በብሔረሰቡ ቋንቋ ‹‹የሮ›› እንደሚባልና የሚጨፈረውም አስከሬን ከቤት ሲወጣ ሲል መሆኑን ገልፀዋል። (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 07/2005)።

ምስል: 1 ወንዶች ጦር ይዘው ክብ ሰርተው እየጨፈሩ የተሰማቸውን ጥልቅ ሀዘን ሲገልፁ፣ ሴቶች ደግሞ ዳር ቁመው ጭፈራውን በእልልታ ሲያጅቡ (የሮ የተባለው የጭፈራ አይነት)

ይህ ከላይ የተጠቀሰው ከዋኔ እየተከወነ እያለ አራት ሰዎች ተመርጠው የመቃብር ጉድጓድ[7] እንዲቆፍሩ ይደረጋል።

በቀብሩ ጊዜ ከርቀት የሚመጡት ሰዎች ደግሞ ለለቅሶ መከወኛ የሚጠቀሙባቸውን ቁሳቁሶች (ምግብ፣ ጦር፣ ጥሩምባ፣ ዲንክ፣ ቶህ[8]፣ ጋሻ ወዘተ) የመሳሰሉትን በመያዝ ይመጣሉ። በተጨማሪም ወንዶች ከጦሩ ጫፍ ላይ እርጥብ ሳር ያስራሉ። ይህንን የሚያደርጉበት ምክንያትም ‹‹እኛ የምንሄደው ለቅሶ ለመድረስ ነው፣ ለሰላም ነው›› የሚል ትርጉም አለው። (ቄስ ሳሙኤል፣ ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 18/2005)።

በቤንች ብሔረሰብ ዘንድ ለቅሶን በተለያዩ መንገዶች ይገልፁታል። ቤተሰቦቻቸው እየተነሱ በመውደቅ፣ አካላቸውን በስለት በማድማት፣ ግንባራቸውን በገጀራ በመቁረጥ፣ ወዘተ የተሰማቸውን ጥልቅ ሐዘን ይገልፃሉ። እነዚህን ድርጊቶች ካልፈፀሙ ለሟች አላዘኑም፣ እንዳውም በመሞቱ ደስተኞች ናቸው ተብሎ እንደሚታሰብ በቡድን ውይይት ጊዜ ለመረዳት ተችሏል። (የቡድን ውይይት፣የካቲት፣ 16/2005)።

ከርቀት የሚመጡት ሰዎችም ልክ እንደ ሟች ቤተሰቦች የተሰማቸውን ሐዘን ከሟች የቅርብ ዘመዶች ፊት በመሄድ ሦስት ጊዜ[9] በመነሳት እና በመቀመጥ ያለቅሳሉ። ሦስት ጊዜ ከተነሱና ከተቀመጡ በኋላ ለእንግዳ ማረፊያ ወደተዘጋጀላቸው ቦታ ይሔዳሉ።

የአንድን ባለቃልቻ የቀብር ስነስርዓት ማድመቂያዎች አንዱ ሟቹ በህይወት ዘመኑ ይጠቀምበት የነበረው ፈረስ ነው። ይህንን በተመለከተ አቶ አቤል እና አቶ አለማየሁ እንደሚከተለው ይገልጹታል።

> *… በድሮ ጊዜ አንድ ባለውቃቢም ሆነ ባላባት ሲሞት ከኮባ ግንድ የሰው ምስል በመቅረፅ የሟችን ልብስ፣ ቆብ፣ ጋቢ በማልበስ ሰውየው (ሟች) በአካል እንዳለ በማስመሰል ወንበር ላይ አስቀምጠው*

---

[7] የመቃብር ቦታው ከእያንዳንዱ ሟች ቤት አጠገብ ነው። እንዳውም የሟች ግቢ ውስጥ ነው ቢባል ይቀላል። የቤተሰብ መቃብር በማለትም ይጠሩታል። በእድሜ ጠገብ ዛፎች የተከበበ ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ውስጥ እንደሚቀብሩ ለመመልከት ችያለሁ።

[8] ዲንኮ እና ቶህ ከእንጨት የሚሰሩ የእስትንፋስ መሳሪያዎች ናቸው።

[9] በቤንች ብሔረሰብ ዘንድ ለቅሶ ትልቅ ማህበራዊ ጉዳይ ነው። ለቅሶ ያልደረሰ ዘመድ ቢኖር በሽማግሌ ተጠይቆ ሊቀጣ ይችላል። የሟች ዘመዶች ለሁሉም ሰዎች መልዕክት ልከው መሞቱን ካልተናገሩ እና ሰውየው ከሌላ ሰው ሰምቶ ከመጣ ለምን ለእኔ አልተላከም ብሎ ካሳ እንዲሰጠው ይጠይቃል። ስለዚህ ሶስት ጊዜ ብድግ ቁጭ እያሉ የሚከውኑት የመጣውን ሰው ለመቁጠር እንዲያመቻቸው ነው።

*ከበው ያለቅሱ ነበር። አሁን ግን ይህ ቀርቶ ፈረሱን ኮርቻ በመጫን የሟች አገልጋይ ጃንጥላ ይዞ ሰውዬው ፈረሱ ላይ እንዳለ በማስመሰልና ጥላውን በመዘርጋት ያለቅሳሉ። በፈረሱ አይን ውስጥም በርበሬ እንዲጨመር ይደረጋል። (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 07/2005)።*

በሟች ፈረስ አይን ውስጥ በርበሬ የሚጨመርበት ምክንያት እንኳን ሰው ፈረሱ እንኳ ጌታው በመሞቱ አዝኖ እያለቀሰ ነው በማለት ሰዎች በደንብ እንዲያለቅሱና እንዲጨፍሩ ለማድረግ ነው። የሰው ምስል በመቅረፅ ወንበር ላይ አስቀምጠው ሲያለቅሱ የነበሩበት ሁኔታ የቀረበት ምክንያት በአሁኑ ሰዓት የፕሮቴስታንት እምነት እየተስፋፋ ስለመጣ እና ምስሉን ጣኦት ማምለክ ነው በማለት እያስተማሩ ስለሆነ መሆኑን አቶ ኖፒ ይገልጻሉ። (ቃለመጠይቅ፣ የካቲት፣ 17/2005)።

በክዋኔው ላይም ቀጥሎ የሰፈረው ግጥም እየተዜመ እንደሚለቀስ አቶ ቡንሶ ባይባ (የካቲት 18/2005) ነግረውኛል።

| <u>ቤንችኛ</u> | <u>አማርኛ</u> |
|---|---|
| ንያጋ ፋራ የከማ (ባይስታማ) | ባባ ፈረስህ አለቀሰች |
| ታጋ ባቢ ካይጉኤ ውሳ ማካማ | ጌታየ የለም አለች |
| ንያጋ ማገታይድ ዎጣማ | ጦርህም ተደፋ |
| ይስዶንሲሾ ባአማ | የሚያነሳው አጣ |
| ንያጋ ባካሽይንድ ዎጣማ | ወንበሩም ወደቀ |
| ይስዶንሲሾ ባአማ | የሚያነሳው አጣ |
| ሾንግይ፣ ትያርብይ፣ ድንክይ ቦጋ ካንግ | ክራሩ፣ ከበሮው፣ ጥሩምባው በሙሉ |
| ከይን የካ ቦጋ ትያታይስ ኢልንያ | አምርሮ አለቀሰ ጌታውን ፈለገ |
| ሚታውስይንድ ኢስዎጥ ኢይናማ | ላሚቷም እንደሰው ዘለለች ጨፈረች |
| ውዋጋ ባብ ይስይንድ ኮይስታ ባአማ። | ጌታዋን ፈለገች ጌታዋንም አጣች። |

ባለውቃቢው በመሞቱ ሁሉም (ቁሳዊውም ሆነ ህይወት ያለው) አካላት ማዘናቸውን የሚያሳይ ግጥም ነው። ፈረስና ላም ባለቤታቸው በመሞቱ አምርረው ሲያለቅሱ፣ ጦሩ ባለቤቱ ካላነሳው አልነሳም ሲል፣ መቀመጫው ወንበሩ እንደ ሰው ሲወድቅ እና የሚመጥነኝ የለም ሲል፣ ባለውቃቢው በህይወት ዘመኑ የሚጫወትባቸው ክራር፣ ከበሮ እና ጥሩንባ ማዘናቸውን፣ ወዘተ የሚያመለክት ግጥም ነው።

ባለውቃቢው ይጠቀምበት የነበረውን ፈረስ ሌሎች ሰዎች አይገለገሉበትም፡፡ ባለቤቱ ከሞተ በኋላም ፈረሱ እንደድሮው እንክብካቤ አይደረግለትም፡፡ በዚህ የተነሳም ፈረሱ ዛሬ ምን በላ፣ ምን ጠጣ የሚለው ሰው ባለመኖሩ ያዝናል፤ የሚለውን ሀሳብ እንደሚይዝ በቡድን ውይይት ጊዜ (አቶ አቤል እና ቄስ ሳሙኤል) ገልፀውልኛል፡፡ (የካቲት 16/2005)፡፡ በተመሳሳይ የባለውቃቢው ጦር ባለውቃቢው ከሞተ በኋላ የሚገለገልበት ሰው የለም፡፡ ጦሩ የተለየና ለዚህ ማዕርግ ተብሎ የተዘጋጀ ነው፡፡ ባለውቃቢው ከሞተ በኋላ ጦሩ የሚቀመጠው ተደፍቶ (ጫፉ ወደታች ተደርጎ) ነው፡፡ ይህም የሚያመለክተው "… ባለቤቱ ስለሞተና የሚጠቀምበት ስለሌለ እንዲሁም የሚንከባከበው ስለሌለ… እንዲህ ተደርጎ እንዲቀመጥ ይደረጋል" ሲሉ (አቶ ተሾመ፣ የካቲት 14/2005) ገልጸውልኛል፡፡ እነዚህ ሀሳቦች ናቸው በለቅሶው ጊዜ በግጥም እየተዜሙ የሚከወኑት፡፡

በአብዛኛው በሁሉም በቤንች የለቅሶ አይነቶችና ክዋኔያቸው ጊዜ ሴቶችም ሆኑ ወንዶች ለየብቻ ነው የሚከውኑት፡፡ ምክንያቱ ደግሞ የወንዶች ጭፈራ በጣም ከባድ ስለሆነና ብዙ አቅምን የሚጠይቅ በመሆኑ ሴቶች ችለው አይከውኑትም ብለው ስለሚያስቡ ነው፡፡ ሴቶች ለብቻቸው በመሆን በተለይም የሟች ሚስቶች[10] እና ልጆች ሟች በህይወት ዘመኑ ይገለገልባቸው የነበረውን ልብሶች፣ የመመገቢያ ዕቃዎች፣ የጦር መሳሪያዎች ወዘተ በመያዝ ያለቅሳሉ፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ ደግሞ ለለቅሶው ድምቀት ሲባል ጥይት ይተኮሳል፡፡ በጥንት ጊዜ ሁሉም ሰው (ወንዶች) ጠመንጃ ስለነበራቸው በየትኛውም የለቅሶ ክዋኔ ላይ ጥይት ካልተኮሱ ሐዘናቸውን አልገለፁም፤ ተብሎ ይታሰብ ነበር፡፡ አሁን ግን ጠመንጃ ሁሉም ስለማይዝ ገንዘብ እየከፈሉ እንዲተኩሱ ይደረጋል፡፡ በዚህም ማዘናቸውን ይገልፃሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ አቶ ክፍሌ ‹‹ሰዎች ጥይት የሚተኩሱት ለለቅሶው ድምቀት ለመስጠት ብቻ ሳይሆን ሟቹ ጀግና ነበር ለማለት ጭምር ነው፤ ጠመንጃ እንዲይዙ ለተፈቀደላቸው ሰዎች ለአንድ ጥይት እስከ አምስት ብር በመክፈል ይተኩሳሉ›› በማለት ገልጸውልኛል፡፡ (ቃለመጠይቅ፣ ጥር፣ 07/2005)፡፡

ከርቀት ለቅሶ ለመድረስ የሚመጡ ሰዎች የየራሳቸውን ምግብ ይዘው ይመጣሉ፡፡ ለቅሶ መድረሳቸውን ሄደው ከሟች የቅርብ ዘመዶች ደርሰው በሟች የተሰማቸውን ጥልቅ ሐዘን ከገለጹ በኋላ ተመልሰው ያመጡትን ምግብ ይመገባሉ፡፡ ይህ የሚሆንበትን ምክንያት በቡድን ውይይት ጊዜ እንደተረዳሁት ‹‹… በቤንች ብሔረሰብ ባህል መሰረት ለቅሶን ለመከወን ብዙ ኃይል ይፈልጋል፡፡ ሙሉ ቀን ማልቀስን ይጠይቃል፡፡ መነሳት መውደቁ፣ አካልን መጉዳቱ፣ ክብ ሰርቶ

---

[10] የቤንች ብሔረሰብ ባላባቶች ታላላቅ መሪዎች (ቲያቶች) ከአንድ በላይ ሚስት ሊያገቡ ይችላሉ፡፡

መዞሩ፣ በጦር የሚደረገው ጭፈራ ወዘተ. በሙሉ ከፍተኛ ኃይል የሚጠይቁ ናቸው፡፡ ስለዚህ ለለቅሶው ድምቀት ለመስጠትና ሰዎች እንዳይደክሙ እየተመገቡና እያረፉ ለቅሶውን ማድመቅ አለባቸው፤ ከሚል አስተሳሰብ የመነጨ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ በዚህ የተነሳም ሁሉም ሰው ወደ ለቅሶ ቤት የሚሄደው ምግብ ይዞ ነው፡፡

ምስል: 2 ለቀስተኞች ይዘው የመጡት ምግብ ከአንድ ላይ ተሰብስቦ ሲቀመጥ

የባለቃልቻው አስከሬን ከመኖሪያ ቤቱ በሚወጣበት ጊዜ ወልዳ የመከነች ላም (ካርሸን) በራፍ ላይ ቀርባ ትታሰራለች፡፡ ከዚያም ወንዶች በትር እና ድንጋይ ይዘው እንዲደበድቧት ይደረጋል፡፡ የሟች የመጀመሪያ ልጅ ደግሞ ከእንሰት ቅጠል የተሰራ ማቶት (ፋሲኪን) ይዞ በበራፍ ላይ ይቀመጣል፡፡ ከዚያም ሬሳው ወጣ ሲል ይህ የበኩር ልጅ አስከሬኑን አራት ጊዜ ብድግ እያደረገ ለመሸከም ይሞክራል፡፡ በብሔረሰቡ ቋንቋም ‹‹ካጭ›› አደረገ ይባላል፡፡

ይህ ከላይ የተጠቀሰው ስርዓት የሚፈፀምበት ምክንያት ከብቶችንና ሌሎች የብሔረሰቡን ንብረቶች የሟች ነፍስ ይዞ ይሄዳል፤ ተብሎ በባህሉ ስለሚታሰብ ነው፡፡ ቄስ ሳሙኤል ይህንን ሐሳብ በተመለከተ የሚከተለውን ነግረውኛል፡፡ "ይህ ካልተደረገ ከብቶች ሁሉ ይሞታሉ፤ በሐገር ላይ ሰላም አይኖርም፤ መቅረብ ያለበት መስዋዕት ለሙት ነፍስ አልቀረበም፤ ይህ ሁሉ ችግር እንዳይደርስ ከብቲቱ ‹‹ውጥን ቂቲ›› (ተወግራ መሞት አለባት›› ይላሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 18/2005)፡፡

የበኩር ልጅ አራት ጊዜ የሟችን አስከሬን ለመሸከም የሚሞክርበት ምክንያት ደግሞ ‹‹ሟች ቀባሪ አለው፡፡ ቀባሪ አፍርቶ (ወልዶ) ነው የሞተው›› የሚል ትርጉም እንዳለው ቄስ ሳሙኤል አያይዘው ይገልጻሉ፡፡ እነዚህ ስርዓቶች ከተከናወኑ በኋላ አስከሬኑን አጅበው ወደ ቤተሰቡ መካነ

መቃብር ይሸኑታል፡፡ መካነ መቃብሩ ‹‹መንከር›› በመባል ይጠራል፡፡ ‹‹መንከር›› የቤንችቴት እና ሌሎች ባላባቶች (ቲያቶች) ሲሞቱ የሚቀበሩበት የቤተሰብ መቃብር ቦታ ነው፡፡ ለመመልከት እንደቻልኩት በእድሜ ጠገብ ዛፎች የተከበበ ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ነው፡፡ በሁሉም የመቃብር ቦታዎች የሚገኙ ዛፎችን መቁረጥ በጥብቅ የተከለከለ ነው፡፡ እንዳውም አንዳንድ ሰዎች እንደነገሩኝ ሰውየውን በጥይት እንደመግደል ይቆጠራል፡፡ ሰው ሲቆርጥ ቢገኝም ቆራጩን እስከ መግደል ሊያደርስ ይችላል፡፡

አስከሬኑን የሚሸከሙትም ከባለውቃቢው ጋር አብረው ይኖሩ የነበሩ ቆንቦች ናቸው፡፡ ሌሎችም ሰዎች (የእምነቱ ተከታዮች) ቢሸከሙት ምንም ችግር እንደሌላ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስለ ጉድጓድ አቆፋፈሩ ጠይቄ እንደተረዳሁትም ‹‹የባለቃልቻ መካነ መቃብር በጣም ሰፊ ነው፡፡ በግምት ከ 4-5 ሜትር ስፋት ሊኖረው ይችላል፡፡ በአራት መዓዘን መልክ ከተቆፈረ በኋላ ወደ ጎን በውስጥ በኩል እንዲሰፋ ይደረጋል፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያትም "ከሟቹ ጋር የሟቹ ንብረቶች አብረው ስለሚቀበሩ" መሆኑን አቶ ቡንሶ የተባሉ መረጃ አቀባይ ይገልፃሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት፣ 18/2005)፡፡

ባለውቃቢው ሊቀበር ሲል ወልዳ የጨረሰች ላም[11] (ካርሽን) መቃብር ጉድጓድ አካባቢ ትታረዳለች፡፡ በምትታረድበት ጊዜ ‹‹እንቧ›› የሚል ድምፅ ካወጣች ፈጣሪ (የሮስንዶ) መስዋዕትነቱን ተቀብሏል፤ የሟች ነፍስ ገነት ትገባለች ተብሎ ይታሰባል፡፡ ድምፅ ሳታወጣ ከሞተች ግን በተተኪው ባለቃልቻ ላይ ችግር ይደርሳል፤ በቤንች ብሔረሰብ ላይ ሰላም ይጠፋል፤ ድርቅ ይሆናል፤ ወዘተ. ተብሎ ይታሰባል፡፡

በቤንች ለቅሶ ክዋኔ ጊዜ የምትታረደው ላም የብሔረሰቡን እምነት ገላጭ ናት፡፡ ከለቅሶው በስተጀርባ የብሔረሰቡ እምነትም ተጠብቆ እንዲቆይ እና ከትውልድ ትውልድ እንዲተላለፍ የማድረግ አቅሙ ከፍተኛ ነው፡፡ ብሔረሰቡ ሲያምንበት የቆየውን እና እያመነበት ያለውን ልማድ ለትውልድ ለማስተላለፍ ከሚጠቀምባቸው መንገዶች አንዱ ለቅሶ ነው፡፡ እምነትን የሚገልፁ ስርዓቶች በለቅሶ ጊዜ ይፈፀማሉ፡፡ ከእነዚህ ስርዓቶች መካከልም የእርድ ስርዓት ይጠቀሳል፡፡ ይህ የእርድ ስርዓት ከብሔረሰቡ እምነትና አምልኮ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ አቶ አቤል የተባሉ መረጃ

[11] ላም ከሌሎች እንስሳት ተለይታ ለዚህ ስርዓት የተመረጠችበት ምክንያት የቤንችቴት ፈጣሪ የሆነው "የሮስንዶ" ከእንስሳት ሁሉ መርጦ ላምን (ዲያንት) ለመስዋዕትነት ፈቅዷል፤ በጥንት ጊዜም "የሮስንዶ" እንስሳት ሁሉ አምዐው ተመለከተ፡፡ ከዚያም ሁሉንም እንስሳቶች (የቤትና የዱር) አባሮ ጫካ ውስጥ እንዲኖሩ አደረገ፡፡ ከዚያም ላም የሰውን ልጅ እንድታገለግል ብሎ ከጫካ አወጣት፡፡ ፈጣሪዋ "የሮስንዶ"ም ስለሚወዳት ለመስዋዕትነት ትቀርባለች፤ የሚል ሚት ስላለ ነው፡፡

አቀባይ "በለቅሶ ጊዜ የሚታረደው እርድ ከብሔረሰቡ እምነት ስርዓት ጋር የተያያዘ ነው። የሟችን ነፍስ ለማስደሰት እና መልካም እንዲገጥማት እንዲሁም ለፈጣሪ መስዋዕት ለመስጠት ይታረዳል። ባይታረድ ደግሞ ችግር ሊደርስ ይችላል፤ የሟችን ነፍስ ፈጣሪዋ ይጠይቃታል፤ ለእኔ መስዋዕት አላቀረባችሁም ብሎ ከብቶችን ሊገድል ይችላል፤ በሰው ላይም ችግር ሊያደርስ ይችላል፤ … በጣም ስለሚታመን የግድ መደረግ አለበት" ብለውኛል። (ቃለ መጠይቅ፣ጥር 07/2005)።

ምስል፡ 3 ላሟ ከታረደች በኋላ ደሙ በፔል (በባለውቃቢው መጠጫ) ተደርጎ እንዲቀበር ይደረጋል፤ በተያያዘም ቀሪው ደም በኮባ ቅጠል ሆኖ የመቃብር ጉድጓዱ ሲረጭ

ላሟ ከታረደች በኋላ በኮባ ቅጠል እና በባለቃልቻው መጠጫ (ፔል) ደሙ ይደረጋል። ከዚያም በኮባ ቅጠል የሆነው ደም በተቆፈረው የመቃብር ጉድጓድ ላይ ይረጫል። የሚረጭበት ምክንያት ሟችን (ባለቃልቻውን) የሚፈታተነው እርኩስ መንፈስ ስላለ ከተቀበረ በኋላ የሟችን አስከሬን እንዳይረብሽ ደሙን ቀምሶ እንዲሄድ መሆኑን ቄስ ሳሙኤል ይገልፃሉ። (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 18/2005)።

በመጠጫው (ፔል) የተደረገው ደም ደግሞ ከሟቹ በራስጌ በኩል ተደርጎ ይቀበራል። የዚህ ምክንያትም ከላይ ከጠቀስኩት ጋር ተመሳሳይነት አለው። ከዚያም ላሟ እንደታረደች የላሟ ልብ እንዲወጣ ይደረግና በሟቹ አስከሬን ልብ ላይ ተደርጎ፤ የሟች ልብሶች እንዲሁ አንድ ላይ ሆነው

በላሟ (በእርጥቡ ቆዳ) አስከሬኑ ይገነዛል። ከዚያም በሳጥን ውስጥ ሆኖ በተቆፈረው ጉድጓድ አስገብተው በአፈር ያለብሱታል።

የላሟ ልብ በሟቹ አስከሬን ልብ ላይ የሚደረግበትን ምክንያት አቶ ክፍሌ እና ቄስ ሳሙኤል እንደሚከተለው ይገልፁታል።

> *…አንድ ባለቃልቻ ሲሞት የሚደረግ ደንብ ነው። ሰውዬው (ሟች) በህይወት ዘመኑ አገርን መርቋል፣ በሽታ እንዲጠፋ ለምኗል፣ አዝመራ ፍሬ እንዲያፈራ ለምኗል፣ ባጠቃላይ ሐገር ሰላም እንዲሆን ሲመረቅና ሲጠብቅ የነበረ የብሔረሰቡ ታላቅ ሰው ነው። ታላቅ የእምነት መሪ ነው። በሚሞትበት ጊዜም እነዚህ ነገሮች በሙሉ ተጠብቀው እንዲኖሩ የሟች ልብ እንዳይደርቅ (በህዝቡ ላይ እንዳያዝን) እና እረጥቦ እንዲኖር ለማድረግ የላሟን ልብ በልቡ ላይ በማድረግ በትኩስ ቆዳ ተጠቅሎ እንዲቀበር ይደረጋል። (ቃለመጠይቅ፣ ጥር፣07 እና 18/2005 በተከታታይ)*

በቡድን ውይይት ጊዜ ከመረጃ አቀባዮቹ እንደተረዳሁት ከላይ በአቶ ክፍሌ እና በቄስ ሳሙኤል የተጠቀሱት ሐሳቦች ትክክል መሆናቸውን ነው። አቶ መኮንን የተባሉ መረጃ አቀባይ አባቴ ሲያወራ ሰማሁ ብለው እንደገለፁልኝ በድሮ ጊዜ አንድ ባለቃልቻ ይሞትና (በሌላ ቦታ ሄዶ) በዚያው አካባቢ ይቀብሩታል። ከዚያም በቤንች ብሔረሰብ ላይ ረሃብ እና ድርቅ ተከሰተ። ከዚያም የሐገር ሽማግሌዎች ተሰብስበው ባለቃልቻው የት እንደተቀበረ ተጠይቆ ከተቀበረበት (ከወር በላይ) የሆነ አስከሬን አምጥተው ላም በማረድ፣ ስርዓቱ ተፈፅሞ እንደተቀበረና ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ድርቁም ጠፋ፣ ጥጋብም ሆነ… (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት፣23/2005)።

ልብሱ እና ሌሎች የሟች ንብረቶች አብረው የሚቀበሩበት[12] ምክንያትም ከአሁን በኋላ የአንተን ልብስ ማን ይለብሳል፣ የአንተን ንብረቶች ማን ይገለገልባቸዋል፣ ብለው ስለሚያስቡ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ በለቅሶ ጊዜ የሚከተለው ግጥም እየተዜመ ይለቀሳል።

| <u>ቤንችኛ</u> | <u>አማርኛ</u> |
|---|---|
| ኒያጋ ባካሽን ምባባ ኦናግያን ምባንስም | ባባ ወንበርህ ላይ ማን ይቀመጥ ከቶ |
| ኒያጋ ናቡጥይስ ምባባ ኦናግያን ኡናንስም | ባባ ጠመንጃህን ማን ይሸከም ከቶ |
| ኒያጋ ፈርይስ ምባባ ኦናግያን ጫንስም | ባባ ፈረስህን ማን ይጋልብ ከቶ |

[12] በድሮ ጊዜ በቤንች ብሔረሰብ ባህል ከሚሞቱ ታላላቅ ሰዎች ጋር ብዙ ንብረቶች አብረው ከመቀበራቸው ባሻገር ሰውም ከነህይወቱ ከሟች ጋር አብሮ ይቀበር እንደነበር ይነገራል። ከጌቶች ጋር (ከሟቾች) የምትሔዱ ተብለው ሲጠየቁ አራት ሰዎች እኔ… እኔ… እያሉ ፈቃዳቸውን ይገልፁ ነበር። ፈቃደኛ የሆነ ሰው ከጠፋም በሚስጢር አራት ሰዎች ተይዘው ከሟች ጋር ይቀበሩ ነበር። ሲቀበሩም ከሟች ራስጌ ጠጅና መጠጫ፣ ከእግርጌ ጋያና ትንባሆ (ጌትና ድንባይ) እንደተሸከሙ አፈር እንዲመለስባቸው ይደረጋል።

ኒያጋ ኩባይጣ ምባባም ሃኑሻያን ኢሽንስዎ

ምያሃቃን ይስኬንድይ ኖር ሃክንሳርኑኤ ማኬንዴ

ባባ ባንተ መጠጫ ማን ይጠጣ ከቶ

አንችልም አሉ ከሚያህ ሰው ታጥቶ፡፡

ሚችን ሊተካው የሚችል፣ ዙፋኑን ወይም ወንበሩን ሊረከብ፣ ጠመንጃውን ሊይዝ፣ ፈረሱን ሊያዝ፣ በሚች መጠጫ ሊጠጣ ወዘተ የሚችል ሰው ከሚያህ (ደቡብ ቤንች ወረዳ ውስጥ የሚገኝ ቀበሌ) ሰው የለም፤ የሚል ሀሳብ ያዘለ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትን ቁሶች ሊጠቀም የሚችል ብቁ ሰው ሊኖር አይችልም ብለው ስለሚያስቡ ከሚች አስከሬን ጋር አብረው ይቀብሯቸዋል፡፡

### 4.1.3 ከቀብር በኋላ

ባለቃልቻ በቤንች ብሔረሰብ ዘንድ ትልቅ ቦታ ስለሚሰጠው ከተቀበረ በኋላም ረዘም ያለ (እስከ 15 ቀናት) የሚደርስ እና ጊዜ የሚወስዱ ክዋኔዎች ይዘጋጃሉ፡፡ ከቀብር መልስ ሁሉም የቅርብ ዘመዶች (ሚስቶች፣ ልጆች እና መሰል ጎረቤቶች) በሙሉ ሐዘናቸውን ለመግለፅ ፀጉራቸውን ይላጫሉ፡፡ ይህንን በተመለከተ ወ/ሮ በሸቲት ዘነበ እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡፡

> *... ከቀብር መልስ እኛ ሴቶች ጥቁር ልብስ እንለብሳለን፡፡ ፀጉራችንም እንላጫለን፡፡ ወንዶች ደግሞ ጥቁር ቆብ ያደርጋሉ፡፡ ሁላችንም ጫማ አናደርግም፡፡ የቅርብ ዘመዶች ከሆን እስከ ስድስት ወር ድረስ እንለብሳለን፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ እስከ ወር ድረስ ሊለብሱ ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም ነጭ ክር አንገታችን ላይ እናስራለን፡፡ ይህንን ካላደረግን ለሚቹ አላዘኑም ተብለን እንወቀሳለን፡፡ የቅርብ ሰው ሙቶባቸው ነው እየተባለ በገቢያም ሆነ መንገድ ስንሔድ ሌሎች ሰዎች ይጠይቁናል፡፡ (ቃለመጠይቅ፣ የካቲት 21/2005)*

የብሔረሰቡ ተወላጆች ጥቁር የሚለብሱበት ምክንያት የተሰማቸውን ሐዘን ለመግለፅ ነው፡፡ ይህንን ካላደረጉ በሌሎች ዘንድ ይተቻሉ፡፡ “ለዘመዷ ወይም ለአባቷ ሞት ያላዘነች” እየተባባሉ መገለል ሊደርስባቸው ይችላል፡፡ ሌላው የእርድ ሥርዓት ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ባለቃልቻው በህይወት ዘመኑ እያለ ሐብትና ንብረት ስለሚኖረው ለቅሶ ለመድረስ ለመጡ ሰዎች ከብት ታርዶላቸው እየጨፈሩ (ሐዘንን በሚገልፅ መንገድ) ይመገባሉ፡፡ ከርቀት የመጡት ሰዎች እስከ 15 ቀን ድረስ ‹‹የሮ›› እየጨፈሩ እና እያለቀሱ ይቆያሉ፡፡ ከአስራ አምስት ቀን በኋላ ግን በአካባቢው ያሉት የሐገር ሽማግሌዎች ተነስተው በመቆም ‹‹ከአሁን ጀምሮ ማዘኑ ይብቃ፡፡ የሚች መንፈስ ሐገርን ይጠብቅ፣ ከብትን ይጠብቅ፣ ሐገር ሰላም፣ ጥጋብ፣ ልምላሜ ይሁን፣ የተወለደው ይደግ ወዘተ በማለት ከመረቁ በኋላ የለቅሶው ስርዓት ይፈፀማል፡፡ የሚች ቤተሰቦች ግን እስከ ስድስት ወር ድረስ ጥቁር ለብሰው ሀዘናቸውን ሊገልፁ ይችላሉ፡፡

## 4.2 የባላባትና የባለሚያንግ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ

በ 4.1.1 እንደገለጽኩት የቤንችን ብሔረሰብ በእምነቱ በኩል የሚያስተዳድረው ባለቃልቻው ነው፡፡ ይህ ሰው (ባለቃልቻው) የባላባትነት ሚናንም ደርቦ ሊይዝ ይችላል፡፡ ከእምነቱ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ሊመለከትና ባህላዊ ዳኝነት (ፍርድ) ሊሰጥ ይችላል፡፡

የባላባትና የባለሚያንግ የለቅሶ ስርዓት የሚባለው ደግሞ በብሔረሰቡ ዘንድ እንደ ንጉስ ለሚቆጠሩና ለሚጠሩ የቤንች ጎሳዎች ነው፡፡ ብሔረሰቡም ‹‹ቲያት›› ወይም ጌታ ብለው ይጠሯቸዋል፡፡ የእነዚህ ‹‹ቲያቶች›› ዋና *ሥራ* በምዕራፍ ሦስት በገጽ (40) እንደገለጽኩት የህዝቡ የበላይ ሆነው ህዝቡን ማስተዳደር፣ ግብር ማስገበር፣ ለተበደለ ፍርድ መስጠት፣ ወዘተ የመሳሰሉ ተግባራትን ማከናወን ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች በአካባቢው (በብሔረሰቡ) ዘንድ ከባለቃልቻውም በላይ የሚፈሩና የሚከበሩ ናቸው፡፡

በቤንች ብሔረሰብ ዘንድ ከ 70 በላይ ጎሳዎች አሉ፡፡ ሁሉም ጎሳዎች ግን የባላባት ዘር የላቸውም፡፡ የባላባት ዘር ያላቸው እንደ ቄስ ሳሙኤል አገላለፅ "ከቤንች ጎሳ ባይኬስ፣ ከሼይ ቤንች ጎሳ (ናይኬስ፣ ኮይንኬስ፣ ቶም (እያረከ) ወዘተ፣ ከሜር ጎሳ (ዛን ግንድ፣ ኮርጅ፣ ግኻርንያእ፣ ማግ፣ ቡዝንድ፣ ማችኬስ፣ ኤርስ፣ ዳርግናም፣ አራምኬስ፣ ሾሽኬስ ወዘተ ናቸው፡፡ (ቃለመጠይቅ፣ ጥር፣ 18/2005)

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሦስት ዋና ዋና ጎሳዎች (የቤንች ጎሳ፣ የሼይ ቤንች ጎሳ እና የሜር ጎሳ) በውስጣቸው በአጠቃላይ ከሰባ በላይ ንዑስ ጎሳዎችን ያካታሉ፡፡ የሁሉም የበላይ እና "የቤንች ንጉስ ነው" እያሉ የሚጠሩት ደግሞ ቤንችቴትን ነው፡፡ ቤንችቴት የቤንች ንጉስ ሆኖ በስሩም በርጊናንስ፣ አዙናንስ፣ ኮምቲካስ፣ ዳኪራስ፣ ጋሪናንስ፣ ሻሽንቴት እና ማተብናንስ የሚባሉ የቤንች ‹‹ቲያቶች›› አሉት፡፡ እነዚህን በሙሉ አስተሳስሮ የሚገዛውና የበላይ ሆኖ የሚመራው ቤንችቴት የተባለው የዘር ግንድ ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ሲነግሱ ዣኸርንቴት፣ በእንቴት፣ ቤንችቴት፣ ሜርቴትና ሼቴት እየተባሉ ይጠራሉ፡፡

በአሁን ጊዜ እነዚህ ቲያቶች ብዙም የሉም፡፡ ያለመኖራቸውን ምክንያት ደግሞ በቡድን ውይይት ጊዜ መረጃ አቀባዮቼ እንደሚከተለው ይገልፁታል፡፡

> *"ድሮ ድሮ የምንዳኘው፣ ፍርድ እና እርቅ የምናገኘው በመሪዎቻችን ነበር፡፡ ስናጠፋ እንቀጣለን፤ ግብር እንከፍላቸዋለን፤ ሸንጎ አብረን እንቆማለን፤ … አሁን ግን ያ ሁሉ ቀርቶ በማናውቃቸው ሰዎች ነው የምንመራው፡፡ ፊደል በቆጠሩ እና ከሌላ ቦታ በመጡ ሰዎች ነው የምንዳኘው፡፡ ለቲያቱ*

*ወይም ለሚንጊው (ንጉስ) እውቅና የሚሰጠው የለም። በጣም እሩቅ በሆኑ የቤንች ቦታዎች ካልሆነ እነዚህ መሪዎችን ማግኘት አይቻልም። ዘራቸው ግን አለ። አይንገሱ እንጂ እኛ እነማን እንደሆኑ እናውቃቸዋለን።* (ቄስ ሳሙኤል፣ አቶ ክፍሌ እና አቶ ሾጫ፣ የካቲት፣ 16/2005)።

ከሰዎቹ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው ይህ ባህላዊ የሆነው አስተዳደራዊ ስርዓት በአሁኑ ሰዓት እየቀነሰ መምጣቱን እና በጣም ርቀት ባላቸው የቤንች ስፍራዎች አልፎ አልፎ መገኘቱን ነው። እኔም በመስክ ቆይታየ ለማረጋገጥ እንደቻልኩት እነዚህ "ቲያቶች" የሚኖሩት በደቡብ ቤንች ወረዳ ገጠራማ አካባቢዎች መሆኑን ነው። ነገር ግን እነዚህ ቲያቶች መኖራቸው ቢታወቅም እንደ ድሮው ብዙም እውቅና እንደማይሰጣቸው ለማወቅ ችያለሁ።

የእነዚህ ‹‹ቲያቶች›› (ጌቶች) የለቅሶና የቀብር ሥነ ስርዓት ከሌላው የቤንች ብሔረሰብ (አባላት) የተለየ ነው። የክዋኔውን ዝርዝር ጉዳይ ደግሞ በንዑስ ክፍሎች በመከፋፈል እንደሚከተለው እተነትናለሁ።

### 4.2.1 ከቀብር በፊት

አንድ ባላባት ወይም ቲያት[13] በህይወት ዘመኑ ልክ እንደ ባለ ቃልቻው ሁሉ የሚጠብቁትና የሚያገለግሉት ሰዎች አሉ። ይህን ባላባት ወይም ቲያት የሚንከባከቡት ሰዎች "ወይዘስ" ይባላሉ። የታመመው ቲያት መሞቱ የማይቀር ከሆነ ወይዘስ የተባሉት ጠባቂዎች ለማንም ሰው ሳይነግሩ የተለያዩ ዝግጅቶችን ያከናውናሉ። ለምሳሌ ጥቁር በግ መርጠው ያርዳሉ። ይህንንም ስጋ ወይዘሶች ናቸው የሚመገቡት። የጥቁር በግ ስጋ የተመረጠበት ምክንያት ‹‹ቲያቱ›› በሚሞቱበት ጊዜ (በጣረሞት ላይ እያሉ) ጣረሞቱ እንዳይበረታባቸው የጥቁር በግ ደም መፍሰስ አለበት፤ ብለው ስለሚያስቡ መሆኑን በቡድን ውይይት ጊዜ ለመረዳት ችያለሁ። የሟች ነፍስ እንደወጣ ሞቷል፤ ተብሎ አይነገርም። ከሞተ በኋላ በእጁ ያጠለቀውን አንባር (ከብር የተሰራ)[14] አውልቀው በሚያንጊው ግቢ ውስጥ ያስቀምጣሉ። ይህንን የሚያደርጉበት ምክንያትም ‹‹ሌላ ባለቲያት ሲተካ የሚያጠልቀው አንባር ይኸ›› በመሆኑ እና ሁሉም ነገር እንደነበረው እንዲቀጥል ለማድረግ እንደሆነ አቶ መኮንን ይገልፃሉ። (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት፣ 23/2005)። ይህ ከተከወነ

---

[13] በአብዛኛው በቤንች ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት ጊዜ ሁሉንም የሟች አይነቶች (ባለቃልቻ፣ ባላባትና ቲያት፣ የእድሜ ባለፀጎች፣ ጎልማሶች እና ህፃናትን) የሚያመሳስላቸው ነገር አለ። ለምሳሌ ከቀብር በፊት እና ከቀብር በኋላ ያለው ስርዓት በአብዛኛው ይመሳሰላሉ። የሚለዩትም የሚሰጡት የጊዜ ርዝመት እና ትርጉም እንዲሁም ከመሪው (ከእምነት) ወይም ከ‹‹ቲትት›› ጋር የተያያዘ ከሆነ ብቻ ነው። ስለዚህ እጥቡቱ፣ ግንዘቱ፣ ወዘተ. ተመሳሳይነት ስላለው ከመጀመሪያው ላይ ከጠቀስኩት ውጪ የተለየ ትርጉም ካላስገኘ በስተቀር በሌሎች ላይ እንብዛም አላካትም።

[14] አንባሩ (ዱል) የንጉስነት (የጌታነት) ምልክት ነው። ይህን አንባር ማንም ሰው ማጥለቅ አይችልም።

በኋላ የግንዘት ስርዓት ይካሄዳል፡፡ የግንዘት ስርዓቱን በተመለከተ አቶ አቤል የተባሉ መረጃ አቀባይ እንደሚከተለው ይገልፁታል፡፡

> *ቲያቱ እንደሞተ አንባሩ (ዱል) ከወለቀ በኋላ በሳሙና በደንብ ይታጠባል፡፡ ከዚያም ግንዘት የሚችሉ የአካባቢ ሽማግሌዎች ይገንዙታል፡፡ በሁሉም ሟቾች ዘንድ ግንዘቱ ተመሳሳይ ነው፡፡ ጆሮ፣ አፍንጫ፣ አፍ በጨርቅ ይደፈናሉ፡፡ የወንዱ ብልት እና እጅ ጣቶች በአንድ ላይ በጨርቅ ይታሰራሉ፡፡ እግር ይታሰራል፡፡ በንፁህ ጨርቅ ይጠቀለላል፡፡ ከዚያም አዲስ እንጨት ተቆርጦ ውስጡ ተቦርቡሮ በጨርቅ የተጠቀለለው አስከሬን በተቦረቦረው እንጨት (ያም) በማስገባት ክዳኑን መግጠም ነው፣ በማለት ገልፀዋል፡፡ (ቃለመጠይቅ፣ ጥር፣ 07/2005)*

የሟች ጆሮ፣ አፍንጫ እና አፍ በጨርቅ የሚደፈኑበት ምክንያት ፈሳሽ ከአስከሬኑ እንዳይወጣ ነው፡፡ ከብልቱ ጋር እጅን አያይዘው የሚያስሩት ለመገነዝ እንዲያመች እንጂ የተለየ ትርጉም እንደሌለው መረጃ አቀባዮቹ ገልፀውልኛል፡፡

የሴቶችም የግንዘት ስርዓት ከወንዶች የግንዘት ስርዓት አይለይም፡፡ የሚለየው ነገር ቢኖር ግንዘቱን የሚያካሂዱት በአካባቢው የሚገኙ አሮጊቶች መሆናቸው ነው፡፡ “ወንዶች የሴትን ገመና ማየት የለባቸውም” ከሚል የመነጨ መሆኑን አቶ አለማየሁ የተባሉ መረጃ አቀባይ ገልፀውልኛል፡፡

የግንዘቱ ስርዓት ከተጠናቀቀ በኋላ አስከሬኑ ሚያንጊው ቤት ይቀመጣል፡፡ ከዚያ በኋላ ክራር (ሾንጋ) ይመታል፡፡ ዘፈን ይዘፈናል፡፡ ከብት ይታረዳል፡፡ ይህንን የሚያደርጉት ወይዘስ የተባሉ ጠባቂዎች ናቸው፡፡ ከእነዚህ ወይዘሶች ውጭ ሌላው ሰው ቲያቱ መሞቱን አያውቁም፡፡ የሟች ቤተሰቦች በሆነ አጋጣሚ ቢሰሙ እንኳ እንዳያለቅሱና ለሌሎች ሰዎች እንዳይነግሩ ይደረጋል፡፡ በተወሰኑ ቀናት በሚስጢር ተጠብቆ መቆየት አለበት፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያትም ወራሹን (ተከታዩን ቲያት) ለመምረጥ እንዲያመቻቸው ነው፡፡

እንደ አቶ አቤል ገለፃ በአብዛኛው የመሪነትን ስልጣን የሚይዙት የባይኬስ ዘሮች ናቸው፡፡ ሌሎች አይዙም፡፡ ምክንያቱም የቤንች ንጉስ ተብሎ የሚጠራው ቤንችቴት ስለሆነና ለቤንችቴት የሚቀርበው ደግሞ ባይኬስ ጎሳ ስለሆነ ስልጣን ከዚህ ጎሳ ይሳባል፡፡ ሌሎች ከነገሱ ግን በሐገር ላይ ችግር ይደርሳል፤ ተብሎ ይታሰባል፡፡ የብሔረሰቡን ወይም የጎሳውን የዘር ግንድን መሰረት ለመግለፅ እና የማንነትን ጥያቄ መልስ በለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ውስጥ ለመመለስ እና ለማወቅ ያስችላል፡፡ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑት በለቅሶው ጊዜ በአልቃሾች የሚደረደሩት የሙሾ ቃል

ግጥሞች ናቸው፡፡ ግጥሞቹ የሚቹን የዘር ግንድ ከመግለፃቸውም በተጨማሪ ስለሚቹ ማንነትና ተግባር ገላጮች ናቸው፡፡ ለአብነት ያህል የሚከተለውን ግጥም መመልከት ይቻላል፡፡

<u>ቤንችኛ</u>

ኮጆዋ ባንጋኤ
ባይ መጠፈኪያስዎ
ዎርጉዋ!
ሻሻ ጋኪትናስ
ቃዝኒሲ ያራሳርጉሳ
ባባ ሙሳጉሾዎ
ባባ ኡሻጉሾዎ
ዎጣ ኒ ኤታንቁዬሽንዶዴ!

<u>አማርኛ</u>

የባላባት ጎሳ
እንደእናት የምናየው አንድ አባታችን ጠፋ
የዎርጉ ዘር
የጋኪት ልጅ
አውጥቶ የማይመልስ
የተራቡትን የምታበላ
የተጠሙትን የምታጠጣ
እንዴት ሞት ወሰደህ!?

ከዚህ ግጥም እንደምንረዳው ከሚቹ ጋር የተያያዙ ብዙ ነገሮች በውስጡ አካቷል፡፡ ከእነዚህም መካከል ሚቹ የየትኛው ጎሳ አባል እንደሆነ እንረዳለን፡፡ በመጀመሪያው ስንኝ "ኮጆዋ ባንጋኤ" ወይም "የባላባት ጎሳ" ከሚለው የምንረዳው ሚቹ ከቤንችቴት የጎሳ ዘር መሆኑን ነው፡፡ ምክንያቱም በቤንች ብሔረሰብ ዘንድ ባላባትነት ወይም የመሪነትን ሚና እንዲጫወቱ የሚመረጡት ከቤንችቴት ነውና፡፡ በተያያዘም ከዋናው ጎሳ ውስጥ ከየትኛው ንዑስ ጎሳ እንደተመረጠ የሚጠቁም "የዎርጉ" የሚል ቃል እናገኛለን፡፡ ስለዚህ ሚቹ ዋና ጎሳው ቤንችቴት ሆኖ በንዑስነት ደግሞ የዎርጉ እንደሆነ እንረዳለን፡፡

በተያያዘም የሚቹን ተግባራት እና ባህሪያትን ከግጥሙ መመልከት ይቻላል፡፡ ይኸውም ከላይ እንደምናየው ሚች እንደ እናት እሩህሩህ እና ለጋስ መሆኑን፤ የተራቡትን የሚመግብ፣ የተጠሙትን የሚያጠጣ፣ ወዘተ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ በአጭሩ በቤንች ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት ጊዜ ከከዋኔው ጋር ተያይዘው የሚመጡት የሙሾ ግጥሞች በአብዛኛው የሚችን ማንነት፣ ስነምግባር፣ የዘር ሀረግ (ግንድ)፣ ወዘተ የሚገልፁ ናቸው፡፡

በቤንች ብሔረሰብ ዘንድ ተመሳሳይ የሆነ የኑዛዜ ስርዓት አለ፡፡ ይህም ስርዓት ሲሞቱ አስከሬኔን ‹‹ከዚህ ቦታ ቅበሩት›› የሚል ነው፡፡ በመሆኑም ቲያቶችም ሆኑ ሌሎች ሰዎች ሲሞቱ የሚቀበሩት ለእነሱ ተብሎ በተዘጋጀ ደን ውስጥ ነው፡፡

### 4.2.2 በቀብር ጊዜ

ሌሎች ሰዎች ሳይሰሙ ወይዘሶች ብቻ ከጥንት ጀምሮ የንጉሱን አስከሬን ወደሚያርፍበት ደን (ኩበም) ተሸክመው ይሄዳሉ፡፡ ከዚያም በደኑ ውስጥ አልጋ ሰርተው አጥር አጥረው፣ ከጨረሱ በኂላ አስከሬኑን ማንም ሳያይ አልጋው ላይ አድርገው ይጠብቁታል፡፡ እነዚህ ጠባቂዎችም (ወይዘሶች) እዛው ጎጆ ሰርተው ከብት እያረዱ እና እየበሉ ከሁለት እስከ ሦስት ወራት ድረስ አስከሬኑን ይጠብቁታል፡፡ ይህ የሚሆንበትን ምክንያት አቶ አቤል እና አቶ አለማየሁ የተባሉ መረጃ አቀባዮች እንደሚከተለው ይገልፁታል፡፡

> *… በቤንች ባህል መሰራት ቲያት የተባሉ ሰዎች ሲሞቱ ብዙ ዝግጅቶችን ይጠይቃል፡፡ ሰዎቹ ሲሞቱ መሞት ሳይሆን ወደ ‹‹ነብርነት›› ይቀየራሉ ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ቲያት በተለይም ቤንችቴት ዘር ሲሞቱ ነብር ይሆናሉ ሌሎች ደግሞ ቀብሮ ይሆናሉ ብለው ስለሚያስቡ ነው፡፡ ስለዚህ ሟቹ ነብር ሆኖ እስኪወጣ እና ጫካ እስኪገባ ድረስ ወይዘሶች በመካን መቃብሩ (መንከር) ዳር በመሆን አይናቸው ሳይነቅሉ (ሳያነሱ) ተራ በተራ አስከሬኑን ይጠብቃሉ፡፡*[15] *(ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 07/2005)*

እነዚህ ቲያቶች የሚቀበሩት ለቲያቶች ተብሎ በተዘጋጀ መቃብር ነው፡፡ የቤተሰብ መቃብር እንደሆነም ይነገራሉ፡፡ በሆነ አጋጣሚ (በማህበራዊ ኑሮ፣ ከአካባቢው ተለይቶ በሌላ ሩቅ ቦታ ሰፍሮ ወዘተ.) ኑሮ አንድ ቲያት ቢሞት ከቤተሰቡ መካነ መቃብር አካባቢ መቀበር እንዳለበት ብሔረሰቡ የተሰማማው ጉዳይ ነው፡፡ አቶ አለማየሁ የተባሉ መረጃ አቀባይ እና የባይኬስ ጎሳ ከራሳቸው ገጠመኝ ጋር አያይዘው እንደሚከተለው ይገልፁታል፡፡

> *… የንጉስ ዘር ከሆኑ የትም ቦታ ይሙቱ በጨለማ አስከሬኑ ተጉዞ አያቶቻቸው መቃብር ቦታ ማረፍ አለባቸው፡፡ ለምሳሌ፡- የእኔ አጎት ከፋ ምድር (ጨና) የሚባል ቦታ ሞተ፡፡ ከዚያ ግን አልተቀበረም፡፡ ሲሞትም ወስዳችሁ አባቶቼ መካነ መቃብር ዳር ቅበሩኝ ስላለ የግድ በጨለማ አምጥተን አባቶቻችን መቃብር (ደን) ውስጥ ነው የቀበርነው፡፡ እንዳውም የተፀዳዳበትን ሰገራ ሁሉ ሳይቀር ከደኑ ውስጥ እንዲጣል ይደረጋል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 07/2005)*

አቶ አለማየሁ ከላይ የገለፁት የሚፈፀምበት ምክንያት አንደኛ የሟች ቃል ስለሆነ ነው፡፡ የሟች ቃል ደግሞ ይከበራል፡፡ ሌላው ቲያቶች በሌላ ቦታ (ሀገር) ቢቀበሩ ንግስናው (ንጉስ የመሆኑ)

---

[15] ምንም እንኳን የቲያት የለቅሶ ስርዓት እንዳለ በሁለተኛ የመስክ ስራ ጊዜ ተደውሎልኝ ብሔድም ስርዓቱን ግን ሙሉ በሙሉ ለማየት አልቻልኩም፡፡ ምክንያቱም ደግሞ ‹‹ከወይዘሶች›› ውጭ ያለውን ሰው በስርዓቱ እንዲካፈል ስለማይፈቅዱ ነው፡፡ ጠይቄ እንደተረዳሁት ሌላ ሰው ካለ በቀላሉ ሟች ወደ ነብርነት አይቀየርም፡፡ ብለው ስለሚያስቡ ነው፡፡

ሁኔታ በቤንች ላይ ያከትማል፤ ለሌሎች ሰዎች አሳልፎ የመስጠት ያህል እንደሆነ ይታሰባል። ሟች የተፀዳዳው ሰገራ ደግሞ "በረከት ነው" ብለው ስለሚያስቡ አምጥተው ደኑ ውስጥ እንደሚጥሉት በቡድን ውይይት ጊዜም ለማረጋገጥ ተችሏል። (የካቲት፣ 16/2005)።

ወይዘሮች አስከሬኑን ትኩር አድርገው (አይናቸውን ሳያነሱ) የሚጠብቁት ደግሞ ሟቹ (ቲያቱ) ነብር ሆኖ ወጥቶ ሲሔድ እንዲያዩት ነው። ከዚያም ከሦስት ወር በኋላ ወይዘሮች ‹‹ጌቶች ነብር ሆነው ወንዝ ተሻግረው ጫካ ገቡ›› በማለት ለተተኪው ቲያት እና ለሌሎች በሚስጥር ይነግራሉ። ከዚህ ሐሳብ ጋር በተያያዘ አቶ ክፍሌ የተባሉ የመረጃ አቀባይ እንደሚከተለው ይገልፁታል።

> *... ቲያት የሆኑ የቤንችቴት ዘሮች ሲሞቱ ወደ ነብር ይቀየራሉ። ባንድ ጊዜ ሳይሆን ከ 2-3 ወራት ድረስ ሊወስድ ይችላል። ወይዘሮች አስከሬኑን በደን ውስጥ ሆነው ወደ ነብርነት እስኪቀየር ድረስ ይጠብቁታል። ከዚያም በአካባቢው ነብር ከጮኸ፣ በአካባቢው ነብር በግ፣ ጥጃ ወዘተ በልቶ ከሔደ እና ወይዘሮች ከሰሙ ጌቶች ነብር ሆነው ወንዝ ተሻግረው ሲሄዱ አይተናል ተብሎ ይነገራል። (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት፣ 17/2005)*

ወይዘሮች የቲያቱ አስከሬን ወደ ነብር ተቀየረ፤ ብለው ከመጡ በኋላ ሌሎች ከቤት የነበሩት ሽማግሌዎችና ወይዘሮች ወደ መካነ መቃብሩ ይሔዳሉ። ከዚያም ከአልጋው ላይ ያለውን የአስከሬን ሳጥን ንብ ሰፍሮበት ከሆነ እውነትም ሟች ወደ ነብርነት ተቀይሯል፤ ተብሎ ይወሰዳል። በተጨማሪም አዲስ በተተካው ቲያት ላይ ጥሩ ነገሮች እንደሚገጥሙት እና ዘመኑም የጥጋብና የደስታ ዘመን እንደሚሆን በባህሉ ይተረጎማል። ምናልባት የሟችን አስከሬን ጉንዳን ሰፍሮበት ከሆነ የችግርና የርሀብ ዘመን ከመሆኑም በተጨማሪ ተተኪው ቲያት እድሜ አይኖረውም ተብሎ ይታመናል።

እነዚህ ሰዎች በሚሞቱበት ጊዜ ወደ ነብርነት ይቀየራሉ የሚባሉት በህይወት እያሉ "የነብርን ያህል ስልጣን፣ ጀግንነት፣ አቅም እና ተፈሪነት በብሔረሰቡ ዘንድ ስለሚሰጣቸው" መሆኑን አቶ አለማየሁ የተባሉ መረጃ አቀባይ ይገልፃሉ። (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 07/2005)። በመሆኑም እነዚህን ሰዎች ሞት አያሸንፋቸውም፤ መሞት ሳይሆን ወደ ነብርነት መለወጥ ነው፤ ብለው እንደሚያምኑም አቶ አለማየሁ አያይዘው ይገልፃሉ። ሌሎች ሰዎችን ደግሞ የተናቁ አድርጎ ለማሰብ ወደ ቀበሮነት ይቀየራሉ፤ ብለው ያምናሉ። ቀበሮ በብሔረሰቡ ዘንድ የተናቀ እና ዝቅተኛ ተደርጎ እንደሚታሰብ በቃለ መጠይቅ ጊዜ ቄስ ሳሙኤል ገልጸውልኛል። (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 18/2005)

የቲያቱ አስከሬን ወደ ነብርነት ተለውጧል፤ ተብሎ ከታመነበት በኋላ አስከሬኑን አልጋው ላይ (ከዚያው ቦታ) ይጥሉታል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ አቶ አቤል እንዲህ ይላሉ፡፡ "በእርግጥ ሄዶ ማየት ባይፈቀድልኝም በ1997 ዓ.ም ከፈረንጆች ጋር ሆኘ በአውሮፕላን የቲያቶችን መቃብር ቦታ ጎብኝቻለሁ፡፡ በደኑ ውስጥ ብዙ አልጋዎች አሉ፡፡ ከአልጋው ላይ ደግሞ የአስከሬን ሳጥኖች መኖራቸውን አይቻለሁ፡፡ አፈር ቆፍረው አይቀብሩትም፡፡" (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 07/2005)

የሟቹን አጥንት በጉድጓድ ውስጥ የማይቀብሩበት ምክንያት ሟቹ ነብር ስለሆነ የሚቀበር ነገር የለም፡፡ አጥንቱ ብቻ ነው የቀረው፤ ስለዚህ አጥንቱ ቢቀበር ባይቀበር ችግር የለውም፡፡ በማለት ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ በንጉስ የቀብር ስርዓት ጊዜ ወይዘስ በመሆን ያገለገሉ ሰው ገልፀውልኛል፡፡ በተያያዘም በሦስት ወር ቆይታቸው ጊዜ ሟችን በዘፈን፣ በፉከራ ወዘተ እያሞገሱ እንደሚጨፍሩ ነግረውኛል፡፡ ምን ምን እንደሚሉ ግን ለመግለፅ ፈቃደኛ አይደሉም፡፡ ምክንያቱም ይህንን እና ሌሎች ስርዓቶችን ብንናገር ጥሩ አይደለም፡፡ ነብር ሆኖ የወጣው ሟች ከኛ ላይ መቅሰፍት ያደርስብናል፤ ሲሉ ገልፀውልኛል፡፡

ከዚያም ወይዘሶች ለአካባቢ ሰዎች ይነግራሉ፡፡ የሞተው የጎሳው መሪ፣ የአካባቢ ዳኛ፣ የአካባቢው አስተዳደር ስለሆነ በአካባቢው ያሉት ሰዎች በሙሉ የሚበላ ምግብ እንዲያዘጋጁ ይደረጋል፡፡ ሌሎች ወይዘሶች ደግሞ እሩቅ ላሉ ሰዎች ‹‹ቲያቱ›› መሞቱን እንዲነግሩ ይደረጋል፡፡ ልክ እንደ ባለቃልቻው ሁሉ ‹‹አባታችን ቀለለ›› እንጅ ሞተ አይሉም፡፡ ምክንያቱን ደግሞ ቄስ ሳሙኤል ሲገልፁ ‹‹ቲያቱ ወይም ባላባቱ ነብር ሆኖ ጫካ ይገባል፤ እንጅ ይሞታል ተብሎ በብሔረሰቡ ዘንድ አይታሰብም፡፡ ስለዚህ ቀለለ ይባላል፡፡ "ዛክንድ ቀለለ" ይላሉ፡፡ ዛክንድ የዝሆን ጥርስ ነው፡፡ ስለዚህ ባላባቱ በዝሆን ጥርስ ይመሰላል፡፡ የዝሆን ጥርስ መሆን ትልቅ ክብር ነው፡፡ ስለዚህ ይህ ክብር ያለው ሰው ስለሚታወቅ ‹‹ዛክንድ ቀለለ›› ብለው ሲናገሩ ‹‹ዛክንድ›› ማን እንደሆነ ያውቃሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣18/2005)

ምስል 4፡ ባላባቶች (ቲያቶች) የሚቀበሩበት ቦታ የሚያሳይ ፎቶ በከፊል፡፡

ከርቀት የሚመጡት ሰዎችም ተሰባስበው ይመጣሉ፡፡ ሲመጡ ግን በሬ፣ ላም ወይም ወይፈን ይይዛሉ፡፡ ሰውየው (ሚች) በአካባቢው ዘንድ እንደ ንጉስ (አስተዳዳሪ) ስለሚታይ ባዶ እጅ ወደ ንጉስ መቅረብ ክልክል እንደሆነ በቡድን ውይይት ጊዜ የተለያዩ ሰዎች ገልፀውልኛል፡፡ (የካቲት፣ 16/2005)

በመሆኑም ያመጡት ከብት ይታሰርና የሚቹ ንብረቶች በቅያሬ ተሰጥቷቸው አርደው እንዲበሉ ይደረጋል፡፡ በቤንች ብሔረሰብ ዘንድ ቲያቱን ለሞት ያበቃው ሃብትና ንብረቱ ነው፤ ተብሎ ስለሚታሰብ የመጣው ሰው በሙሉ ንብረቱን በሙሉ አጠፋፍቶት እንዲሔድ ይደረጋል፡፡ ከዚያም ጋሻ፣ ጦር፣ ከበሮ፣ ጥሩንባ፣ ክራር ወዘተ… በመያዝ እየጨፈሩ[16] ሐዘናቸውን እንዲገልፁ ይደረጋል፡፡ ጭፋሮውም በ 4.1 እንደገለፅኩት ‹‹የሮ›› የተባለውን የጭፈራ አይነት ነው፡፡ በባለቲያቶች ለቅሶ የሴቶች ሚና በብዛት ምግቦችን ማዘጋጀት ነው፡፡

### 4.2.3 ከቀብር በኋላ

የባላባቶች ለቅሶ ሰፊ ጊዜን የሚጠይቅ ነው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ሚቹ በብሔረሰቡ ዘንድ ያለው ደረጃ ከፍተኛ በመሆኑ ነው፡፡ እስከ አንድ ወር ድረስ ጊዜ አላደርስ ያላቸው የሩቅ ሰዎች ከብት እየያዙ ከሚች ቤተሰቦች እየመጡ ሐዘናቸውን ይገልጻሉ፡፡ ከአንድ ወር በኋላ የሚች ሚስቶች

[16] በቤንች ብሔረሰብ ዘንድ ሰው ሲሞት የሚጨፈረው የሚችን ነፍስ ያስደስታታል፤ ጥሩ ነገር ይገጥማታል፤ ገነት በቀላሉ ትገባለች ወዘተ. እየተባለ ስለሚታሰብ እና የሰዎችን ጀግንነት ለመግለፅ ነው፡፡

የውርስ ስርዓት ይካሄዳል፡፡ በቤንች ብሔረሰብ ዘንድ የሟቹን ሚስቶች የሚወርሰው የሟቹ ታናሽ ወንድም ነው፡፡ ምክንያቱን አቶ ክፍሌ ሲገልፁ ‹‹የሟች ታናሽ ወንድም እንደራሱ አድርጎ ይንከባከባቸዋል፤ ለችግር አሳልፎ አይሰጣቸውም፤ ስለሚባል እንዲወርስ ይደረጋል›› (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 07/2005) በማለት ይገልፃሉ፡፡ ይህ ስርዓት ከተከናወነ በኋላ የሐዘን ስርዓቱ ይጠናቀቃል፡፡

## 4.3 የእድሜ ባለፀጎች የለቅሶ ስርዓት

በቤንች ብሔረሰብ ዘንድ የእድሜ ባለፀጎች የለቅሶ ስርዓት የሚባለው እድሜያቸው ከ 60 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ሲሞቱ መሆኑን አብዛኛዎቹ መረጃ አቀባዮቹ ይስማማሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች ብዙ ያዩ፣ ልጅ ወልደው የጨረሱ፣ የሚገባቸውን የሰሩ፤ ተብለው ስለሚታሰቡ የለቅሶ ስርዓቱም ከሌሎች ይለያል፡፡ ልክ ከአሁን በፊት እንደገለፅኩት ምን ምን ዝግጅቶች እንደሚደረጉ በዝርዝር እተነትናለሁ፡፡

### 4.3.1 ከቀብር በፊት

አንድ ሽማግሌ ወይም አሮጊት ሲታመሙ ልክ እንደ ሌሎች ሰዎች ሁሉ በቤተሰብ በኩል ይጠበቃሉ፡፡ በሽታቸው ፀንቶ ከሞቱም ከቤተሰቡ አባላት መካከል ግንዘት የሚችል ሰው ሰውነታቸውን አጥቦ እንዲገንዛቸው ይደረጋል፡፡ የግንዘቱ ቅደም ተከተልም ከላይ በ (4.1 እና በ 4.2) እንደገለፅኩት ተመሳሳይነት አለው፡፡ ቤተሰቡ የሚገንዘበት ምክንያትም የሟችን ገመና ከቤተሰቡ ውጭ ሌሎች ማወቅም ሆነ ማየት የለባቸውም፤ ብለው እንደሚያስቡ በቡድን ውይይት ጊዜ ለመገንዘብ ችያለሁ፡፡ በሌሎች የለቅሶ አይነቶች ለመግለፅ እንደሞከርኩት በብሔረሰቡ ዘንድ ብዙም የኑዛዜ ስርዓት የለም፡፡ ቢኖርም እንኳ የመቀበሪያ ቦታቸውን ብቻ ነው ነግረው የሚያርፉት፡፡

ግንዘቱ ከተጠናቀቀ በኋላ መልዕክተኞች ተመርጠው መሞቱን (ቷን) ለሌሎች የሩቅ ሰዎች እንዲነግሩ ይደረጋል፡፡ መልዕክተኞችም ‹‹እገሌ›› ወይም ‹‹እከሊት›› አርፈዋል፤ በማለት ይናገራሉ፡፡ አርፈዋል የሚባልበት ምክንያትም ሰዎቹ (የእድሜ ባለፀጋዎቹ) መሞት በሚገባቸው ትክክለኛ የእድሜ ደረጃ ላይ ነው ያረፉት ተብሎ ስለሚታሰብ መሆኑን ቄስ ሳሙኤል ይገልፃሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ጥር፣ 18/2005)፡፡ ከርቀት የሚመጡ ሰዎችም የተለያዩ ቁሶችን (ጦር፣ ዱንክ፣

ፍርግግን፣ ጋሻ ወዘተ) በመያዝ እና ከጦሩ ጫፍ ላይ እርጥብ ሳር በማሰር ተሰባስበው ወደ ሟች ቤት ይሄዳሉ፡፡

እነዚህ የእድሜ ባለፀጎች በህይወት ዘመናቸው ብዙ ሀብት እና ንብረት ያፈሩ ስለሆኑ ሀብት እና ንብረታቸው በሙሉ ለለቅሷቸው ክዋኔ ማስኬጃ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ በመሆኑም ሰዎቹ እንደሞቱ ቀሪ የቤተሰቡ አባላት ለለቅሶው ማስፈፀሚያ የተለያዩ ምግቦችን ያዘጋጃሉ፡፡

ምስል፡5 ሴቶች ለለቀስተኛው አምቾ የተባለውን የምግብ አይነት ሲያዘጋጁ፡፡ በስተቀኝ በኩል ያለው ደግሞ የተዘጋጀ (የበሰለ) አምቾ ነው፡፡ ከማን ለቅሶ ላይ እንደተወሰደ ለመጥቀስ ሰዎች ፈቃደኞች አይደሉም፡፡

ከአምቾ በተጨማሪ ሌሎች የምግብ እና የመጠጥ አይነቶች (ጩሞ (ጊያዕቶሪ)[17]፣ ጠላ፣ አረቂ እንዲሁም የእርድ ስርዓቶች) ይዘጋጃሉ፡፡ የሞተው ሰው በጣም ሀብታም ከሆነ እስከ አስር ከብት ሊታረድለት ይችላል፡፡ በምልከታ ጊዜ ለማየት እንደቻልኩትም በአንድ የለቅሶ ስርዓት ላይ ስምንት ከብቶች መታረዳቸውን ነው፡፡ በእርዱ ጊዜ የተለያዩ መጠጦች (ጠላ፣ አረቂ፣ ጩሞ

[17] ጊያዕቶሪ ወይም (ጩሞ) ከደረቅ የቡና ቅጠል፣ ዝንጅብል፣ ኮረሪማ፣ ጤናዳም፣ ቃሪያ፣ በሶብላ፣ ነጭሽንኩርት፣ ጨው፣ ወዘተ. አንድ ላይ በማድረግ የሚዘጋጅ የብሔረሰቡ ባህላዊ መጠጥ ነው፡፡ ጩሞ በአብዛኛው ለጉንፋን መድኃኒት እንደሆነም ይናገራሉ፡፡

ወዘተ) ለሚያርዱት ሰዎች ይሰጣል፡፡ እነዚህ መጠጦች ግን ከእርዱ ጋር የሚያገናኛቸው ጉዳይ እንደሌለ ለማወቅ ተችሏል፡፡ እርዱ የሚፈፀመውም ከቀብር በፊት እና ከቀብር በኋላ ነው፡፡ "ከቀብር በፊት ለመቅበር የሚመጡት ሰዎች እንደደረሱ የሚመገቡት ይታረዳል፡፡ ያለው አምስት ስድስት ሊያርድ ይችላል፤.... ከቀብር በኋላ ደግሞ ያንኑ ያህል (አምስት ስድስት) ከብቶችን ሊያርዱ ይችላሉ፡፡" ሲሉ (አቶ አንዱ አለም ጋይ ቃለ መጠይቅ፣የካቲት 17/2005) ገልጸውልኛል፡፡

ለማየት እንደቻልኩት ምግቦችን እና መጠጦችን በማዘጋጀት በኩል የሴቶች ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ወንዶቹ የእርዱን ስርዓት ብቻ ከፈፀሙ በኋላ ምግቦች ላይ የሚከውኗቸው ተግባሮች የላቸውም፡፡ ይህንን በተመለከተ ወ/ሮ ታደለች ወዳጆ የተባሉ መረጃ አቀባይ "ወንዶች የእኛን ስራ አይችሉም፡፡ ከብት ካረዱ ሌላ አይሰሩም፡፡ ቢሰሩ እንኳ ሌሎች ሰዎች (ወንዶች) ይስቃሉ፡፡ እኛም እንስቃለን፡፡" በማለት ይገልፃሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 17/2005)

ከምግቦች ጎን ለጎን ወጣቶች ተሰባስበው ይጨፍራሉ፡፡ ከዚያም የለቅሶ ሰዓቱ ሲደርስ እና ሰዎቹ ሲሰበሰቡ አስከሬን ከቤት በማውጣት ለቀብር ይዘጋጃሉ፡፡

ምስል 6፡ ለቀብር ዝግጅት ሲያደርጉ (ከበሮ በመምታት የቅርብ ሰዎች እንዲሰበሰቡ ሲዘጋጁ)

### 4.3.2 በቀብር ጊዜ

በቤንች ብሔረሰብ ዘንድ አንድ ሽማግሌ ወይም አንዲት አሮጊት ስትሞት አይለቀስም። ባለመለቀሱ ከሌሎች የብሔረሰቡ የለቅሶ አይነቶች ለየት ያደርገዋል። የማይለቀስበትን ምክንያት ቄስ ሳሙኤል ሲገልፁ ‹‹የሞቱት ሰዎች ይህን ምድራዊ አለም አይተውታል፣ ወልደዋል፣ መስራት ያለባቸውን ሁሉ በዘመናቸው አጠናቀዋል፣ ስለዚህ የቀረባቸው ነገር ስለሌለ የሚገባቸው ለቅሶ ሳይሆን ጭፈራና ዘፈን ነው በማለት ይገልፃሉ። (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 18/2005)

በእድሜ የገፉ ሰዎች ሲሞቱ ‹‹ጎዝ›› የሚባል የጭፈራ አይነት በስፋት ይጨፈራል። ወጣቶች ሰውነታቸውን አመድ፣ ከሰል፣ አፈር በመቀባት፣ እንዲሁም ቅጠል በመልበስ ጋሻ በመያዝ፣ ጦር በመስበቅ ክብ በመስራት እና ግማሹ በአንድ በኩል በመሰለፍ ሌላው ደግሞ በአንድ በኩል በመሰለፍ ወደፊትና ወደኋላ በመወዛወዝ ይጨፈራሉ። ጭፈራው ብዙ ጉልበትን የሚጠይቅ ስለሆነ በአብዛኛው ወጣቶች እንደሚያከናውኑት በቡድን ውይይት ጊዜ ለመረዳት ችያለሁ። ሌሎች የብሔረሰቡ አባላት ዳር ቆመው በእልልታ መልክ ወጣቶችን ያጅባሉ። አንዳንድ የእድሜ ባለፀጎች ደግሞ ጋሻ እና ጦር በመያዝ እና በመቆም ሲከውኑ ተመልክቻለሁ። (ጋቸብ ቀበሌ፣ ጥር፣11/2005)

አመድ፣ ከሰል እንዲሁም አፈር ሰውነታቸውን መቀባታቸው በሟቹ ማዘናቸውን ለመግለፅ ነው። በአንተ (ባንች) መሞት አዝነናል፣ ነገር ግን የቀራችሁ ነገር ስለሌለ ጨፍረን መሸኘት አለብን ብለው እንደሚያስቡ አቶ መኮንን የተባሉ መረጃ አቀባይ ገልፀውልኛል። (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት፣ 23/2005)

በሁሉም የቤንች የለቅሶ አይነቶች (ከህፃናት ለቅሶ ውጭ) አስከሬን ከቤት ሲወጣ ወልዳ የጨረሰች ላም ትታረዳለች። በአብዛኛው ሴቶች ሲሞቱ ግን የእርድ ስርዓት ላይኖር ይችላል። ምክንያቱን ደግሞ ቄስ ሳሙኤል እና አቶ ክፍሌ ሲገልጹ ‹‹ወንዶች ሲሞቱ ወንዶችን የሚፈታተኑ እርኩስ መናፍስት አይጠፉም። እነዚህ መናፍስት የሟችን ነፍስ ሊያስጨንቁ ይችላሉ፣ እንዲሁም በቀሪ ቤተሰቡ ላይ ችግር እንዲከሰት ሊያደርጉ ይችላሉ። በሴቶች ላይ ግን ምንም ችግር አያደርሱም። ሴቶች ከመናፍስቱ ጋር ግንኙነት የላቸውም፣ ተብሎ እንደሚታሰብ ይገልፃሉ። (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 18 እና 07/2005 በተከታታይ)

ሰሜን ቤንች ወረዳ ጋቸብ በሚባል ቀበሌ በምልከታ (ጥር 11/2005) ለማየት እንደቻልኩት ሬሳው ከቤት በሚወጣበት ጊዜ አንዲት ላም በሽማግሌዎች ትታረዳለች፡፡ ስጋውንም ‹‹መንጃ›› የተባሉ ጎሳዎች ሲመገቡ አይቻለሁ፡፡ በተጨማሪም የሟች የበኩር ልጅ የአባቱን አስከሬን አራት ጊዜ ነክቶ ሌሎች ሰዎች ተሸክመው እንዲሄዱ ሲያደርግ አይቻለሁ፡፡ የበኩር ልጅ አስከሬኑን አራት ጊዜ የሚነካበት ምክንያትም ‹‹ሟች ቀባሪ አለው›› ለማለት እንደሆነ በቡድን ውይይት ጊዜ ለማረጋገጥ ችያለሁ፡፡ (የካቲት፣ 16/2005)

የአሮጊቶች አስከሬን በሚወጣበት ጊዜም ይህ ከፍ ሲል የጠቀስኩት ስርዓት ይደረጋል፡፡ ለምሳሌ፡- ሰዎቹ ልጆች ባይኖራቸውስ? ብዬ ለጠየኩት ጥያቄ ቄስ ሳሙኤል የተባሉ መረጃ አቀባይ "… ልጅ ከሌላቸው በጣም ይታዘናል፤ በጣም ይለቀሳል፤ ይህ ወይም ይች ቀባሪ እንኳ የሌለው ወይም የሌላት ተብሎ ይታዘንላታል (ለታ)፡፡ ከዚያም አስከሬኑ በሚወጣበት ጊዜ የሟች የቅርብ ዘመድ ድቡልቡል ድንጋይ እንዲያንከባል ይደረጋል፤ ሲሉ ገልጸውልኛል፡፡ (ቃለ መጠየቅ፣ ጥር፣ 18/2005)

ድቡልቡል ድንጋይ እንዲንከባለል የሚደረገው ለቀባሪ ሳይበቁ በመሞታቸው ድንጋዩ እራሱ ተንከባሎ ይቅበራቸው፤ አፈር ያልብሳቸው፤ የመጣው ሰውም ሟቾች ልጅ አለመኖራቸውን አውቀው በደንብ ሊያዝኑ እንደሚገባቸው… የሚያመለክት መሆኑን በቡድን ውይይት ጊዜ (አቶ አለማየሁ እና አቶ አቤል፣ የካቲት/16/2005) ገልፀውልኛል፡፡

በተያያዘም ሴቶች (አሮጊቶች) በሚሞቱበት ጊዜ የሟች ጎረቤቶች በሙሉ የሟችን ንብረቶች (መመገቢያ ሳህኖች፣ ድስቶች፣ ምጣዶች፣ ብርጭቆዎች ወዘተ) በመያዝ አስከሬኑ በሚወጣበት ሰዓት ውጭ አውጥተው ይሰባብሯቸዋል፡፡ ይህ የሚደረገውም "ከእንግዲህ በአንድ ሳህን ባንድነት መመገቡ፣ ድስቶችን የመዋዋሱ፣ በአንድ ብርጭቆ አብሮ መጠጣቱና መዋዋሱ አከተመ፣ ተለያየን ወዘተ" የሚል ትርጉም እንዳለው አቶ ክፍሌ ገልፀውልኛል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 07/2005)

የእድሜ ባለፀጎች በሚሞቱበት ሰዓት በምልከታ ለማየት እንደቻልኩት እና ከፍ ሲል እንደገለፅኩት በአብዛኛው የሚጨፍሩት ወጣቶች ናቸው፡፡ የሟችን መሞት አግባብነት የሚገልፁ ግጥሞችን በጋራ በማዜም አስከሬኑን ይሸኛሉ፡፡ ለምሳሌ ቀጥሎ የሰፈረው በሰሜን ቤንች ወረዳ በጋቸብ ቀበሌ በአንድ የለቅሶ ስርዓት ጊዜ ሲያዜሙ የሰማሁት ነው፡፡

| ቤንችኛ | አማርኛ |
|---|---|
| ንያስ ወፈስ ታማን ምጥኤፈሰርጉኤ | ያንተ ሞት ሞት ሳይሆን ክብር ነው |
| ንያስ ዎርዶንተ ታማን ዎጥኤሳርጉኤ | ያንተ ሞት ሞት ሳይሆን ሰርግ ነው |
| ንያስ ካዥ ታማን ዎጥኤሳርጉኤ | ያንተ ሞት ሞት ሳይሆን ደስታ ነው |
| ንም ሽዱሽ ቦጋ ከንግይ ፋቱሻግዛዎ | የቀረህ ጉዳይ የለም ሁሉም የተፈፀመ ነው፡፡ |

(ምልከታ፣ ጥር 11/2005)

ስንኞቹ የሟችን መሞት ተገቢ መሆኑን የሚያንፀባርቁ ናቸው፡፡ ለቅሶውን ወይም ሀዘኑን በሌላ ተለዋጭ (በክብር፣ በሰርግ እና በደስታ) ተክተውት እናያለን፡፡

ከአሁን በፊት በተገለፁት የለቅሶ አይነቶች እንደታየው በብሔረሰቡ ዘንድ የቤተሰብ መቃብር ቦታ አለ፡፡ ለምሳሌ፡- አንድ የእድሜ ባለፀጋ ከቤተሰቡ መካነ መቃብር እርቆ ቢሞትና ከዚያው (በሌላ ቦታ) ቢቀበር፣ ከመቀበሩ በፊት ጥፍሩ ተቆርጦ፣ ፀጉሩ እና ፂሙ ተላጭቶ መጥቶ ከቤተሰቡ መካነ መቃብር ቦታ በአንድ ላይ ሆነው እንዲቀበሩ ይደረጋል፡፡ ሬሳዬን ወስዳችሁ ከቤተሰቦቼ መካነ መቃብር ዳር ቅበሩኝ ብሎ ከተናዘዘም ቃሉ (ኑዛዜው) ይከበራል፡፡ ጥፍሩ፣ የፂሙ እና የራሱ ፀጉር ብቻ ተመርጦ ወደ ቤተሰቡ መካነ መቃብር ለምን እንደሚመጣ አቶ መኮንን የተባሉ መረጃ አቀባይ "…እነዚህ ሦስቱ ነገሮች በቶሎ አይበሰብሱም፣ ወይም ወደ አፈርነት አይቀየሩም፡፡ ስለዚህ ብዙ ጊዜ (ለረጅም ጊዜ) በአፈር ውስጥ የመቆየት እድሜ ስላላቸው መጥተው ሲቀበሩ የሟች አስክሬን እንደመጣ ይቆጠራል፣ ሌሎች ግን በቀላሉ ሊበሰብሱ እና ወደ አፈርነት ሊቀየሩ ይችላሉ›› በማለት ገልፀዋል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት፣ 23/2005)

ለመቅበር ከተለያዩ አካባቢዎች ተሰብስበው የመጡት ሰዎች አስከሬኑን አጅበው ወደ መካነ መቃብሩ ስፍራ ይሸኛሉ፡፡ በተደጋጋሚ ለመግለፅ እንደሞከርኩት የመቃብሩ ቦታ ከሟች መኖሪያ ብዙም አይርቅም፡፡ በመሆኑም ከተመረጡ ቀባሪዎች ውጪ ማንኛውም ሰው ደኑ ውስጥ ገብቶ ሊቀብር አይችልም፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉት መረጃ አቀባይ እና ከ1992 ዓ.ም ጀምሮ በቀብር ስርዓት ላይ ሲሳተፉ የነበሩ አንጋፋ አዛውንት የአቀባበሩን ስርዓት እንደሚከተለው ይገልፁታል፡፡ "አዛውንቶች የሚቀበሩት ከሌሎች መቃብሮች (ሴቶች፣ ወጣቶች እንዲሁም ህፃናት) ተለይተው ነው፡፡ ወንዶች (አዛውንቶች) ከፍ ያለ ቦታ ላይ ተፈልጎ ይቀበራሉ፡፡ ሴቶች ደግሞ ታች (ዝቅተኛ ቦታ ላይ) ተፈልጎ ይቀበራሉ፡፡ ይህ የሚደረገው በሁሉም ነገሮች

ወንዶች የበላይ ናቸው፤ ቤተሰብን ያስተዳድራሉ፤ ሀገርን ይመራሉ፤ የእምነት አባት (መሪ) ይሆናሉ። ሴሎች ግን አይችሉም።" በማለት ይገልፃሉ። (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት፣ 14፣2005)

ከዚህ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለውም ወንዶችን የበላይ ሴሎችን ደግሞ የበታች አድርጎ የማሰብ ሁኔታ እንዳለ ነው። መኖሩ ብቻም ሳይሆን ከሞቱ በኋላም ይህ አስተሳሰብ በብሔረሰቡ ዘንድ እንደሚቀጥል እና ቋሚ ሆኖ እንደሚኖር ያሳያል።

ሴቶች እና ሕፃናት ከፍተኛ ቦታ ተፈልጎ ቢቀበሩስ ምን ችግር አለው? ብየ ለጠየኳቸው ጥያቄ እኒህ ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉት መረጃ አቀባይ "ሁሉም ነገር ተበላሸ! አበቃልን! ... ሚስት ለባሏ፣ ህዝብ ለመሪው አይታዘዝማ! ባህል ይጠፋላ! ፈጣሪ ይቆጣላ!" ብለውኛል።

የቀብር ስርዓቱ በወንዶች ከተጠናቀቀ በኋላ ሁሉም ሰዎች ተሰብስበው ወደ ሟች ቤት ይሄዳሉ።

### 4.3.3 ከቀብር በኋላ

የእድሜ ባለፀጎች ከተቀበሩ በኋላ እንደ ሟቹ የሃብትና ንብረት ሁኔታ የእርድ ስርአት እንደሚኖር በ (4.3.1) ላይ ገልጫለሁ። ሟቹ ሐብታም ከሆነ ከብት ታርዶ እስከ ሰባት ቀን ድረስ እየተጨፈረ ሊቆይ ይችላል። ሐብት ከሌለው ደግሞ ጎረቤቶች በሚያዋጡት ምግብ የሩቅ ሰዎች እንዲሸኙ ይደረጋል። ወጣቶች ደግሞ በህብረት እየጨፈሩ እስከ ሰባት ቀን ይቆያሉ። ‹‹ከቀብር በኋላም ሆነ ሰዎቹ ከሞቱበት ጊዜ ጀምሮ ‹‹ኩሊት››[18] የሚሉት የጭፈራ አይነት ይጨፈራል። ብዙ ጉልበትና ሐይልን ስለሚጠይቅ በአብዛኛው ወጣቶች ተሰባስበው ይጨፍራሉ" ሲሉ አቶ ግርማ ግዥ ገልጸውልኛል። (ቃለመጠይቅ፣ ጥር፣03/2005)

ምስል 7፡ ከቀብር በኋላ በሟች ቤት ግቢ ወጣቶች በህብረት ሲጨፍሩ

[18] ‹‹ኩሊት›› ከጭፈራ አይነቶች አንዱ ሲሆን የእድሜ ባለፀጎች ሲሞቱ የሚጨፈር ጭፈራ ነው። ጋሻ እየተመታ ጦር እየተሰበቀ በሐዘን ይልቅ ደስታን የሚያመለክት የጭፈራ አይነት ነው። ኩሊት ወጣቶች ክብ በመስራት የሚጨፍሩት ጭፈራ ነው። በዚህ የጭፋራ አይነት ሴቶች (ኮረዶችም) ይሳተፋሉ።

ከሰባት ቀን በኋላ የለቅሶው ፍፃሜ ይሆናል፡፡ ፍፃሜውን የሚያሳውቁትም የአካባቢው ሽማግሌዎች ናቸው፡፡ ከእንግዲህ በኋላ ሁላችንም ወደየስራችን እንመለስ፤ አዝነናል፤ ጨፍረናል፤ የሟችን ነፍስ መልካም ይግጠማት፤ ላለነውም የእነሱን እድሜ ይስጠን፤ ፈጣሪ ከብቱን ይባርክ፤ ሀገርን ይባርክ፤ የተወለደው ይደግ፤ የተዘራው ያፍራ፤ ወዘተ እያሉ በመመረቅ ለቅሶው (ጭፈራው) እንዲቆም እንደሚያደረጉ አቶ አንዱዓለም ጋይ የተባሉ መረጃ አቀባይ ይገልፃሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት 13/2005)

## 4.4 የወጣቶች የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ

ይህ አራተኛው የለቅሶ ክዋኔ አይነት ነው፡፡ በዚህ ስር የሚካተቱት የቤንች ብሔረሰብ ተወላጆች እድሜያቸው ለአቅመ አዳም ወይም ሔዋን የደረሱ፤ በጋብቻ ተሳስረው ነገር ግን ያልወለዱትን ነው፡፡ በአብዛኛው ከ14 ዓመት እና ከዚያ በላይ ያሉትን የብሔረሰቡ ተወላጆች የሚያጠቃልል የለቅሶ አይነት ነው፡፡

ወጣቶች የሚባሉት በማህበራዊ ግንኙነታቸው ገና ጀማሪዎች ናቸው፡፡ ስለ አለም ብዙ አላዩም፤ የህይወትን ውጣ ውረድ ሙሉ በሙሉ አልተካፈሉም፤ እንደ ሌሎች ትላልቅ ሰዎች ዘሮቻቸውን አልተኩም፡፡ በአጭሩ ከእነሱ የሚጠበቀውን በሙሉ ስላልጨረሱ በሚሞቱበት ጊዜ የለቅሶ ስርዓቱም ከሌሎች ይለያል፡፡ እያንዳንዱን የለቅሶ ክዋኔ ሂደት በመቀጠል እተነትናለሁ፡፡

### 4.4.1 ከቀብር በፊት

አንድ ጎረምሳ ወይም አንዲት ኮረዳ በሚታመሙበት ጊዜ ቤተሰቦቻቸው በጣም ይጨነቃሉ፡፡ ጭንቀቱ ከላይ ከጠቀስኳቸው የለቅሶ አይነቶች የበለጠና የተለየ ነው፡፡ ምክንያቱም ደግሞ እነዚህን ሰዎች (ወጣቶችን) ቤተሰቦቻቸው በሙሉ ከህመምተኛው ጎን ሆነው ጭንቀቱን ስለሚካፈሉ ነው፡፡ ሆኖም ህመምተኛው የማይድን መሆኑ ከታወቀ በቤት ውስጥ የተለያዩ ዝግጅቶች እንዲዘጋጁ ይደረጋል፡፡ ከዝግጅቶች መካከልም ምግቦችን (እንደ ጎደሬ፣ አምቾ፣ ጨሞ፣ ወዘተ) ማዘጋጀት፣ ድንኳን መስራት፣ እና የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡

በብሔረሰቡ ዘንድ የታመሙ ወጣቶች የማይድኑ ከሆነ እና ከሞቱ እንደሌሎች (ከአሁን በፊት እንደገለጽኳቸው) ሳይሆን ወዲያውኑ ይለቀሳል፡፡ ለዘመድ አዝማድ መልዕክት ይላካል፡፡ የሚላኩት ሰዎችም ወጣቶች ናቸው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ለቅሶው ብዙ ስለማይቆይ ቶሎ ቶሎ ሄደው በፍጥነት እንዲነግሩ እና ዘመድ አዝማድ ተሰብስበው መጥተው እንዲቀብሩ ነው፡፡

በምልከታ (አማን ከተማ፣ጥር፣ 20/2005) ጊዜ ለማየት እንደቻልኩት ሟቹ እድሜው 25 ዓመቱ ነው። ከአማን ሆስፒታል ነበር ሞቶ የወጣው። ይዘውት (ተሸክመውት) የመጡ ሰዎች በአብዛኛው የሟች ቤተሰብና የሟች የቅርብ ጓደኞች ናቸው። እንደሞተ ሁሉም በአንድ ላይ እየተነሱ እየወደቁ፤ እየዘለሉ አካላቸውን ሲጎዱ ተመልክቻለሁ። አስከሬኑ ከሟች መኖሪያ ቤት ሲደርስም መውደቅ እና መነሳቱ በስፋት ይስተዋላል። እየተነሱ እየወደቁ አካላቸውን ካልጎዱ ለሟች አላዘኑም ይባላሉ።



ምስል፡ 9 በሟች የተሰማቸውን ሀዘን በመነሳት በመውደቅ ሲገልፁ

ከቤት እንደተደረሰም ልክ እንደሌሎች የለቅሶ አይነቶች የእጥበትና የግንዘት ስርዓት ይፈፀማል። ግንዘቱን የሚፈጽሙት የሟች ቤተሰቦች ናቸው። የግንዘቱም ሆነ የእጥበቱ ሂደት ተመሳሳይ ስለሆነ እዚህ በዝርዝር መግለፁ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘሁትም።

በቤንች ብሔረሰብ ባህል ዘንድ የሞተው ልጅ ከአሁን በፊት እህል ዘርቶ እና አዝመራው አድጎ ከሆነ እህሉ ተቆርጦ በለቅሶው ጊዜ ሴቶች ይዘው ያለቅሳሉ። የዚህን ትርጉም አቶ ኩን ናካ የተባሉ መረጃ አቀባይ ሲገልጹ ‹‹ልጁ ወጣት ነው፤ ያዘመረውን አዝመራ እንኳ አልካወነ፤ መሞት አይገባውም ነበረ፤ ገና ብዙ አላየም፤ በተጨማሪ ደግሞ ለሚያይ ሰው የሟቹን እድሜ ለመግለፅ ነው፤ እህሉን ቆርጠን የምናለቅሰው›› ብለዋል። (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 07/2005)

ሟቹ የሞተው ጧት ከሆነ ከሰዓት (ከሰባት ሰዓት) ጀምሮ የቀብር ስርዓቱ እንዲከናወን ይደረጋል። ከሰዓት በኋላ ከሞተ ደግሞ በማግስቱ አራት ሰዓት አካባቢ እንዲቀበር ይደረጋል። ይህ የሚሆነውም ቀደም ብዬ በሌሎች የለቅሶ አይነቶች ለመግለጽ እንደሞከርኩት ለቅሶ በቤንች

ብሔረሰብ ዘንድ ትልቅ ማህበራዊ ጉዳይ ስለሆነ ሌሎች ሰዎች በቀብሩ እንዲገኙ ለማድረግ ታስቦ መሆኑን በቡድን ውይይት ጊዜ ለመረዳት ችያለሁ። በመሆኑም ከሰዓቱ አንፃር ታይቶ የመቃብር ጉድጓድ እንዲቆፈር ይደረጋል። የመቃብር ቦታው ከሟች ግቢ ብዙም አይርቅም። ጉድጓዱ ከተቆፈረ በኋላ ከበሮ እየተመታ ይለቀሳል። ለቀብሩም የአካባቢው ሰው እንዲዘጋጅ ይደረጋል።

### 4.4.2 በቀብር ጊዜ

በቤንች ብሔረሰብ ዘንድ ወጣት ሲሞት የተለየ የለቅሶ ስርዓት እንዳለው ለመግለፅ ሞክሬያለሁ። በምልከታ ጊዜ እንዳየሁት የሟች ንብረቶች (ልብሶች፣ የጌጥ እቃዎች፣ወዘተ) በሙሉ በቤተሰቦቹ ተይዞ ይለቀሳል። ለየት ያለውና በሌሎች የብሔረሰቡ የለቅሶ አይነቶች ያላየሁት የሟች የቅርብ ዘመዶች የሟቹን ኮት በመያዝና በመርፌ በማያያዝ በለቅሶው ክዋኔ ጊዜ ከቦታ ቦታ በመዘዋወር ሊቀብር ከመጣው ሰው ብር የሚሰበስቡበት መንገድ ነው።

ምስል 10፡ የሟች የቅርብ ዘመድ በሟች ልብስ ላይ መርፌ በመሰካት እየተንቀሳቀሰች ብር ስትሰበስብ

ይህንን ከላይ የተጠቀሰውን (ብር በመርፌ የማያያዝ) ባህል አስመልክተው አቶ አቤልና አቶ አለማየሁ የተባሉ መረጃ አቀባዮች እንደሚከተለው ይገልጹታል።

> *… ይህ ባህል በቅርብ ቀን የመጣ ነው። የመጣውም ከሸኮ ብሔረሰብ ይመስለኛል። ምክንያቱ ደግሞ በሸኮ ብሔረሰብ ዘንድ ሰው ሲሞት እንዲህ የማድረግ ባህል መኖሩን ስላየሁ ነው። የቤንች ብሔረሰብ ግን ከጥንት ጀምሮ እንዲህ አይነት ነገር ፈጽሞ አያውቅም። በቅርብ ከኢሕአዴግ ጀምሮ የመጣ ነው። ባህላችን አይደለም ይቅር እያልን ብንናገርም እስካሁን ሊቀር አልቻለም። በአንዳንዶቹ የለቅሶ አይነቶች ላይ እየቀነሰ ነው፤ በአንዳንዶቹ ደግሞ በብዛት ሰዎች እየተንቀሳቀሱ ብር ሲሰበስቡ ይታያል፤ (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 07/2005)*

በተያያዘም ለቅሶ ለመድረስ ከሩቅ የመጡ ሰዎች በሟች ልብስ ላይ ብር በመርፌ አያይዘው ካላስቀመጡ አላዘኑም፤ በመሞቱ ደስተኞች ናቸው፤ ተብሎ እንደሚታሰብ ይገልፃሉ። በምልከታም እንዳየሁት እያንዳንዱ ሰው የቻለውን ያህል ብር እንደሚሰጥ እና የሰጠው የብር

መጠን ታይቶ የተለየ አቀባበል[19] እንደሚደረግለት ተመልክቻለሁ። ብሩም ለለቅሶው ማስኬጃነት ይውላል። ሰዎች ከቀብር ሲመለሱ የሚጠጡት ቡና፣ ጠላ፣ አረቄ፣ ጠጅ ወዘተ. ተገዝቶ እንዲስተናገዱ ይደረግበታል።

ወጣቶች ሲሞቱ በጣም ይለቀሳል። ቤተሰብ የገዛ አካላቸውን በስለት ይጎዳሉ። ወዳጅ ዘመድ ደግሞ በመነሳት በመውደቅ በሟች የተሰማቸውን ሐዘን ይገልፃሉ። ይህ የሚሆንበትም ምክንያት ሟቹ (ቿ) ገና ያላየ (ች)፣ ወልዶ ያልሳመ(ች)፣ ወዘተ በመሆናቸው መሆኑን በቡድን ውይይት ጊዜ ለመረዳት ችያለሁ።

ከሟቹ ጋር የተያያዙ ግጥም ነክ ጉዳዮችም የለቅሶው አንድ አካል ናቸው። ለምሳሌ በአንድ የለቅሶ ስርዓት ጊዜ የሚከተለውን ግጥም የሟች እናት በልጇ ሞት የተሰማትን ሀዘን አስመልክታ ስትገጥምና ታዳሚውን ስታስለቅስ ተመልክቻለሁ።

| <u>ቤንችኛ</u> | <u>አማርኛ</u> |
|---|---|
| እርሽ ቦጋ እርሻም ሀይቃ (ባኣ) | ልጄ በልጅነቱ ተቀጨ |
| ኢሳጋ ንያዕ አጥን አታርጉይስትያ | እንደሰው አልሆነ፣ |
| ማሽታይድ ኡትውዋርጉኤ | ትዳር አልያዘ፣ |
| ንያዕድ ሳርጉኤ | ልጅም አልወለደ፣ |
| ኤናቃይፁሽጋ ሻብይስ | ያረስከውን አዝመራ፣ |
| ሙዕክርጥይስታ ነናሻዓ | ሳትከውን ቀረህ፣ |
| ታይስ አፈርቅን ሀስማኬ | እኔን ያስቀድመኝ፣ |
| ምያት ታና በቃ | ብዙ አይቻለሁ |
| ንያዕድ ታና የለ | ልጅም ወልጃለሁ |
| ታጋ ከምስይድ ታና ሀስማሀ | ዘርም ተክቻለሁ |
| ታይስ አፈርቅን ሀስማኬ | እኔን ያስቀድመኝ.... |

[19] ለምሳሌ አንድ ሰው የሰጠው ብር ብዙ ከሆነ የተለየ ዝግጅት ወደተዘጋጀለት ቤት ተወስዶ እንዲመገብ ይደረጋል። አነስተኛ ከሆነ ደግሞ አንፃራዊ ወደሆነው ቤት እንዲወሰድ ይደረጋል። ይህ ባህል በለቅሶ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በሚዛን ቆይታዬ (በሁለት አመት) በሰርግ ስርዓት ጊዜም እንደሚደረግ ለማየት ችያለሁ። እኔም አንዱ ተሳታፊ ነበርኩ። በሰርግም ጥሩ ብር የሰጠ ሰው ለብቻው የተለየ ድግስ ይዘጋጅለታል።

ከዚህ ግጥም መረዳት እንደሚቻለው እናት በልጇ ሞት ማዘኗን እና በእሱ ፋንታ እሷ ብትሞት ደስ እንደሚላል የሚገልፅ ነው። የሞተው ልጅ ትዳር ያልመሰረተ፣ ልጅ ያልወለደ፣ ካሁን በፊት የዘራውን አዝመራ ያልከወነ ወዘተ. ገና በልጅነቱ የሞተ እንደሆነ ከእናቱ ንግግር መገንዘብ ይቻላል። በመሆኑም ይህን አይነት አሳዛኝ ታሪክ ያለው ልጅ ሲሞት የመጣው ሰው በሙሉ በጣም ያዝናል፤ ያለቅሳል። እናትም (ሙሾ አውራጇ) አልቅሳ ሌሎች እንዲያለቅሱ እና እንዲያዝኑ ታደርጋለች።

ሌላው ደግሞ ወጣቶች ክብ ስርተው የሚጨፍሩት ጭፈራ ነው። ጭፈራው እንደሌሎች የለቅሶ የጭፈራ አይነቶች ሳይሆን በሟቹ ማዘናቸውን የሚገልፅ ነው። የክቡ ትርጓሜ ከአሁን በፊት ሟች ከኛ ጋር አብሮ ሲጨፍር ነበር። በሰርግ ቤቱ፣ ሰው ሲሞት፣ ስንጫወት ወዘተ. አይለየንም ነበር፤ የሚል ትርጉም አለው። ወጣቶችም ከበሮ በመምታት፣ ጦር በመስበቅ፣ ቶሆና ፍርግን[20] እየነሩ፤ ሴቶች ደግሞ ቃጭል እያቃጨሉ ይጨፍራሉ።



ምስል፡11 ሴቶች በቃጭል (ቶሪ) ወንዶች ደግሞ የተለያዩ ቁሶችን በመያዝ ሲጨፍሩ

[20] ቶሆና ፍርግን፡ የእስትንፋስ መሳሪያዎች ናቸው። ቶሀ በግምት አንድ ሜትር የሚደርስ ቁመት ያለው ሲሆን ከዋንዛ እንጨት የሚሰራ ነው። ፍርግን ደግሞ አንድ ስንዝር ያህል ርዝመት ያለው ሆኖ ከሸንበቆ የሚሰራ የእስትንፋስ መሳሪያ ነው። ቃጭል የሚባለው ደግሞ ልጃገረዶች በለቅሶ ጊዜ እግራቸው ላይ በማሰር የሚጨፍሩት ነው። የሚሰራውም ከቆርቆሮ ወይም ከኮርኪ ነው።

ከእነዚህ ቁሶች (ጦር፣ ከበሮ፣ ቶሀ፣ ፍርግን እና ቃጭል) ጋር በተያያዘ አቶ አቤል የተባሉ መረጃ አቀባይ በቃለ መጠይቅ ጊዜ ሲገልፁ "... በለቅሶ ጊዜ እነዚህ መሳሪያዎች ለለቅሶው ድምቀት እንዲሰጡ ተብለው ነው የሚዘጋጁት፡፡ እነዚህ ቁሶች ከሌሉ ለቅሶው አይደምቅም፡፡ ለቅሶው ካልደመቀ ደግሞ ነውር ነው፡፡ የሟች ቤተሰቦች እኛን (ታደሚውን) ያኮርፋሉ፤እኛም ለቅሶ ሲኖረን እንዲደምቅ አሁን ማገዝ አለብን፤ ስለዚህ ነው በእነዚህ መሳሪያዎች ታግዘን የምንጨፍረው፤ በማለት ይገልፃሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 07/2005)

እንዲህ እየተደረገ የሟች አስከሬን የመቀበሪያው ሰዓት ሲደርስ ሴቶች እስከመቃብሩ ቦታ አድርሰው ሲመለሱ ወንዶች ይቀብራሉ፡፡ ሴቶች ሲቀበር የማይመለከቱበት ምክንያት እንደ አቶ ክፍሌ ገለጻ "ቦታው የቤተሰብ መቃብር ነው፡፡ ከቤተሰቡ መካከል አንድ ባላባት ወይም ባለውቃቢ ተቀብሮበት ሊሆን ስለሚችል የዛን ባላባት ወይም ባለውቃቢ መንፈስ (የሙት መንፈስ) ላለመረበሽ ታስቦ ነው፡፡ ሴቶች ደግሞ ከማልቀስ ወደ ኋላ ስለማይሉ ለዚህ ነው እንዳይሔዱ የሚደረገው፡፡ ከሄዱ ደግሞ መንፈሱ ተቆጥቶ ሊያሳምማቸው ወይም ሊገላቸው ይችላል" በማለት ይገልፃሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 07/2005)

### 4.4.3 ከቀብር በኋላ

ከቀብሩ በኋላ ወጣቶች ተሰብስበው እስከ ሰባት ቀን ድረስ ይጨፍራሉ፡፡ እስከ ሰባት ቀን ድረስ የሚቆየውም በተለያዩ ምክንያቶች ቀብሩ ላይ ያልተገኙ ሰዎች መጥተው እንዲደርሱ ለማድረግ መሆኑን በቡድን ውይይት ጊዜ አቶ ክፍሌ ገልጸውልኛል፡፡ (የካቲት 16/2005)

ወጣቶች ከተቀበሩ በኋላ ከሌሎች የለቅሶ አይነቶች የተለየ ስርዓት የለም፡፡ ለየት የሚለው እና በሌሎች የለቅሶ አይነቶች የሌለው እስከ ስድስት ወር ድረስ የሟች እናት ከልጇ መቃብር በየጊዜው እየሄደች የማልቀሷ ሁኔታ ነው፡፡ እናት በልጇ ሞት ማዘኗን ከምትገልፅባቸው መንገዶች አንዱ መሆኑን በቡድን ውይይት ጊዜ (የካቲት፣ 16/2005) ለመረዳት ችያለሁ፡፡ ከስድስት ወር በኋላ ደግሞ የሟቹን ንብረቶች (አልባሳትን) ከመቃብሩ ላይ አስቀምጣ ትመጣለች፡፡ ይህም የሚደረገው "ካሁን በኋላ ሀዘኑ ይበቃኛል፤" የሚል ትርጉም እንዳለው አቶ ባላካኝ የተባሉ መረጃ አቀባይ ገልጸውልኛል (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 03/2005)፡፡ በተያያዘም ወ/ሮ ዘነበች ኮምቴስ የተባሉ መረጃ አቀባይ ከራሳቸው ልምድ ጋር አያይዘው እንደሚከተለው ይገልፁታል፡፡

*...እኔ የዛሬ ሶስት አመት አካባቢ ልጄ በወባ በሽታ ሞተ፡፡ ቀብረን ከመጣን ጀምሮ እስከ ስድስት እና ሰባት ወር ድረስ ከልጄ መቃብር ሳልደርስ ውየ አላውቅም፡፡ መቃብሩ ዳር ተቀምጬ*

*አለቅሳለሁ። የምሔደው ልጄን ስለምወደው ነው። ጠዋት የሄድኩ ከሰዓት እመለሳለሁ። ስሄድ ደስ ይለኛል። ያገኘሁት ሁሉ ይመስለኛል።...ባለቤቴ ሲቆጣኝ ልብሶቹን ሰብስቤ ወስጄ መቃብሩ ላይ አስቀምጬ መጣሁ። ከዚያ በኋላ ሂጄ አላውቅም።" በማለት ይገልፃሉ። (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 12/2005)*

ልብሶቹ መቃብሩ ቦታ ላይ የሚጣሉበት (የሚቀመጡበት) ምክንያት ደግሞ እናትየዋ ልብሶቹን እያየች እንዳታለቅስ ታስቦ መሆኑን አቶ ተሾመ ይገልፃሉ። (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት 14/2005) ከስድስት ወር በኋላ የወጣቶች የለቅሶ ስርዓት ያቆማል።

## 4.5 የሕፃናት የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ

የሕፃናት የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ከሌሎች የቤንች የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔዎች የተለየ ነው። በዚህ ስር የሚካተቱት የብሔረሰቡ ተወላጆች በአብዛኛው እድሜያቸው ከዜሮ አመት እስከ አስር እና አስራ አንድ ዓመት ድረስ ያሉትን ነው። እነዚህ ሕፃናት በሚሞቱበት ጊዜ የለቅሶ ክዋኔው ብዙም አይደምቅም። እንደሌሎች የለቅሶ አይነቶች ብዙ ዝግጅት አያስፈልግም። አስከሬን የማሳደር ስርዓትም አይኖርም። ለዘመድ አዝማድ ትኩረት ሰጥቶ መርዶ መላክም አይታሰብም። የእርድም ሆነ ሌሎች ተያያዥ የምግብ ዝግጂቶች አይኖሩም። እነዚህን ከላይ የዘረዘርኳቸውን ጉዳዮች ጠቅለል አድርገው አቶ አቤል እና ቄስ ሳሙኤል የተባሉ መረጃ አቀባዮች እንደሚከተለው ይገልፁታል።

*... የሕፃናት ለቅሶ ከሌሎች ይለያል። አይለቀስም። አልፎ አልፎ ቤተሰቦች ያለቅሳሉ። የሟቹ እድሜ ከፍ ያለ ከሆነ... ሰባት፣ ስምንት፣ አስር ዓመት ከሆነ በመጠኑ ይለቀሳል። ሰውም ሂደ ሊደርስ ይችላል። አለመድረስም ይችላል። ብዙም ችግር የለውም። በመጠኑ በሚለቀስበት ጊዜም ቶሀ እና ፍርግን እየተነፋ ነው። ቤተሰቡም የሟችን ልብስ፣ የሚጠጣበትን ቀንድ ይዘው ይጨፍራሉ። ወዲያው ለተወለደ ወይም እስከ አምስት ዓመት አካባቢ ለሆነው ሕፃን ግን አይለቀስም። ምክንያቱም እናትየዋ ገና መውለድ ስለምትችል ፈጣሪዋን ማማረር የለባትም፣ ተብሎ ስለሚታሰብ ነው። አምርራ ካለቀሰች ደግሞ ፈጣሪዋ ለወደፊት ልጅ ላይሰጣት ይችላል፣ ተብሎ ስለሚታሰብ ትኩረት አንሰጠውም። (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 07 እና 18/2005 በተከታታይ)*

እናትም ሆነች ሌሎች ቤተሰቦች ፈጣሪያቸውን ማማረር የለባቸውም፣ ስለሚባል በህፃናት ለቅሶ ጊዜ ብዙም እንደማይለቀስ ከአቶ አቤል እና ከቄስ ሳሙኤል መረዳት ይቻላል። እግር ጥሏቸው ወይም የቅርብ ጎረቤት የሆኑ ሰዎችም ከለቅሶው ቤት ደርሰው ኑረው ከቤት ሲወጡ "ጌታ ይተካላችሁ" ብለው በመመረቅ ይሄዳሉ። ዘመድ አዝማድ አልሰማም ተብሎ ስለማይጠበቅ እንደሞቱ ወዲያውኑ ሊቀበሩ ይችላሉ። ከቀብር መልስም የተለየ ዝግጅት አይኖርም። ምክንያቱም ሟቹን ለመቅበር የሚመጣ ሰው ስለማይኖር ነው።

# 5. ማጠቃለያ እና ይሁንታ

## 5.1 ማጠቃለያ

በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ የቤንች ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ምን እንደሚመስል ተገልጿል። በቤንች ብሔረሰብ አንድ ሰው ሲሞት ሟች በብሔረሰቡ ዘንድ ካለው ማህበራዊ ደረጃ፣ ከፆታ እና ከሟች እድሜ አንፃር የተለያዩ የለቅሶ ስርዓቶች ይካሔዳሉ። የብሔረሰቡ የለቅሶ ዓይነቶችም በአምስት ክፍሎች ከፍሎ ማየት እንደሚቻል ተገልጿል። እነሱም የባለቃልቻ፣ የባላባትና ሚያንግ፣ የእድሜ ባለፀጎች፣ የጎልማሶች እና የሕፃናት የለቅሶ ስርዓት አይነቶች ናቸው። ከአምስቱ የብሔረሰቡ የለቅሶ አይነቶችም በወጣቶች የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ጊዜ በጣም እንደሚለቀስ፤ በአንፃሩ ደግሞ የእድሜ ባለፀጎች የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ በጭፈራ ታጅቦ አስከሬናቸው እንደሚሸኝ ለመረዳት ተችሏል።

እያንዳንዱ የለቅሶ አይነት የራሱ የሆኑ ዝግጅቶችን እና ክዋኔን የሚጠይቁ፤ የራሱ የሆነ የጊዜ ርዝመት ያሉት፤ እንደሆነ በዝርዝር ተገልጿል። ለዚህ የዝግጅት እና የጊዜ መርዘም ማህበረሰቡ ይሁነኝ ብሎ ከታሪኩ፣ ከአስተሳሰቡ፣ ከእምነቱ እና ከፍልስፍናው የቀዳው፤ የነበረና አሁንም ያለ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

በእያንዳንዱ የሟች አይነትም የሟቹ (ቿ)ን ማንነት፣ የዘር ሀረግ፣ እምነት፣ ስነ ምግባር ወዘተ የሚገልፁ የሙሾ ግጥሞች እንደሚከወኑ በጥናቱ ታይቷል። እነዚህን የሙሾ ግጥሞች የሚደረድሩት የሟች ቤተሰቦች፣ ከሟች ጋር የቅርብ ግንኙነት የነበራቸው ሰዎች መሆናቸውም ታውቋል።

እንደ ሟች እድሜ እና ማህበራዊ ደረጃ የብሔረሰቡ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ደረጃና አቅም ምን እንደሚመስል፣ ክዋኔው በምን ላይ የተመሰረተ እንደሆነ (የእርድ፣ የድግሱ ሁኔታ፣ የለቅሶው የቆይታ ጊዜ፣ የጠባቂዎች፣ የቀባሪዎች፣ የገናገሮች እና የመርዶ ነጋሪዎቸ ማንነት) በምን እና በማን ላይ የተመሰረተ እንደሆነ በዝርዝር ተካቷል። በተያያዘም ለቅርብ ጎረቤቶች ሰው መሞቱን ለማሳወቅ የቁሶች (ከበሮ፣ ጥይት እና ጥሩምባ) ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ተገልጿል።

እናት እና አባት በሚሞቱበት ጊዜ የበኩር ልጅ ድርሻ ከፍተኛ እንደሆነም ሌላው በጥናቱ የተገለፀ ጉዳይ ነው። የበኩር ልጅ የአባቱን ስልጣን ሊረከብ ይችላል። አስከሬን ከቤት በሚወጣበት ጊዜ

የአባቱን ወይም የእናቱን መሞት እና ሟች ቀባሪ እንዳለው ወይም እንዳላት ለመመስከር አስከሬኑን አራት ጊዜ በመንካት ለሌሎች ቀባሪዎች ይገልፃል።

የብሔረሰቡ የመቀበሪያ ቦታም መንክር እንደሚባል እና ከሟች ግቢ ብዙም የማይርቅ የቤተሰብ መቃብር እንደሆነ ተመልክተናል። ይህ መንክር የሚባለው የመቃብር ቦታም በእድሜ ጠገብ ዛፎች የተሸፈነና ዛፎቹን መቁረጥም ሆነ ሌሎች የቤት እንስሶችን ማስገባት የተከለከለ መሆኑን በቆይታየ ማረጋገጥ ችያለሁ።

በቤንች ብሔረሰብ ዘንድ ለቅሶ ትልቅ ማህበራዊ አንድነትን ማጠናከሪያ ስርዓት ነው። በብሔረሰቡ እምነትና አስተሳሰብ ዘንድ ለሰርግና ለልደት ተጠርቶ መቅረት፣ ለደቦ ስራ ተለምኖ ሳይመጡ መቅረት፣ እንዲሁም በሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች አለመሳተፍ በማህበራዊ ኑሮ ላይ የሚያስከተለው ችግር ብዙም አይኖርም። ነገር ግን በለቅሶ ጊዜ አንድ የማህበረሰቡ አባል አለመሳተፍ ወይም ሂዶ የተሰማውን ሀዘን አለመግለፅ ከማህበራዊ ኑሮ መገለል ብቻም ሳይሆን እስከ ከፍተኛ ቅጣት ሊያስቀጣ ይችላል። ማህበራዊ አንድነትን ከማስጠበቅ እና ከማጠናከር በተያያዘ በለቅሶ ውስጥ ሟችን መቅበር ብቻ ሳይሆን ከክዋኔው ጋር ተያይዘው የተለያዩ መልዕክቶች ከትውልድ ትውልድ እንዲተላለፉ ይደረጋል። ከእነዚህም መካከል የብሔረሰቡ የታሪክ ተሳታፊነትን የሚያፀኑ፣ የብሔረሰቡ ቋሚ የሆነ ሀገረሰባዊ የስልጣን ሽግግርን የሚያበስሩ፣ የብሔረሰቡን ወይም የጎሳውን የዘር ግንድ መሰረት የሚገልፁ፣ የብሔረሰቡን ሐገረሰባዊ እምነት መንገርና ማስጠበቅ፣ የሚሉት ጉዳዮች በለቅሶው እንደሚተላለፉ ለማየት ተችሏል።

በብሔረሰቡ ዘንድም ሰው በሚሞትበት ጊዜ ስሜታቸውን የሚገልፁት አካልን በስለት በማድማት፣ በመነሳት በመውደቅ፣ ፀጉርን በመላጨት፣ ጥቁር ልብስ በመልበስ፣ መሬት ላይ በመተኛት፣ እስከ ስድስት ወር ድረስ በሟች መቃብር በመመላለስ፣ ወዘተ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል።

## 5.2 ይሁንታ

የብሔረሰቡ እንግዳ ተቀባይነት እና መስተንግዶ የሚያውቅ እንዲሁም የሚያውቁትን ለመንገር ያላቸው ቀና አስተሳሰብ ይሁን የሚባሉ ጉዳዮች ስለሆኑ ለሌሎች መሰል አጥኝዎችም ይህ ድርጊታቸው ተጠናክሮ ቢቀጥል መልካም ነው።

ስለ ብሔረሰቡ ታሪክ የሚያስረዱ በመጽሐፍ መልክ የተዘጋጁ መረጃዎች ባለመኖራቸው፤ ተጨባጭ መረጃ ለማግኘት ስለማይቻል እና ለአጥኝዎችም አስቸጋሪ ስለሆነ የዞኑም ሆነ

የወረዳዎች የባህል እና ቱሪዝም ኃላፊዎች የብሄረሰቡን ታሪክ አዋቂዎች ዋቢ በማድረግ የሚያዘጋጁበት ሁኔታ ቢኖር። ይህን እንድል ያስቻለኝም አብዛኛዎቹ የቤንች ሽማግሌዎች (በተለይም ደቡብ ቤንች ወረዳ ያሉት) ስለ ብሔረሰቡ ታሪክ በጠየኳቸው ጊዜ የሚሰጡኝ ምላሽ እነሱ ከሞቱ በኂላ የብሔረሰቡ ታሪክ የማይገኝ መሆኑን ስለተረዳሁ ነው።

የቤንች ብሔረሰብ ባህል በተለይም (ለቅሶ፣ ሰርግ፣ ባህላዊ እምነቶች እና ከበራዎች) የሚደረጉ ዝግጅቶች በሙሉ ለአጥኝዎች ክፍት አይደሉም። ነገር ግን የተጠየቀውን ያህል ገንዘብ የሚከፍል ሰው ዝግ የሆነውን ባህል ሊመለከት ይችላል። በመሆኑም የአጥኝዎች ዋና ዓላማ የብሔረሰቡን ታሪክ እና ባህል ዘግቦ ማቆየት መሆኑ ታውቆ፤ ማንኛውም አጥኝ መመልከት የሚችልበት ሁኔታ ቢፈጠር መልካም ነው።

በዞኑ ብዙ የውጭ ሀገር ጎብኝዎች እና የባህል አጥኝዎች መኖር ለሀገር ውስጥ አጥኝዎች እኔ እንዳየሁት ችግር ፈጥሯል። ስለዚህ አንዳንድ መረጃ አቀባዮች የሀገር ውስጥ አጥኝዎችን የሚጠይቁት የገንዘብ መጠን የውጮች በሚከፍሏቸው መጠን ስለሆነ የሚመለከተው አካል ቢመለከተው እና የግንዛቤ ስራ ቢሰራ የተሻለ ይመስለኛል።

ይህ ጥናት ትኩረት ባደረገባቸው ወረዳዎች የሚገኙ የባህል እና ቱሪዝም ጽ/ቤት ቢሮዎች ውስጥ ያሉ ቁሳዊ ባህሎች እንደ ጋሻዎች፣ ጭራ (ያል) ፣ክራር (ሾንጋ)፣ ጥሩምባ (ቶህ)፣ ባህላዊ መጠጫዎች (ፔል)፣ የመሳሰሉት ቁሶች የተቀመጡበት ቦታ ስለማይመች እና ከፊሎቹ እየተሰባበሩ፣ ከፊሎቹ ደግሞ ቅርፃቸውን ቀይረው ስለተመለከትኩ፤ እነዚህ ቁሶች የብሔረሰቡን ማንነት ጠብቆ ከማቆየት አኳያ ያላቸው ሚና ከፍተኛ ስለሆነ የሚመለከተው አካል ይህንን ተገንዝቦ የተሻለ ቦታ መርጦ እንዲያስቀምጣቸው ቢደረግ ጠቀሜታው ጉልህ ነው።

## ዋቢ ጽሑፎች

ሐረገወይን ድፋባቸው:: "የክስታንኛ የለቅሶ ግጥሞች::" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ የባችለር ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ (ዲማጽ)፣ 1974::

ሕይወት አበሩ:: "የመኢኒት ብሄረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርአት ክዋኔ::" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ 2003::

ማናዬ እንግዳው:: "በደብረ ማርቆስ ከተማና አካባቢዋ የሚገኙ የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ንጽጽራዊ ጥናት::" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ 2005::

ምንታምር ልንገርህ:: "የቤንች ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ 2003::

ሞገስ ሚካኤል:: "በላይ አርማጭሆ ወረዳ የሚደረግ የቀብር ስነስርአት፣ በስርአቱ ላይ የሚካሄድ ቀረርቶ፣ ፉከራና ክዋኔው::" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ 2002::

ሽመልስ አክሊሉ:: "የቋሪት ወረዳ የለቅሶ ስነስርአትና የግጥሞች ይዘት ትንተና::" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ዲማጽ፣ 1997::

ቄስ ሳሙኤል ዳልቴት:: የቤንች ብሔረሰብ ታሪካዊ አመጣጥ:: ሚዛን ተፈሪ፣ 2000:: (ያልታተመ)::

በሪሁን መንግስቱ:: "የወየታና የፉከራ ግጥሞች ክዋኔና ይዘት ትንተና::" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ 2004::

ቤንች ማጂ ዞን ባህል እና ኢንፎርሜሽን ቢሮ:: የቤንች ብሔረሰብ ታሪክ እና ባህል ገፅታዎች:: ሚዛን ተፈሪ፣ 1999:: (ያልታተመ)

ተራመድ ጥላሁን:: "የቤንች ተረት እና ምሳሌዎች ቅርፅና ይዘት ትንተና" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ዲማጽ፣1992::

ኩንዲሳ ፈርኪ:: የቤንች ብሔረሰብ ባህልና ጥናት:: ሚዛን ተፈሪ፣ በቤንች ማጂ ዞን ባህልና

ማስታወቂያ የተዘጋጀ፣ 1988:: (ያልታተመ)

አስቴር አንጀሎ:: "የጋሞ ብሄረሰብ የለቅሶ ስርአት::" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ዲማጽ፣ 1997::

አቡበከር ሀሰን:: "የሺናሻ ብሄረሰብ የሀዘንና የተገኮር ስርአት ክዋኔ::" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ዲማጽ፣ 1998::

ወርቃየሁ አረጋ:: "የአዊ ሕብረተሰብ ሴንቲ (የለቅሶ ስርአት) እና የአውኚ ዚንዚምኚ (የሙሾ) ግጥሞች ይዘት ትንተና::" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ዲማጽ፣ 1995::

ዘላለም ፋንቱ:: "የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ በበና ፀማይ ወረዳ::" በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ 2004::

ዘሪሁን አስፋው:: *የስነ-ጽሁፍ መሰረታውያን*:: አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣1992::

የሚዛን አማን ከተማ አስተዳደር:: ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት የ2004 ዓ.ም የ3ኛው ሩብ አመት እቅድ ክንውን አፈጻጸም ሪፖርት:: ሚዛን፣ 2004:: (ያልታተመ)

የሚዛን አማን ከተማ አስተዳደር:: ግብርና ጽ/ቤት የ 2004 ዓ.ም አመታዊ ሪፖርት:: ሚዛን፣ 2003:: (ያልታተመ)

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር:: *የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት*:: አዲስ አበባ፣ ባናዊ ማተሚያ ቤት፣ 6ኛ ዕትም፣ 1992::

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል:: *አማርኛ መዝገበ ቃላት*:: አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1993::

*የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦና ሕዝቦች ፕሮፋይል*:: በብሔረሰቦች ምክር ቤት በባህልና ቋንቋ ታሪክና ቅርስ ጥናት ተቋም የተዘጋጀ፣ ሀዋሳ፣ ፍቅረ ሳላም ማተሚ ቤት፣ 2001::

ዳምጠው በቀለ:: "በደብረዘይት ከተማ የሙሾ ግጥም አይነቶች::" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣ ዲማጽ፣1996::

ጌታመሳይ ግዛው:: "የሸናሻ ብሔረሰብ የቀብር ስርዓተ ክዋኔ ከፎክሎር ዘውጎች አንፃር"

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣ ዲማጽ፣ 2002።

ግርማ ግኘ። የቤንች ብሔረሰብ አመጣጥ ታሪክ። ሚዛን ተፈሪ፣ 1999። (ያልታተመ)

ፈለገሕይወት ዘገየ። "በባንጃ ሸኩዳድ ወረዳ የቀብር ስነ ስርዓትና የለቅሶ ግጥሞች ስብስብ ይዘት ትንተና።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ዲማጽ፣ 1997።

ፈቃደ አዘዘ። "የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች አፋዊ ኪነተቃል ጥናት።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለሴሚናር የቀረበ፣ 1970 (ያልታተመ)።

Bauman, Richard. *Story, Performance and Event*. Contextual Studies of Oral Narrative. Cambridge: Cambridge University Press, 1986.

Bauman, Richard. *Verbal Art as Performance*. Rowley, Mass: Newbury House Publishers, 1977.

Ben-Amos, D. "Context in Context." Western Folklore, 1993. Pp. 209-226.

Christian, Rapoled. "Towards a Grammar of Benchnon" University of Linden, 2006.

Dorson, Richard M. *Folklore and Folk Life: An Introduction*. London፡ the University of Chicago Press 1972.

Finnegan, Ruth. *Oral Tradition and the Verbal Arts: a Guide to Research Practices.* New York: Thomson Publishing Company, 1992.

Finnegan, Ruth. Oral Poetry: Its Nature, Significance and Social Context. Cambridge: Cambridge University Press, 1977.

Goldstein, Kenneth. *A Guide for Field Workers in Folklore*. American Folklore Society by Folklore Associates, INC. 1964.

Hallam, Elizabeth. "Death and the Transformation of Gender in Image and Text" in D. Field, J. Hockey and N. Small (eds.) *Death, Gender and Ethnicity*. London: Routledge, 1997. Pp.108- 124.

Krugor, Richared. Focus Groups: A Practical Guide for Applied Reasearch. New bury Park, CA Sage, 1994.

Lovell, Alice. "Death at the Beginning of Life" in D. Field, J. Hockey and N. Small (eds.) *Death, Gender and Ethnicity*. London: Routledge, 1997. Pp. 30-52.

Mary, Ann. "A Basic Vocabulary List of [Bench] and the Verb Root in [Benchnon]" University of Linden Press, 1981.

Rappaport, Roy A. *Ritual and Religion in the Marking of Humanity*. Cambrige: Cambrige University Press, 1999.

Sims, Martha. and Martine Stephens. *Living Folklore: An Introduction to the Study of People and their Traditions.* Ohio: Utah State University Press. 2005.

Small, Neil. "Death and Difference" in D. Field, J. Hockey and N. Small (eds.) *Death, Gender and Ethnicity*. London: Routledge, 1997. Pp. 209- 226.

Turner, V. Witter. *From Ritual to Theater: the Human Seriousness of Play*. The Michigan University, Performing Arts Journal Publication, 1982.

Vansina, Jan. *Oral Tradition as History*. USA: The University of Wisconsin Press.1985.

*World Book of Encyclopedia. World Book- Child Craft International*, Inc. Vol,5. USA. 1959.

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ፦ የመረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል

### ሀ. ቁልፍ መረጃ አቀባዮች

| ተ.ቁ | መረጃ አቀባይ ስም | ዕድሜ | ጾታ | ሥራ | መረጃ የተሰበሰበበት ቀን | መረጃ የተሰበሰበት ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ መሳህ ጴጥሮስ | 68 | ወ | የሀገር ሽማግሌ | የካቲት 19/2005 ዓ.ም | ኮብ ቀበሌ |
| 2 | አቶ ግርማ ግኘ | 37 | ወ | የመ/ሰራተኛ | ጥር 05/2005 ዓ.ም | አማን |
| 3 | ቄስ ሳሙኤል ዳልቴት | 45 | ወ | | ጥር 18/2005 ዓ.ም | ሚዛን |
| 4 | አቶ አለማየሁ ይርሴ | 73 | ወ | ጦረተኛ | ጥር 07/2005 ዓ.ም | ሚዛን |
| 5 | አቶ ኖፒ ኮይስተ | 78 | ወ | አርሶ አደር | የካቲት 17/2005 ዓ.ም | ጠመንጃጅ |
| 6 | አቶ አቤል ኤርዶ | 58 | ወ | ጦረተኛ | ጥር 07/2005 ዓ.ም | ሚዛን |
| 7 | አቶ ተሾመ ገብሬ | 43 | ወ | አርሶ አደር | የካቲት 14/2005 ዓ.ም | ኮብ |
| 8 | አቶ ባላካኝ ዘምቴት | 53 | ወ | የመንግስት ሰራተኛ | ጥር 03/2005 ዓ.ም | ቁጤ ከተማ |
| 9 | አቶ መኮንን ካሳ | 57 | ወ | አርሶ አደር | የካቲት 23/2005 ዓ.ም | ሚያህ |
| 10 | አቶ ኩን ናካ | 38 | ወ | የመንግስት ሰራተኛ | ጥር 07/2005 ዓ.ም | ዋቻ ማጂ |
| 11 | ወ/ሮ ዘነበች ኮምቴስ | 57 | ሴ | የቤት እመቤት | ጥር 12/2005 ዓ.ም | አማን |
| 12 | አቶ አንዱ አለም ጋይ | 42 | ወ | አርሶ አደር | የካቲት 13/2005 ዓ.ም | ዴሬታ |
| 13 | አቶ ቡንሶ ባይባ | 49 | ወ | አርሶ አደር | የካቲት 18/2005 ዓ.ም | ዘሚቃ |
| 14 | አቶ ሾጪ ባይቤስ | 73 | ወ | አርሶ አደር | የካቲት 13/2005 ዓ.ም | ጋቸብ |
| 15 | ወ/ሮ በሽቲት በቀለ | 55 | ሴ | የቤት እመቤት | የካቲት 21/2005 ዓ.ም | ጠመንጃጅ |
| 16 | ወ/ሮ ታደለች ወዳጆ | 48 | ሴ | የቤት እመቤት | ጥር 17/2005 ዓ.ም | ጋቸብ |
| 17 | አቶ ክፍሌ ለማ | 81 | ወ | ጦረተኛ | ጥር 07/2005 ዓ.ም | ሚዛን |
| 18 | አቶ ደረጀ ምርካና | 35 | ወ | የልማት መረጃ መሰብሰብና ማሰራጨት የስራ ሂደት አስተባባሪ | ጥር 12፣19 እና 27 | ደብረ ወርቅ |

## ለ. የንዑሳን መረጃ አቀባዮች

| ተ.ቁ | መረጃ አቀባይ ስም | ዕድሜ | ጾታ | ሥራ | መረጃ የተሰበሰበበት ቀን | መረጃ የተሰበሰበበት ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ወንድሙ አስረስ | 49 | ወ | የመንግስት ሰራተኛ | የካቲት 17/05 | አዲስ አለም |
| 2 | ወ/ሮ ሳራ አህመድ | 31 | ሴ | መምህርት | የካቲት 22/05 | ጠመጃጅ |
| 3 | አቶ ግርማ ከበደ | 28 | ወ | ጋዜጠኛ | ከጥር 08 እስከ ጥር 20/05 | ደብረ ወርቅ |
| 4 | አቶ ፍቃዱ አባዬ | 43 | ወ | የደብረወርቅ ከተማ የሰው ኃብት ኃላፊ | ጥር 06/2005 | ደብረ ወርቅ |
| 5 | አቶ ዮሐንስ ሞገስ | 27 | ወ | ጋዜጠኛ | ጥር 19፣ 23፣ የካቲ. 16፣18 21፣ እና 22 | ሚዛን |
| 6 | አቶ ማሞ ተስፋዬ | 29 | ወ | የቅርስ ጥበቃ ባለሙያ | የካቲት 17/05 | ደብረ ወርቅ |
| 7 | አቶ ወንድሙ ኩዱ | 30 | ወ | ጋዜጠኛ | ጥር 19፣ 23፣ የካቲ. 16፣18 21፣ እና 22 | ሚዛን |

## አባሪ ሁለት፡- ለቃለ መጠይቅ የቀረቡ የመነሻ ጥያቄዎች

1. የቤንች ብሔረሰብ ታሪካዊ አመጣጥ ምን ይመስላል?
2. ብሔረሰቡ ምን ምን ማህበራዊ ጉዳዮችን በጋራ ያከናውናል?
3. የቤንች ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት ታሪካዊ ዳራው ምን ይመስላል?
4. የቤንች ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት በስንት ይከፈላል? ምን ምን ተብለው ይከፈላል? ለመከፈል መሰረቱ ምንድን ነው?
5. በየትኛው የእድሜ ክልል ያለ ሰው ሲሞት ነው በጣም የሚለቀሰው? ለምን? በተቃራኒው ሐዘኑ የማይበዛውስ በየትኛው የእድሜ ክልል ውስጥ ያለ ሰው ሲሞት ነው? ለምን?
6. የለቅሶ ስርዓት የሚከናወነው ወይም ቀብር የሚደረገው በስንት ሰዓት ነው? ለምን? ለቅሶው እስከ ስንት ቀን ሊቆይ ይችላል?
7. ለለቅሶ ክዋኔ ማስኬጃ ብቻ ታስቦ የሚዘጋጂ ምግብ ይኖራል? ካለ ከሟች ጋር የሚያገናኘው ጉዳይ አለ? እንዴት?
8. አስከሬኑ በምን ይቀመጣል? ከምን ይሰራል? ለምን? ይህ ነገር ባይኖርስ? ማን ያዘጋጀዋል?

### ለቡድን ውይይት የቀረቡ የመነሻ ጥያቄዎች

1. ሰው ሲሞት ይለቀሳል? ወይስ ይዘፈናል? ወይስ ይጨፈራል? ለምን? ማነው ከሶስቱ አንዱን የሚከውነው ልጆች እነማን?
2. ሟች በሞተ በስንተኛው ቀን ይቀበራል? ብዙ ቀን የሚቆይበት ሁኔታ ይኖራል እንዴት/ ለምን?
3. ሴቶች ሲሞቱ የሚደረገው ስርዓት ወንዶች ጋር ተመሳሳይ ነው?
4. ማህበራዊ ፋይዳ ይኖረዋል? ለቅሶ የቀረ ሰው ምን ይባላል? የሚደርስበት ማህበራዊ ችግር ይኖራል?
6. በእድሜ ዘመንዎ ለቅሶ ስርዓቱ ላይ የተለወጠ  አለ የሚሉት ይኖራል?
7. ለቅሶ በህብረት መከወኑ ለማህበረሰቡ የሚሰጠው ጥቅም ይኖራል? ለምሳሌ....

## አባሪ ሶስት፡- የተሰበሰቡ የሙሾ ግጥሞች

| ቤንችኛ | አማርኛ |
|---|---|
| 1.ፍንፅይስ ሻቃን ምጣጉሽ ባባግዛዎ ነና | ነብር ገዳይ ነበርክ አባቴ በጫካ |
| ዶድ ባህይስ ሻቃን ምጣጉሽ ባባግዛዎ ነና | አንበሳ ገዳይ ነበርክ በጫካ |
| ጋምይስ ምጣጉሽ ባባግዛዎ ነና | ዝሆን ገዳይ ነበርክ በጫካ |
| ምያህ ጉድ ማክማኬ | ጉድ በል ሚያህ ጉድ በል |
| ኒያጋ ቦይ ምግንተናኝዎ | ዛሬ ነው ሀዘንህ ያድባርህ |
| 2. ሽል ኪያጽ ሙፅ ሽዓ | ቀረብን አሉ እንደልብ መብላቱ |
| ሽል ኪያጽ ኡሽ ሽዓ | ቀረብን አሉ እንደልብ መጠጣቱ |
| ሶያጋ ባስ ኡሽ ሽዓ | ቀረብን አሉ ፍትህ ዳኝነቱ |
| ባባ ፈንጻ ባያ ይስቱሽ ነና ሀይ ሹማ | አንተ ነብሩ ሞተህ እናት አባቱ፡፡ |
| 3. ኒያጋ ባካሽን ምባባ ኦናግያን ምባንስዎ | ባባ ወንበርህ ላይ ማን ይቀመጥ ከቶ |
| ኒያጋ ናቡጥይስ ምባባ ኦናግያን ኡናንስዎ | ባባ ጠመንጃህን ማን ይሸከም ከቶ |
| ኒያጋ ፈርይስ ምባባ ኦናግያን ጫንስዎ | ባባ ፈረስህን ማን ይጋልብ ከቶ |
| ኒያጋ ኩባይጣ ምባባዎ ሃኑሻያን ኢሽንስዎ | ባባ ባንተ መጠጫ ማን ይጠጣ ከቶ |
| ምያሃቃን ይስኬንድይ ኖር ሃክንሳርኑኤ ማኬንዴ | አንችልም አሉ ከሚያህ ሰው ታጥቶ |
| 4. ሩን ኡሽ ኤሽንይንድ ኬትንኡሽንይንድ ባይስ ነዓይስቱኤ | እናት ነበርሽ እኮ ለቤቱ ለደጁ |
| ፈርይ ማግ ኡርድይ (ፍንፅ) ሽዳማ | እንዲህ ለሚቀረው ሲዘጋጋ ደጁ፡፡ |
| ውይ…ይው…ይው…ውይ…. | ኡ…ኡ…ኡ…ኡ…. |
| ይያም ውሳ ሀምሲሻ ውቶይስ ፅያጽንድ | እግሯን እስሯት የምትሔድበትን |
| ይስን ኑና ሙፅኩሻጋ ውጋ ኩኛ ሽድማኬ | እጇንማ ለምን የበላንበትን፡፡ |
| 5. ንያጋ ኒያፅንድይ ኪይንቃን እር ዳማ | ባባ ልጆችን ተንጫጩ ዛሬ ወድቆባቸው |
| ንያጋ ዘሳንድ አይንቃን ምጣ ምባባዎ | ባባ ጎረቤቶች ተንጫጩ ዛሬ ወድቆባቸው |
| ባስይስ ብይየኑናራድ ኑግንቃነ እያርዳማ | ባባ ተበዳዮች ተናጫጩ ዛሬ ወድቆባቸው |
| ንያጋ ጽያንታንድይ ምባባዎ ቦይስታንገንዴ | ባባ ላሞቹ ተናጫጩ ዛሬ ወድቆባቸው |
| ጾጥንድይ ሻቃንደሳት ኪይንቃን ምጣንጌንዴ | ባባ አራዊቶች ተንጫጩ ዛሬ ወድቆባቸው |
| ይፀቀንአጋ ክንግኤሽን ይርሻጋ ኩስ ነናጻ | የሁሉም ባረፊያ አንተ ነበርካቸው |

| | |
|---|---|
| ይፀቀንአጋ ክንግኤሽን ካርታና ነናጻ | የሁሉም መፍትሔ አንተ ነበርካቸው |
| ይፀቀንአጋ ክንግኤሽን ይጥ (ሽታንይ) ነናጻ | የሁሉም ጠበቃ አንተ ነበርካቸው። |
| 6. ንያስ ወፈሰ ታማን ዎጥኤፈሰርጉኤ | ያንተ ሞት ሞት ሳይሆን ክብር ነው |
| ንያስ ዎርዶንተ ታማን ዎጥኤሳርጉኤ | ያንተ ሞት ሞት ሳይሆን ስርግ ነው |
| ንያስ ካዃ̈ታማን ዎጥኤሳርጉኤ | ያንተ ሞት ሞት ሳይሆን ደስታ ነው |
| ንም ሽዱሽ ቦጋ ክንግይ ፋቱሻግዛዎ | የቀረህ ጉዳይ የለም ሁሉም የተፈፀመ ነው |
| 7. ኤስን ድጋምይስቶ ዎባባዎ | በል ደህና ሁን አባባ |
| ንያጋ ማሽጉዳድን ሀክንሳርጉሽኤሽን ጉሳይ ድሮ | ይልቅ መርቀን መንፈስህ አይራቀን |
| ንያጋ ሚያንግ ጉዳድኒ ሀካርጉ ጉይስ ባቅማኬ | ቃልቻህ አይራቀን እኛን ይጠብቀን |
| በርግይስ ኑና ያፈንሴሽን | እድሜ እንዲሰጠን |
| ግዝይስ ኑና ሀጂንሲ ሻኤሽን | ሀብት እንድናፈራ |
| ድግይስ ኑና ያፈንሲሻኤሽን | ጤና እንድናገኝ |
| ኑጋ ንያአም ኑና ሀብንሳርጉሽኤሽን | በልጅነታችን እንዳንሞት |
| ንያጋ ማሽ ኑዳድን ሀክሽንማኬ | መንፈስህ አይራቀን |
| ንያጋ ምያንግ ጉዳድን ሀክሽንማኬ ጉይስ ባቀማኬ | ቃልቻህ አይራቀን፣ ይጠብቀን |
| ንያጋ ቤርግይስ ኑም አስማኬ | ያንተን እድሜ ይስጠን |
| 8. እርሽ ቦጋ እርሻም ሀይቃ (ባኣ) | ልጅ በልጅነቱ ተቀጨ |
| ኢሳጋ ንያዕ አጥን አታርጉይስትያ | እንደሰው አልሆነ |
| ማሽታይድ ኡትውዋርጉኤ | ትዳር አልያዘ |
| ንያዕድ ሳርጉኤ | ልጅም አልወለደ |
| ኔናቃይፁሽጋ ሻብይስ | ያረስከውን አዝመራ |
| ሙፅክርጥይስታ ነናሻዓ | ሳትከውን ቀረክ |
| ዎዳ ኪያጽርጉይስታ | ሩጠህ ሳትጨርስ |
| ኡይንጣም ነና ሽዳ | በአጭሩ ተቀጨህ |
| ታይስ አፈርቅን ሀስማኬ | እኔን ያስቀድመኝ |
| ምያት ታና በቃ | ብዙ አይቻለሁ |
| ንያዕድ ታና የለ | ልጅም ወልጃለሁ |

አባሪ አራት፡ ጥናት የተካሄደበትን አካባቢ የሚያመለክት ካርታ




ምንጭ፡ ከቤንች ማጂ ዞን ከተማ አስተዳደር ቢሮ የተወሰደ

አባሪ አራት፡ ጥናት የተካሄደበትን አካባቢ የሚያመለክት ካርታ




ማውጫ (ቤንች ማጂ ዞን)

1. ጉራ ፈርዳ
2. ሸኮ
3. ደቡብ ቤንች
4. ሼ ቤንች
5. ሜኒት ጎልዲያ
6. ሜኒት ሻሻ
7. ቤሮ
8. ማጂ
9. ሱርማ
10. ሰሜን ቤንች
11. ሚዛን-አማን

ምንጭ፡ የቤንች ማጂ ዞን ካርታ (ከቤንች ማጂ ዞን ፋይናስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የተወሰደ)

ይህ የጥናት ወረቀት ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያነት በእኔ የተሰራ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ውቤ ታደገ